# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## አስረኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ
አስረኛ ክፍል

አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

የመምህር መምሪያ




የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

# አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## አስረኛ ክፍል


**አዘጋጆች፡**

ሡሉጌታ ደታየው (ፒ.ኤች.ዲ)

ጋሻው አረጋ (ፒ.ኤች.ዲ)

**አርታኢዎች፡**

ታደሰ ሲባሞ (ፒ.ኤች.ዲ)

ጌታቸው አዱኛ (ፒ.ኤች.ዲ)

**ሰዓሊ፡**

ታደሰ ደሄደስ (ኤም.ኤስ.ሲ)

**ዲዛይነር፡**

አጥናፉ ዓለሙ (ኤም. ኤስ. ሲ)

**ገምጋሚዎች፡**

ሠኮንን አስማማው (ኤም.ኤ)

ግሩም ጥበቡ (ኤም.ኤ)

ፍሬሕይወት አሰፋ (ኤም.ኤ)



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ

# ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው ስራ የተጀመረው በ2022 እ.ኤ.አ ሲሆን፣ የዲዛይን፣ ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስ በትምህርት ሚኒስቴር በአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP-E) አማካኝነት ነው። የገንዘቡ ምንጭ ደግሞ ብድርና እርዳታ ነው። አበዳሪዎችም፦ የዓለም ባንክ፣ የእንግሊዝ ዓለማቀፍ ልማት ድርጅት (DFID) ከውጭ ልማት ቢሮ (FCDO) ጋር በመተባበር፣ ከፊላንድ የውጭ ጉዳይ ቢሮ፣ ከኖሮጂያን ኢንባሲ፣ ከተባበሩት መንግስታት የህጻናት ፈንድ (UNICEF)፣ ከአለማቀፍ የትምህርት አጋርነት ድርጅት (GPE) እና ከዳኒሽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዓለማቀፉ ትረስት ፈንድ በኩል እገዛው ተገኝቷል። ለዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል።

© በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም

የዚህን መጽሐፍ ክፍል ያለባለቤቱ ፈቃድ በተለያዩ መሳሪያዎች እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የሚያመለክት ሲሆን፣ በተጨማሪም የኮፒራይትና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 55 10ኛ ዓመት አዲስ አበባ ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ይከለክላል።

ይህ መጽሐፍ ለህትመት እንዲበቃ ተሳትፎ ላደረጉ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና የተለያዩ ባላድርሻ አካላት ትምህርት ሚስቴር ምስጋናውን ያቀርባል። በተለይ ደግሞ ትልቁን የማስተባበር ድርሻ በመውሰድ የጽሑፉን ዝግጅት ላስተባበረው ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአጋሮቹ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ የላቀ ምስጋና ይደረሳቸው ይላል።

የኮፒራይትና የሥዕል ባለቤትነት መብቶችን በተቻለ መጠን ለማክበር የሚቻለው ሁሉ ጥረት ተደርጓል። ነገር ግን ሳናወቅ በስዕተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ጽሑፎችና ስዕሎች ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን፣ ስዕተቱን አራት ኪሎ በሚገኘው ዋና መስሪያቤት፣ ትምህርት ሚኒስቴር በአካል በመቅረብ ማመልከት የሚቻል ሲሆን፣ በአካል መምጣት የማይችሉ ደግሞ በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 1367 አዲስ አበባ ብለው መላክ ይችላሉ።

አሳታሚ ድርጅት

_____________ማተሚያ ቤት

የመ.ሳ.ቁ-----------------------

--------------------ኢትዮጵያ

በትምህርት ሚኒስቴር ውል ቁጥር__________

ISBS:978-999944-2-046-9

# መቅድም

ትምህርትና ልማት በቅርበት የተያያዙ፣ ግባቸው አንድ የሆነ ጥረቶች ናቸው። ትምህርት የልማትና ማህበራዊ ለውጥ ቁልፍ መሳሪያ ነው የሚባለበት ዋናው ምክንያትም ይህ ነው። አሁን የምንኖርበት ፈጣን እና ተለዋዋጭ ዓለም በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ አዲስ እውቀት፣ ችሎታና አመለካከት ይፈልጋል። ከዚህ አላማ አንጻር ሥርዓተ ትምህርቱ ብሉ ፕሪንት ብቻ ሳይሆን የአንድ ሀገር የትምህርት ስርዓት ነጸብራቅ ሆኖ ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጥ መሆን አለበት።

ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ከጀመረችና ተግባራዊ ካደረገች ወደ ሶስት አስርት አመታት ተቆጥሯል። ከ1994ቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጀምሮ አገራችን በተደራሽነት፣ በፍትሃዊነትና በአግባብነት አመርቂ እድገት አስመዝግባለች። የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ጠንካራ ጥረቶች ተደርገዋል፤ አሁንም እየተደረጉ ናቸው።

ይህንን እድገት ለማስቀጠል የትምህርት ሚኒስቴር በ2021 አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል። ማዕቀፉ ሁሉንም የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶችን ያጠቃልላል። ማዕቀፉ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውስጥ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ መርሆችን ለማጠናከር ያለመ ሲሆን፣ በቀጣይ የሥርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶች ዝግጅት ላይ መመሪያ ይሰጣል። ይህን የመምህሩ መመሪያና የተማሪ መማሪያ መጽሐፍን ጨምሮ፤ በንቃት የመማር ዘዴዎች የማስተማሪያ ብልሃቶች ላይ የተመሰረተ ነው።

ለዚህ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት እ.ኤ.አ. በ2018 የተካሄዱት የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናቶችና ምክሮች እንደ ዋና መነሻ ያገለግላሉ። የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶች ይዘቱን ከተማሪዎች ዕድሜ ጋር በማመጣጠን፣ አገር በቀል ዕውቀትን መጠቀምን፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቴክኖሎጂን ለመማር እና ለማስተማር መገልገልን፣ የሙያ ይዘቶችን በማዋሃድ፣ የሞራል ትምህርትን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት በማካተት የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርትን በደረጃው እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችልና የተማሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ የትምህርት ዓይነቶችን ለማካተት ጥረት ተደረጓል።

በየትኛውም ሀገር የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል አዲስ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የመማሪያ መጽሃፍትን ማሳተምና የመምህራን መመሪያዎች መታተም በምንም መልኩ ብቸኛ መፍትሄ አይደሉም። ቀጣይነት ላለው መሻሻል የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ጥረት ይጠይቃል። የመምህሩ ሚና ከአስተማሪነት እስከ አነሳሽነት፣ ከመሪነት እስከ አስተባባሪ ድረስ የበለጠ ተለዋዋጭ መሆን አለበት። ለዚህም መምህራን በማዕቀፉ እና በዚህ የመምህራን መመሪያ ላይ በተጠቆሙት ስልቶች ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

መምህራን ይህንን መመሪያ በጥንቃቄ እንዲያነቡትና በውስጡ የተጠቆሙትን ስልቶችን እና ተግባራትን በተግባር በማዋል ተማሪዎቻቸውን እንዲደግፉ እናሳስባለን።

የትምህርት ሚኒስቴር ለሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያና ቀጣይነት ያለው የሥርዓተ ትምህርት ቁሳቁስ ጥራት መሻሻል፣ ተጨማሪ ግምገማና ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችሉንን አስተያየቶችንና ግምገማዎች በደስታ ይቀበላል።

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትምህርት ሚኒስቴር

xxxxx 2014

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


መግቢያ ....................................................................i

ምዕራፍ አንድ፡ የሥራ ባህልና ምርት ....................................................1

ምዕራፍ ሁለት፡ የህይወት ክህሎቶች....................................................12

ምዕራፍ ሶስት፡ ሱስና አደንዛዥ ዕፅ ....................................................22

ምዕራፍ አራት፡ ልቦለድ ....................................................31

ምዕራፍ አምስት፡ እንግዳ ተቀባይነት ....................................................41

ምዕራፍ ስድስት፡ ባህላዊ ክንውኖች ....................................................49

ምዕራፍ ሰባት፡ አካቶ ትምህርት ....................................................59

ምዕራፍ ስምንት፡ ሥነግጥም ....................................................68

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ አንድነትና ብዝሃነት ....................................................77

ምዕራፍ አስር፡ ስደት ....................................................85

ማጣቀሻ ....................................................92

ሥርዐተ ትምህርት ....................................................93

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ በአጠቃላይ ስለቋንቋ ትምህርት የማስተማር መርሆዎችና ዘዴዎች የሚያብራራ ነው። በተናጠል ደግሞ አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀውን መጽሐፍ ለመተግበር የሚያስፈልጉ አንዳንድ መሠረታዊ መንገዶችን ለመምህራን በመጠቆም የሚያግዝ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በመጽሐፉ ውስጥ ለቀረቡት መልመጃዎች የጋራ ሊሆኑ የሚችሉ ናሙና መልሶችንም አካቶ ይዟል።

በመምህር መምሪያው ውስጥ ሁሉም ነገር እንዲካተት አይጠበቅም። ይልቅስ አበይት ይዘቶቹን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የተማሪዎችን ነባራዊ አውነታ ባገናዘበ ሁኔታ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር መጠቆሚያዎችን፣ ማመላከቻዎችንና ፍንጮችን መስጠት ይጠበቃል። መምህራን በዚህ ግንዛቤ ላይ ተመሥርተው አቀራረቡን የበለጠ ማራኪና አመቺ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን ተጨማሪ የአቀራረብ ዘዴዎችን ማሰብና በሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ። ተማሪዎቹ ዘና ባለ ሁኔታ ትምህርቱን በጉጉት እንዲከታተሉ ለማትጋት የመምህራን ኪናዊ አቀራረብ ወሳኝ ነው። በተለይ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ባህልና የዕውቀት ደረጃ ጋር የተገናዘቡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችንና ሌሎች ጨዋታ-ቀመስ ተግባራትን በመጠቀም የትምህርቱን ሂደት ሳቢና፣ ክፍለ ጊዜውንም ተናፋቂ ማድረግ ይቻላል።

ውድ መምህራን፣ የክፍለ ጊዜ ስርጭትን በሚመለከት በዚህ መምሪያ ላይ የተመለከተው አጠቃላይ የምዕራፉን የጊዜ መጠን የሚያመለክት ስለሆነ፣ ለእያንዳንዱ ተግባር የሚበቃችሁን የጊዜ ምጣኔ ለእናንተ የተተወ መሆኑን ተገንዝባችሁ ጊዜውን እንዳስፈላጊነቱ በእየተግባሩ በመከፋፈል እንድትጠቀሙ ይመከራል።

# ምዕራፍ አንድ፡ የስራ ባህልና ምርት (8 ክፍለ ጊዜ)

## ርእስ፡ የስራ ባህል

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፦

- አዳምጠው መረጃዎችን ይናገራሉ፡፡
- በአዳመጡት መሠረት የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡
- የሥራ ባህልና ምርት ከሚለው ምንባብ ያዳመጡትን ፍሬ ሀሳብ ያብራራሉ፡፡
- በተመረጡ ይዘቶች ላይ ውይይት ያካሄዳሉ፡፡
- አውድን መሠረት ያደረገ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- በሚና-ተኮር ልምምድ ንግግር ያከናውናሉ፡፡
- ምንባብ አንብበው የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡
- ሀሳቦችን አፍልቀው ይጽፋሉ፡፡
- የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡
- ቃላት ምንባብን ለመረዳት ያላቸውን አስተዋጽኦ ይገልጻሉ፡፡
- የቃላትን ቀጥተኛና አውዳዊ ፍችዎች ይሰጣሉ፡፡
- በቃል ውስጥ የሚገኙ ምእላዶችን ይለያሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ሰነፍ ይከስራል፣ ሰራተኛ ይከብራል

#### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- “ሰነፍ ይከስራል ሠራተኛ ይከብራል” በሚል ርእስ መምህሩ/ሯ የሚያነቡላቸውን ምንባብ በማዳመጥ ማስታወሻ በመያዝ ይናገራሉ፡፡
- በአዳመጡት መሠረት የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

#### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የሥራ ባህልና ምርታማነትን አስመልክቶ ምንባብ ማዳመጥ
- በሥራ ባህል ላይ መወያየትና መከራከር

## የክፍል ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

በክፍል አንድ ስር ማዳመጥን ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች የምዕራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸው:: በመቀጠልም "ሰነፍ ይከስራል፤ ሠራተኛ ይከብራል" የሚለውን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው:: ከዚያም በዚህ ርእስ አንድ ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ ይንገሯቸው:: ማንበብ ከመጀመርዎ በፊት ግን ሁሉም ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሳተፉ፣ በጥሞና እንዲያዳምጡና ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግዎን አይዘንጉ::

ማዳመጥ የትምህርቱ መጀመርያ በመሆኑ ልዩ ጥንቃቄና ማራኪ አቀራረብ ያስፈልገዋል:: ስለሆነም ታላሚ ተማሪዎቹን "ሰነፍ ይከስራል፤ ሠራተኛ ይከብራል" የሚለውን ይዘት ከማስደመጥዎ በፊት የማዳመጥ ደረጃቸውን በውል መገንዘብ ይጠበቅብዎታል:: ስለሆነም የእለቱን የማዳመጥ ይዘት ለመተግበር የሚያስችል ጥቂት መረጃዎች ለማቅረብ እንሞክራለን:: አላማ መራሽ ማዳመጥን ለማስተማር ሲዘጋጁ ሦስቱን የማዳመጥ ደረጃዎች መከተል ያስፈልጋል:: እነሱም:-

1. በቅድመ ማዳመጥ
2. በማዳመጥ ጊዜ
3. ድህረ ማዳመጥ ናቸው::

ስለሆነም ቀጣዩን የማዳመጥ ምንባብ ለማስተማር ከፍ ሲል የተገለጹትን ደረጃዎች ልብ ሊሉ ይገባል፤ ለተማሪዎቹም ማስገንዘብ ይኖርብዎታል::

ውድ መምህር/ት፣

ከታች የቀረበውን ምንባብ ከማስደመጥዎ በፊት ቀጥሎ በቀረቡት ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች ያላቸውን ሀሳብ እንዲያጋሩ ያድርጉ::

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የስኬት ምስጢሮች የምትሏቸውን ዘርዝሩ::
2. በሕይወት ውስጥ ውጤታማ ለመሆን ዕደለኛ ከመሆንና ጠንክሮ ከመስራት ወሳኙ የትኛው ነው?

አሁን ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ለሁሉም ተማሪዎች ሊሠማ በሚችል ድምጽ በዝግታ ያንብቡላቸው:: አንብበው እንደጨረሱ ደግሞ በተማሪዎች መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው::

## ሰነፍ ይከስራል፤ ሠራተኛ ይከብራል

የተሰጠችውን የሕይወቱን ጊዜ  በዓለም ላይ ሲያሳልፍ ምን ዓይነት ሥራ እየሠራ ቢኖር የሚሻል መሆኑን ለመምረጥ አቅቶት ብዙ ጊዜ ይህንኑ ሀሳብ በልቡ ሲያወጣና ሲያወርድ የሚውል አንድ ሰው ነበር። ይህንኑ ሲያስብ አንድ ቀን በልቡ እንዲህ አለ። "የወረስኩት ጥሩ ርስት አለኝ። ይህንን ርስቴን እህል ብዘራበትና አትክልት በያይነቱ  ብተክልበት መጀመሪያ መሬቱ ይለማል። ሁለተኛም ገንዘብ አገኝበታለሁ። ስለዚህ  ጥቅሜ በሁለት ወገን ይሆናል። በዚያ ላይ ለማሠማራት ብዙ የአባቴ ሠራተኞች ስላሉኝ ሌላም ሠራተኛ አያሻኝ" ብሎ ሀሳቡን በዚህ አቆመ።

ለዚህ የሚሆነውን ልዩ ልዩ የሥራ መሥሪያ መሣሪያዎችን አሰናድቶ የአባቱን ሠራተኞች ጠርቶ እንዲህ አላቸው። "በአባቴ ርስት ላይ በብዙው እህል ለመዝራትና ልዩ ልዩ የምግብ አትክልት ለመትከል አስቤያለሁና ከዛሬ ጀምራችሁ ጧት ጧት ወደ ርስቴ እየሄዳችሁ እንድትሠሩ" ብሎ አዘዛቸው። ከዚያ ቀን ጀምሮ በጧት ተነሥቶ ሠራተኞቹን "ሂዱ ሥሩ" እያለ ይልካቸውና እሱ የትም እየዞረ ሲጠጣ፣ ሲጫወት፣ ሲፈነጥዝ ይውላል። ለሦስት ዓመት ያህል እንደዚህ ከኖረ በኋላ፣ ከእርሻውና ከአትክልቱ ያገኘው ገንዘብ እንኳንስ ሀብት ሊሆነውና የሠራተኞቹን ልብስና ምግብ ሳይችል ቀረ።

### ማደመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ከላይ ካዳመጣችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?
2. ከቀጣዩ የታሪክ ክፍልስ ምን ትጠብቃላችሁ?

ሀሳቡ በጣም መልካም ሆኖ ሳለ ብዙ ገንዘብ ሳያተርፈው በመቅረቱ አዝኖ ርስቱን ከሁለት ከፈለና አንዱን እኩሌታ ሸጠው። አንደኛውን እኩሌታ ግን አከራየው። የተከራየውም ሰው ሦስት ዓመት ሙሉ የእርሻና የአትክልት እንዲሁም ደግሞ ከብት የማርባት ሥራ እየሰራ  በየአመቱ የኪራዩን ዋጋ ትክክል ሲከፍለው ከቆየ በኋላ ወደ ባላቤቱ ዘንድ እንዲህ ሲል መጣ። "ባለቤት ሆይ፣ ያንተን መሬት በመከራዬቴ መልካም እድል ሆነልኝ። ገንዘብ አገኘሁበት። አሁንም የሦስተኛውን ዓመት ኪራይ እነሆ ተቀበለኝ። ደግሞ የምለምንህ አንድ ነገር አለ። ምናልባት ይህን የተረፈውን የርስትህን እኩሌታ ለመሸጥ ፈቃድህ ቢሆን ዋጋውን ልሰጥህ የተዘጋጀሁ ነኝና ለሌላ ሰው አትሸጥብኝ።" ባለቤቱም ቀድሞ የተቀበለውን የመሬቱን ዋጋ አባክኖ ጨርሶ ገንዘብ ቸግሮት ነበርና ደስ አለው። ስለ ዋጋውም ነገር ወዲያው ተነጋገሩና፣ ከተከራከሩ በኋላ በመጨረሻ ተስማሙ።

"እኔ በዚህ መሬት ላይ ባንድ በኩል እየዘራሁ፣ ባንድ በኩል አትክልት በያይነቱ እያስተከልኩ ሦሥት ዓመት ሙሉ ሠርቼ ምንም አላተረፍኩም። አንተ ቦታውን ከእኔ ተከራይተህ፣ በየዓመቱ ኪራዩን ትከፍላለህ። እኔ ግን ርስቴ ነውና ምንም አልከፍልበትም። አንተ ለሠራተኞቹ በየቀኑ የሠሩበትን ሒሳብ ትሰጣቸዋለህ። እኔ ግን ለአባቴ ሠራተኞች የሚበሉትንና የሚለብሱትን መስጠት ብቻ እንጂ ሌላ ትርፍ ገንዘብ አላስብላቸውም። አንተ በግማሹ ርስቴ ላይ ብቻ ነው የሠራኸው፤ እኔ ግን በሙሉ ላይ ነበር። እኔ በሦሥት ዓመት ምንም ሳላገኝበት፣ አንተ በሦሥት ዓመት ውስጥ ይህን ሁሉ ጣጣ ችለህ መሬቱን

ለመግዛት የበቃ ገንዘብ ያተረፍከው እውነት በእኔ መሬት ላይ ሠርተህ ባፈራኸው ነው ወይስ ከሌላ ዘንድ ባገኘኸው ገንዘብ ነው?" ብሎ ባለቤቱ ተከራዩን ጠየቀው:: ሰውየውም "ባንተ መሬት ላይ ሠርቼ ባተረፍኩት ነው" ብሎ መለሰለት::

"እኔ ስከሥር አንተ ይህን ያህል ያተረፍከው ምክንያቱ ምንድን ነው?" ብሎ መልሶ ጠየቀው:: "አንተ ጧት ስትነሳ ሠራተኞችህን ሂዱ ሥሩ ብለህ ትልካቸዋለህ:: እኔ ግን ጧት ተነስቼ ሠራተኞቼን 'ኑ እንሂድ እንሥራ' እላቸዋለሁ:: ምክንያቱ ይህ ብቻ ነው" ብሎ መለሰለት:: "ሂዱ ሥሩ በማለትና ኑ እንሂድ እንሥራ በማለት መካከል ምን ዐይነት ልዩነት አለ?" ብሎ አሁንም ደገመና ቢጠይቀው "ልዩነቱማ አንተ ጧት ተነስተህ ሠራተኞችህን ሂዱ ሥሩ ብለህ ትልካቸውና አንተ ጨዋታና ፈንጠዝያ ወደሚገኝበት ቦታ እየሄድህ ገንዘብህንና ጊዜህን በከንቱ ስታሳልፍ ትውላለህ:: ሠራተኞችህ ደግሞ ጊዜያቸውን በጨዋታና በመግገጥ ያሳልፋሉ እንጂ ምንም ሥራ አይሠሩ፤ አንተ ወደ ጨዋታ መሄድህን ስለሚያውቁ አንተ የምትሰጣቸውን መጥፎ ምሳሌ እየተከተሉ በልባቸው ስንፍና ያድራል:: አንተም ደግሞ ወደ ሥራ መሄዳቸውን ብቻ እንጂ መሥራታቸውንና አለመሥራታቸውን አጠገባቸው ሆነህ ስለማትመለከት ልትቆጣጠራቸውና ልትቆጣቸው አትችልም:: እነሱም ምንጊዜም ቢሆን የሚበሉትንና የሚለብሱትን እንደማትነሣቸው ያውቃሉና ሥራው ቢሠራም ባይሠራም ግድ የላቸውም::

"ስለዚህ ያንተ ጉዳት በሁለት በኩል ነው:: መጀመሪያ፣ አንተ አትሠራም፤ ደግሞ ገንዘብ ስታባክን ትውላለህ:: ሁለተኛ፣ ሠራተኞችህ ምንም አይሠሩ፤ ሰነፎች ናቸው:: ግን አንተ በግድ ቀለባቸውንና ልብሳቸውን ትችላለህ:: አንተ ያልከሠርክ ማን ይክሠር::

"እኔን ብትለኝ ግን፣ ጧት በማለዳ ከመኝታዬ ተነስቼ 'ኑ እንሂድ እንሥራ' ብዬ ሠራተኞቼን ከፊት አስቀድሜ ወደ ሥራ እሄዳለሁ፤ እዚያም ስደርስ ባጭር ታጥቄ በመካከላቸው ሆኜ ስሠራ እውላለሁ:: እነሱም እኔ ስሠራ እያዩ ሊጫወቱ ወይም ሊማግጡ በፍጹም አይችሉም:: የስንፍና ምልክት የሚያሳይ ሠራተኛ ቢኖር በገንዘቡ እቀጣዋለሁ:: ማታም ሲሆን ሠራተኞቼ ወደየቤታቸው ሲበታተኑ እኔ ከኋላ ቀርቼ የተበላሸውን አስተካክዬ፣ የተሠራውን ተመልክቼ ሁሉንም በሥርዐት አድርጌ ቆይቼ ወደ ቤቴ እገባለሁ:: እንደዚህ ሠርቼ እኔ ያላተርፍኩ ማን ያትርፍ:: ይኸውልህ "ሂዱ ሥሩ በማለትና ኑ እንሂድ እንሥራ" በማለት መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት ይህ ነው ብሎ ገንዘቡን ሰጠው:: ባለርስት የነበረው ሰው የመሬቱን ሽያጭ ገንዘብ ይዞ ወደ ፈንጠዝያ ቦታ ሄደ፤ ተከራይቶም የነበረው መሬቱን ገዝቶ ወደ ሥራው ተመለሰ::

(ከበደ ሚካኤል:: 1999:: ገጽ 50-53 መጠነኛ እርማት ተደርጎበት የተወሰደ)

## ክፍል ትምህርት ሁለት: ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ውይይት ያደርጋሉ::
- እንደየአውዱ መናገር ይችላሉ::
- በሚና ጭዋታ ንግግር ይሳተፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ውይይት ማካሄድ::
- በሚና ለዋጭ ተግባራት መሳተፍ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ክፍለ ትምህርት ሁለት ንግግር የሚለው ክፍል በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችና ሚና ለዋጭ ንግግሮች እንዲያደርጉ ቀርቧል:: ይህንን ለማከናወን በውይይት ጊዜ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ ነጥቦችን ለተማሪዎችዎ ያስረዱ:: በቅድመ ንግግር፤ በጊዜ ንግግር እና በድኅረ ንግግር ምን ማከናወን እንደሚገባ ስለ ማዳመጥ እና ስለ ንባብ ደረጃዎች የተሰጡትን ገለጻዎች ከዚሁ ጋር ማነጻጸርና መተግበር ያስፈልጋል:: በመቀጠል የቀረቡትን ተግባራት ለማሠራት ለእርስዎ አመቺ በሚሉት መንገድ ተማሪዎችን በቡድን ይከፋፍሉ:: በዚህ ክፍል በተራ ቁጥር ፩ ና ፪ የቀረቡትን ተግባሮች በመመሪያው መሠረት እንዲሠሩ ያግዟቸው::

### ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## አውራምባ

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለ አውራምባ የስራ ባህል አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ::
- በምንባቡ የቀረቡ መረጃዎችን ይተነትናሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- ጠንካራ የሥራ ባህል::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ይህ ምንባብ በምዕራፉ የመጀመሪያ ትምህርት በመሆኑ ከፍ ሲል ስለ ማዳመጥ ትምህርት እንደተገለጸው ምንባብም ልዩ ጥናቃቄና ማራኪ የትምህርት አቀራረብ ያስፈልገዋል:: ስለሆነም ታላሚ ተማሪዎቹን የዕለቱን ምንባብ ከማስነበብዎ በፊት የንባብ ደረጃዎችን በውል መገንዘብና ተማሪዎቹንም ማስገንዘብ ይጠበቅብዎታል:: ከዚያ በኋላ የእለቱን ምንባብ ለመተግበር የሚያስችል የመማር ማስተማር ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል:: አላማ ተኮር ንባብን ለማስተማር ሲዘጋጁ ሦስቱን የንባብ ደረጃዎች መከተል ያስፈልጋል:: እነሱም:-

1. ቅድመ ንባብ

2. የንባብ ጊዜ

3. ድኅረ ንባብ ናቸው።

ስለሆነም ቀጣዩን ምንባብ ለማስተማር ከፍ ሲል የተገለጹትን ደረጃዎች ልብ በማለት ለተማሪዎቹም ማስገንዘብ ይኖርብዎታል።

ውድ መምህር/ት!

በእያንዳንዱ ደረጃ ምን ምን ተግባራት ይከናወናሉ?

**በቅድመ ንባብ ጊዜ፡**

- ተማሪዎችን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሚያሠሩበት ደረጃ ነው፤
- ተማሪዎች የዕለቱን ንባብ ከማንበባቸው በፊት አጭር ውይይት የሚያካሂዱበት ደረጃ ነው፤
- ተማሪዎች የዕለቱን ንባብ ለማንበብ ጉጉት እንዲያድርባቸው የሚያደርጉበት ደረጃ ነው።
  ተማሪዎች አካላዊና ህሊናዊ ዝግጅት በማድረግ ምንባቡን ለማንበብ የሚያሰናዱበት ደረጃ ነው፤
- "አንድ ኳስ ተጫዋች ሰውነቱን አሟሙቆ ወደ ጫዋታ እንደሚገባ ሁሉ" የንባብ ስሜታቸውን በመቀስቀስ ተማሪዎችዎን የሚያዘጋጁበት ደረጃ ነው፤
- ደረጃው ለንባብ ማዘጋጃ በመሆኑ ስለንባብ ጠቀሜታና ስሜት ቀስቃሽ ተግባራት ማከናወን እንጂ የምንባቡን መልእክት መንገር የለብዎትም፤ ይህ ከሆነ ተማሪዎችዎ የምንባቡን መልእክት አስቀድመው ካወቁት የዕለቱን ምንባብ ሊያነቡት አይችሉም፤
- በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹን ሊያነቃቁ የሚችሉ ጥያቄና መልስ፣ ቀልድ ብጤ፣ ተረት፣ የሚያዝናና ግጥም፣ ወዘተ (በተማሪው መጽሐፍ እንደተገለጸው) በማቅረብ ተማሪዎችዎን ለዕለቱ ንባብ ማዘጋጀት ይችላሉ፤ የሚቀርቡት ጥያቄዎችም ሆኑ ቀልዶች ከሚነበበው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚገናኙ ሊሆኑ ይገባል፤
- የእለቱን የምንባብ ርዕስ የሚመለከት አጭር ድራማ በማሠራት ለንባብ ሊያዘጋጁዋቸው ይችላሉ፤
- ለዚህ የማነቃቂያ ተግባር የሚያስፈለገው ጊዜ ከሁለት እስከ አምስት ደቂቃ ብቻ በቂ ነው፤

የቅደመ ንባብ ጊዜ ሳይንዛዛ ወደ ዋናው ይዘት መግባት ያስፈልጋል። ስለዚህ እርስዎ ከፍ ሲል ከተገለጹት አንዱን በመምረጥ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ሊያሰሩ ይችላሉ።

**በንባብ ጊዜ፡-**

- መምህሩ/ሯ ተማሪዎቹ/ቿ በንቃት ላይ የተመሠረተ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን የሚቆጣጠር/ የምትቆጣጠርበት ደረጃ ነው፤
- ተማሪዎች ወደ ዋናው ነጥብ የሚያተኩሩበት ደረጃ ነው፤
- መምህሩ/ሯ የተማሪዎቹ/ቿ የንባብ ሂደት ዳር የሚያደርስበት/የምታደርስበት ደረጃ ነው፤

- ተማሪዎች አንቀጽ ከአንቀጽ፣ አንቀጽ ከተከታዩ ይዘት፣ የሐሳብ ትስስር፣ ወዘተ ያለውን ዝምድና የሚገነዘቡበት ደረጃ ነው፤
- በዚህ ጊዜ ተማሪዎችዎ የንባብ ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ደረጃ ነው፤
- ተማሪዎችዎ የምንባቡን ምግብ የሚመገቡበት ጊዜ እንጂ ሌላ ሰው ሲያነብ የሚያዳምጡበት ጊዜ አይደለም፤
- ተማሪዎችዎ የምንባቡን መልዕክት እየተገነዘቡ የቋንቋ ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ጊዜ ነው፤
- ተማሪዎችዎ በየግላቸው መጽሐፋቸውን በመያዝ በፀጥታ የሚያነቡበት ጊዜ ነው፤
- ይህ ጊዜ ፀሐፊና አንባቢ የሚገናኙበት ጊዜ በመሆኑ ተማሪዎች በነፃነት ራሳቸውን ችለው የሚያነቡበት ጊዜ ነው፤
- ይህ ጊዜ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ለመሥራት የሚያስችላቸውን ግንዛቤ የሚያገኙበት በመሆኑ በጥሞና ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፤
- ተማሪዎች እንዳይሰለቹ በማሰብ ምንባቡን ለማንበብ ከ10 -15 ደቂቃ ብቻ እንዲወስድ ታስቦ ቢዘጋጅም ተማሪዎች ደጋግመው እንዲያነቡ ማድረግ ይጠበቅብዎታል፤
- "ዳቦ ቢልሱት ምን ዋጋ አለው፤ ቢገምጡት እንጂ" እንደሚባለው ተማሪዎች ምንባቡን ራሳቸው በራሳቸው እንዲያነቡትና የንባቡን መልዕክት እንዲገነዘቡ የሚያደርጉበት ጊዜ ነው።

ይህንን በአጽንኦት ለማሳሰብ የተገደድነው የተማሪዎች የንባብ ክሂል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣት አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ነው። የንባብ ክሂል ዝቅተኛ መሆን ደግሞ በሁሉም የትምህርት አይነቶች ውጤት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ጥናቶች ይጠቁማሉ። ስለሆነም ለተማሪዎችዎ ራስዎ ወይም በሞዴልነት ከክፍሉ ተማሪ መካከል አንዱን/አንዷን በመምረጥ የሚያነቡላቸው ወይም የሚያስነብቡላቸው ከሆነ ተማሪዎችዎ አዳመጡ እንጂ አላነበቡም፤ ይህ ደግሞ የተማሪዎችዎን የንባብ ክሂል ዝቅተኛ ሊያደርግ እንደሚችል ሊገነዘቡ ይገባል። ነገር ግን አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ሲያስተምሩም ሆነ ግጥም ሲኖር ትክክለኛ ቅላጼ ለማስተማር በሞዴልነት አልፎ አልፎ ራስዎ በጮክታ ንባብ ማንበብ ይችላሉ። በተጨማሪም ማዳመጥ ሲያስተምሩ ራስዎ ወይም በመረጡት ተማሪ ማስነበብ ይችላሉ።

በንባብ ጊዜ "የማያነቡ" ተማሪዎች ሊያጋጥምዎት ይችላሉ። ለምን እንደማያነቡ ችግሩን በመገንዘብ መፍትሄ መሻት ይጠበቅብዎታል። ችግሩ ፊደላትን በወጉ ለይተው ስላልመጡ ነው? ይህ ከሆነም ቀላል ነው፤ የተወሰነ ጊዜ ሰጥተው ፊደላትን እንዲለዩ ማድረግ ይችላሉ። የተማሪ መጽሐፍ አለመያዝ፣ የክፍሉ ሥነ ሥርዓት፣ የተለያዩ የንባብ እንቅፋቶች፣ ወዘተ ከሆኑም እንደየሁኔታው መፍትሄ መሻት ግድ ይላል።

### በድኅረ ንባብ ጊዜ

- በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ያልገባቸውን ነገር የሚጠይቁበት ጊዜ ነው፤

- እርስዎ ተማሪዎችዎ ምን ያህል እንዳነበቡና እንዳላነበቡ የሚገነዘቡበት ጊዜ ነው፤
- የተለያዩ የማስተዋል (አንብቦ የመረዳት) ጥያቄዎችን የሚያሠሩበት ጊዜ ነው፤
- የተማሪዎችዎ የንባብ ክሂል ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚገነዘቡበት ጊዜ ነው፤
- የጥያቄና መልስ፣ የውይይት፣ መልመጃዎች የመሥራትና የማረም፣ ወዘተ ጊዜ በመሆኑ ሰፋ ያለ ጊዜ የሚወስድ ነው፤
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በዚህ ጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ሌላ ቀጣይ መልመጃ ለመሸጋገር የሚሰናዱበት ጊዜ ነው።

ከዚህ በላይ የተገለጹት አጠቃላይ መመሪያዎች በመሆናቸው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያሉትን የምንባብ ይዘቶች ለማሠራት ሊጠቅሙ ይችላሉ።

የምንባቡ ርእስና የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የሰፈረ ሲሆን፣ እርስዎ ስለ አውራምባ ማህበረሰብ የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎቹን ያነቃቁ። ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ ረጋ ብለው እንዲያነቡ ያድርጉ። የምንባቡን አራት አንቀጾች ካነበቡ በኋላ ንባባቸውን ገታ በማድረግ ከአራቱ አንቀጾች የተረዱትን ሐሳብ እንዲገልጹ ያድርጓቸው። ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ በዚሁ ክፍል በድህረ ንባብ የቀረቡትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሠረት እንዲመልሱ ያድርጉ።

## ክፍለ ትምህርት አራት: ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የግልና የስራ ደብዳቤ ይጽፋሉ።
- የግለሰቦችን የህይወት ታሪክ ይጽፋሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የግልና የሥራ ደብዳቤ።
- የሰዎች የሕይወት ታሪክ።

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ክፍለ ትምህርት አራት በደብዳቤ አጻጻፍና በሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ላይ ያተኩራል። በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ማስታወሻዎች መነሻ በማድረግ ስለ ደብዳቤ አይነቶችና የአጻጻፍ ስልት፣ እንዲሁም ስለ ሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ጠቀሜታና አስፈላጊነት መሠረታዊ የአቀራረብ ስልቶችን ይግለጹላቸው። በመቀጠል በዚሁ ክፍል ከተራ ቁጥር ፩-፬ የቀረቡትን ተግባራት እንዲከውኑ ያድርጓቸው። በሚጽፉበት ወቅትም ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው።

## ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- የቃላትን ቀጥተኛ ፍቺ ይሰጣሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- የቃላት ቀጥተኛና አውዳዊ ፍች::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ክፍለ ትምህርት አምስት በማዳመጥና በንባብ ክፍሎች ከቀረቡት ጽሑፎች የወጡ የቃላት ፍችዎችን ለማስተማር ተዘጋጅቷል:: እርስዎም በመመሪያው መሠረት ተማሪዎች የቃላቱን ቀጥተኛ አውዳዊ ፍችዎች እንዲሰጡ ያግዟቸው::

## ክፍለ ትምህርት ስድስት: ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ምእላዶችን ይነጣጥላሉ::
- ምእላዶችን ያቀናጃሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ምእላድ መነጣጠል::
- ምእላድ ማቀናጀት::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል ስድስት ሰዋስው በሚለው ክፍል ስር ቃላትን ወደ ምእላዶች ስለመነጣጠልና ምእላዶችን ወደ ቃላት ስለማቀናጀት በምሳሌው መሠረት ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉና በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሠሯቸው ያድርጉ::

### መርጃ መሣሪያዎች

- ጋዜጦች፣
- መጽሔቶች፣
- ናሙና የሕይወት ታሪኮች፣
- ናሙና የማመልከቻ ደብዳቤዎች፣
- የሽያጭ ውል ናሙናዎች፡ ወዘተ.

### ግምገማ

- የአዳመጡትን ጽሑፍ መረዳታቸውን የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡
- በውይይት ንቁ ሆነው መሳተፋቸውንና ሚና ለዋጭ ንግግር ማድረጋቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፡፡
- ከአዳመጡትና ከአነበቡት ማስታወሻ መያዝ መቻላቸውን ደብተሮቻቸውን በማየት ማረጋገጥ፡፡
- በውይይትና በክርክር መሳተፋቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፡፡
- የግልና የሥራ ደብዳቤ መጻፍ መቻለቸውን የጻፏቸውን ምንባቦች በመፈተሽ ማረጋገጥ፡፡
- ለቃላት ቀጥተኛና አውዳዊ ፍች መስጠታቸውን ከደብተሮቻቸው በመመልከት ማረጋገጥ፡፡
- ቃላትን በምእላድ መሸንሸን መቻላቸውንና የተለያዩ ምእላዶችን በማቀናጀት ባለብዙ ምእላድ ቃላት መፍጠር መቻላቸውን ከደብተሮቻቸው በመመልከት ማረጋገጥ፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

፩. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. ሀሰት
7. እውነት
8. ሀሰት

### ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

፩. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. እውነት
2. እውነት
3. ሀሰት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. ሀሰት

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ለ 2. ሀ 3. ሠ 4. መ 5. ሐ

### ክፍል ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ቀጥሎ “ሰነፍ ይከስራል፤ ሠራተኛ ይከብራል” በሚል ርእስ እንድታደምጡት ከተደረገው ምንባብና “አውራምባ” በሚል ርእስ ከቀረበው ጽሁፍ የተወሰዱ ቃላት ተዘርዝረዋል፡፡ ለእነዚህ ቃላት መልስ የሚሆኑት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የውርስ መሬት
2. አያስፈልገኝም
3. ሠራተኞች
4. ሥራ መፍታት
5. እንደማትከለክላቸው
6. የሚጠቅም
7. የማይታይ
8. የእርሻ ቦታ
9. የሕፃንነት
10. ሳያሸንፋቸው

#### የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

መምህር/ት፣ ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ለመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት: የህይወት ክህሎቶች (8 ክፍለ ጊዜ )

## ርዕስ: "ቴክኖሎጂዎች"

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፦

- በመቅረጸ ድምጽ የተቀረጸ የሕይወት ታሪክ አዳምጠው ጥቅልና ዝርዝር መረጃዎችን ይሰጣሉ::
- በሚያደምጡት ምንባብ ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ::
- ማህበራዊ ተራክቦን ተጠቅመው ንግግር ያደርጋሉ::
- የምንባቡን ይዘት ያብራራሉ::
- አመዛዛኝ አንቀጾችን ይጽፋሉ::
- የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍቺ ያብራራሉ::
- የአማርኛ የቃል ክፍሎችን ይለያሉ::

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

### የህይወት ታሪክ

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- አዳምጠው ዝርዝር መረጃዎችን ይይዛሉ::
- በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት የሚቀርቡ ታሪኮችን አዳምጠው የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ያካፍላሉ::
- የማዳመጥ ቴክኒኮችን ይተገብራሉ::

**የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች**

- የማዳመጥ ብልሃቶች ::
- አዳምጦ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት::

**የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ**

ውድ መምህር/ት፣

የማዳመጥ ክንውኑን ከማድረግዎ በፊት ቀጥሎ በቀረበውን ማስታወሻ ላይ ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው::

## ውጤታማ የማዳመጥ ብቃቶች

1. ለማዳመጥ መወሰን

ማዳመጥ ምርጫ ነው:: ስለዚህ ማውራት ለማቆም እና ማዳመጥ ለመጀመር መወሰን አስፈላጊ የመጀመሪያ እርምጃ ነው::

2. የራስን የግል አጀንዳ መተው

አንድን ሰው በእውነት ለመስማት የራስን አጀንዳና ጭፍን ጥላቻ መተው ያስፈልጋል:: ሁሉንም የሚረብሹ ነገሮችና ማንኛውንም ቅድመ-ግንዛቤዎች በማፅዳት ትኩረትን መሰብሰብ አስፈላጊ ነው:: ይህም በሙሉ ትኩረት ለመከታተልና የተለያዩ ዕይታዎች በአዕምሮ ውስጥ ቦታ እንዲፈጥሩ ያግዛል::

3. የማወቅ ጉጉት መኖር

ውጤታማ ማዳመጥ ሌሎች ሰዎች ዓለምን እንዴት እንደሚያዩ ለማወቅ ጉጉት መኖርን ይጠይቃል:: በተቻለ መጠን ለመረዳት መሞከር፣ ክፍት ጥያቄዎችን መጠየቅና ሌሎች ሰዎች ነገሮችን በሚያዩበት መንገድ ለማየት መሞከር ተገቢ ነው::

4. በዓይኖቻችን ተናጋሪውን መመልከት አለማቆም

ንግግሩ የሚከናወነው ፊት ለፊት ከሆነ ከተናጋሪው ጋር የዓይን ግንኙነትን መጠበቅና ለሁሉም የእይታ ፍንጮች ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው:: ሰዎች የአድማጮችን ትኩረት ያደንቃሉ::ይህ ሲሆን ተናጋሪዎች ከአድማጮች ጋር ለመግባባት የበለጠ ችሎታ ይኖራቸዋልም:: ስለዚህ በዐይኖቻችን ተናጋሪውን የምንከታተል ከሆነ በሂደት ምልክቶቹን ለማንበብና የሚነገረውን ትርጉም ለመረዳት የበለጠ ችሎታ ይኖረናል::

5. ሙሉውን መልእክት ማዳመጥ

መልስ ከመስጠት በፊት ሙሉውን መልእክት መስማትንና መረዳትን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በማዳመጥ ሂደት የተዘወተረ መጥፎ ልማድ ለመስማት የሚፈልጉትን ብቻ መስማትና ከዚያ ተናጋሪው ንግግሩን ሲያቆም ወዲያውኑ የምትሰጡትን ምላሽ ማመላለስ ነው:: (ወይም ደግሞ ይባሱኑ፣ ሊነግረን የፈለገውን በመገመት መከታተል ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ ንግግሩን ማቋረጥ በጣም መጥፎ ልምድ ነው::)

6. ታጋሽ መሆን

አንዳንድ ሰዎች ትክክለኛ ቃላትን ለማግኘት፣ አንድ ነጥብ ለማውጣት ወይም አንድን ጉዳይ ለማብራራት ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳሉ:: እንዲያስቡና መልእክታቸውን እንዲያጠናቅቁ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል:: ካልጨረሱ አሁንም መጠበቅ ግድ ይላል::

7. በአክብሮት ማዳመጥ

ልዩ ሀሳብ የማቅረብ መብትን ማክበር በተለይ በሚያዳምጡበት ጊዜ በጣም አስፈላጊና ቁልፍ ጽንሰ ሀሳብ ነው:: በሚገለፁት አስተያየቶች፣ ወይም ጥቅም ላይ በሚውለው የተግባቦት ስልት ውስጥ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: አንደበታዊ ተግባቦት በማይደረግበት ጊዜ እንኳን፣ ኢአንደበታዊ ምልክቶች ስለአድማጮች ይናገራሉ:: ለመፍረድ ሳይሆን ለመስማት ማዳመጥ ያስፈልጋል::

8. የርህራሄ ስሜት መኖር

ሰዎች የግል ወይም የሚያስቃይ ነገር ሲናገሩ ርኅራሄ ሊኖር ይገባል:: ይህ በጣም አስፈላጊ ነው:: ርህራሄ ለአንድ ሰው ከማዘንና ከማሰብ የዘለለ ነው:: ርህራሄ በመጀመሪያ የሌሎችን ስሜት መረዳትንና መሰማትን ይጠይቃል:: ከዚያ ለመልእክቱ እውቅና ሰጥተን አዲስ ግንዛቤያችንን ማጋራት እንችላለን::

9. የራስን ስሜቶች እና ምላሾች ማስተዳደር

ሌሎች የሚናገሩት በውስጣችን ስሜታዊ ምላሽ የሚፈጥሩ ከሆነ፣ የንግግራቸውን ዓላማና የቃሎቻቸውን ሙሉ ትርጉም ለማዳመጥ በትኩረት መከታተል ያስፈልጋል:: ሌሎች እንዲያዝዙን መፍቀድ የለብንም:: ስሜትንና ራስን መቆጣጠር መዘንጋት የለበትም:: በጣም በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንደሆንን በሚሰማን ጊዜ እንኳን መረጋጋታችንን መጠበቅ ኃይለኛ ችሎታ ነው:: ይህ በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ውስጥ ግቦቻችንን ለማሳካት ይረዳናል::

10. የመረዳት ፈተና

ግንዛቤያችንን ለመፈተሽ የሰማነውን በየጊዜው ማጠቃለል ያስፈልጋል:: እንዲሁም፣ ግንዛቤያችንን ግልጽ ለማድረግ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ የሚነገረውን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የሚያስችል ሀሳብ እንስላለን::

እባክዎ ለተማሪዎች የሚያዳምጡትን ጽሑፍ ርእስና የክፍለ ትምህርቱን ዓላማዎች ያስተዋውቋቸው:: በመቀጠልም ከላይ በቀረበው ማስታዎሻ መሰረት ስለ ውጤታማ የማዳመጥ ቴክኒኮች ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው::

ለቅድመ ማዳመጥ ተግባራት የተወሰነ ደቂቃ ይውሰዱና ማዳመጥን ለማስተማር የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ያዘጋጁ፤ (የሚጠቀሚቸው ቴፕ፣ ኮምፒዩተር፣ ሞባይል እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች የሚሠሩ መሆናቸውን እርግጠኛ ይሁኑ፤ ምንም ዓይነት ቴክኖሎጂ ማግኘት የማይቻል ከሆነ በሞባይልዎት ቀርጸው ማስተማር ይችላሉ):: በመቀጠል ተማሪዎች በትረካ መልክ የተቀረጸውን የሕይወት ታሪክ ለማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጉ:: የተማሪዎች ሙሉ ሀሳባቸው ሊያዳምጡት በተዘጋጀው ታሪክ ላይ እንዲሆን ያድርጉ:: ከዚያም የተቀረጸውን ታሪክ አንዴ ለሁሉም ተማሪዎች በሚሰማ የድምጽ መጠን

ያጫውቱና  አጠቃላይ ጥያቄዎች ያስከትሉ (ስንት ተናጋሪዎች ናቸው? ስለ ምን እያወሩ ነው?)። ይህ ተማሪዎች ከተናገሪዎች ድምጽ ጋር እንዲተዋወቁና በሕይወት ታሪኩ ውስጥ የሚጠቀሱት የተለያዩ መረጃዎች የት አካባቢ እንዳሉ እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። ከዚያም ወደ ሁለተኛው ዙር ማጫወት ከመሄድዎ በፊት የተወሰኑ ደቂቃዎች ይውሰዱና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ወይም ተግባራት ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ጥያቄዎችን በትክክል መገንዘባቸውንና ተማሪዎች የተቀረጸውን ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ በሙሉ ትኩረታቸው እንደሚያደምጡት ያረጋግጡ። ቀጥለው ለሁለተኛ ጊዜ ታሪኩን ያስደምጧቸው።

ከዚያም የተወሰኑ ደቂቃዎችን በመስጠት ተማሪዎች ለቀረቡት ጥያቄዎች ወይም ተግባራት መልሶቻቸውን እንዲያዘጋጁ ያድርጉ። ቀጥሎ ለመጨረሻ ጊዜ ታሪኩን እንዲያደምጡ ያድርጉ። ጥቂት ደቂቃዎችን በመስጠት ያላሟሏቸውን መረጃዎች እንዲያሟሉ ያድርጉ። ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ወይም ተግባራት በትዕዛዛቸው መሰረት ያሠሩዋቸው። ያሉበት ሁኔታ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ማስተማር የማይችሉበት አከባቢ ከሆነ የሀዲስ አለማየሁ ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ ስለቀረበልዎት ራስዎ ድምጽዎን ከፍ አድርገው በማንበብ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ይከውኑ። ቴክኖሎጂ መጠቀሙ ተማሪዎችን ስለሚያነቃቃ በመምህሩ መመሪያ ከዚህ በታች የቀረበውን የአዲስ አለማየሁ ታሪክ እቤትዎ ወይም እቢሮዎ ተረጋግተው እያነበቡ በሞባይልዎ ይቅረጹና እክፍል ውስጥ ሞባይልዎትን ከፍተው ያስደምጡዋቸው።

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

የሕይወት ታሪኩን ከማዳመጣችሁ በፊት ሀዲስ አለማየሁ ማን ናቸው? ስለእሳቸው ታሪክና ሥራዎቻቸው የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ በቃል ንገሯቸው።

### የክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ ህይወት ታሪክ

ክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ ከህዝብ ልብ ውስጥ ያኖራቸው "ፍቅር እስከ መቃብር" ቢሆንም የበርካታ ስራዎች ባለቤት ናቸው፤ ለበርካታ አስርት ዓመታትም ሀገራቸውን በመምህርነት፣ በዲፕሎማትነት፣ በሚኒስትርነት እንዲሁም በአርበኝነት በትጋት አገልግለዋል።

ጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረ ማርቆስ አውራጃ ጎዛምን በተባለች መንደር ከእናታቸው ወ/ሮ ደስታ አለሙና ከአባታቸው አቶ አለማየሁ ሰለሞን ኃይሉ ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ.ም ተወለዱ። የአንደኛና ሁለተኛ ክፍል ትምህርታቸውን አዲስ አበባ በስዊድን ካቶሊክ ሚሽነሪዎች በሚተዳደር ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን እስከ ስድስተኛ ክፍል ደግሞ በተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ገብተው ተምረዋል። ይሁን እንጂ በትምህርት ቤቱ በተነሳ የተማሪዎች አመጽ ምክንያት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደው ነበር። ከዚህ በኋላ በዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ይሰጥ የነበረውን የመምህርነት ስልጠና ወስደው በ1923 ዓ.ም ቀድሞ ይማሩበት በነበረው የስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት  በመምህርነት ተቀጥረው  እስከ 1924 ዓ.ም አገልግለዋል።

ሀዲስ አለማየሁ ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ የሀገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር መጀመሪያ በራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ጦር በኋላም በራስ እምሩ በሚመራው የአርበኞች ቡድን ተቀላቅለው የፋሽስትን ጦር በቆራጥነት ተፋልመዋል፡፡ ሀዲስ አለማየሁ ከነጻነት በኋላ አዲስ በተመሠረተው የኃይለ ሥላሴ መንግስት ስልጣን ተሰጥቷቸው እስከ1938 ዓ.ም ድረስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፕሮፖጋንዳ ክፍል ኃላፊነትና በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቆንስላ ተጠሪ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ቀጥሎም በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተዛውረው በወቅቱ አምባሳደር የነበሩት የራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ጸሐፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ሀዲስ አለማየሁ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በይበልጥ የሚታወቁት በደራሲነታቸው ነው፡፡ በሥነ ጽሑፍ ዘርፍ በነበራቸው ተሳትፎ " ተረት ተረት የመሠረት"፣ "ወንጀለኛው ዳኛ"፣ "የልምዣት"፣ "ፍቅር እስከ መቃብር" እና ሌሎችም ልቦለዶችን ጽፈዋል፡፡

ሀዲስ አለማየሁ ጥሩ የተውኔት ጸሐፊም ናቸው፡፡ በ1928 ዓ.ም ገደማ ለመድረክ የበቃው "የአበሻና የወደኋላ ጋብቻ" ቀዳሚ ተውኔታቸው ነው፡፡ ከዮፍታሔ ንጉሴና ከበጅሮንድ ሰብስብ ጋር በመሆን በጋራ የጻፉት "የሆድ አምላኩ ቅጣት" ሌላኛው የሀዲስ አለማየሁ የጥበብ ትሩፋት ነው፡፡

ሀዲስ አለማየሁ በሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ለነበራቸው የላቀ ሚና በርካታ ሽልማቶችን ተቀዳጅተዋል፡፡ ለመጥቀስ ያህል፡- በ1960ዓ.ም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት የወርቅ ሽልማት ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ በ1996 ዓ.ም ደግሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጽሑፍ የክብር ዶክትሬት ሸልሟቸዋል፡፡

አምባሳደር፣ ሚኒስትር፣ መምህር፣ ደራሲና ጸሐፌ ተውኔት ሀዲስ አለማየሁ ህዳር 27 ቀን 1996ዓ.ም በ94 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ግብዓተ-መሬታቸውም አድናቂዎቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

(ሀብታሙ ግርማ፡፡ 2011፡፡ ከገጽ 194-204 ለማስተማሪያ እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ)

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ለመጀመሪያ ጊዜ ስታዳምጡ ከተናጋሪዎች ድምጽ ጋር በመላመድ ሀዲስ አለማየሁን አስመልክቶ የሚነሱ የተለያዩ መረጃዎች በተቀረጸው ድምጽ የት አካባቢ እንዳሉ ለዩ፡፡ በተጨማሪም የጽሑፉን ጥቅል ሀሳብ ተረዱ፡፡
2. መምህሩ ለሁለተኛ ጊዜ የተቀረጸውን ድምጽ ሲያጫውቱ ዝርዝር መረጃዎችን በማስታሻ ደብተሮቻችሁ በማስፈር ለጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ጣሩ ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ማህበራዊ ተራክቦን መሠረት ያደረገ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- አንደበታዊ ተግባቦት ያደርጋሉ

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- በማህበራዊ ተራክቦ ውስጥ ንግግር ማድረግ
- የቃል ንግግር

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ክፍለ ትምህርት ሁለት ንግግር በሚለው ክፍል ማህበራዊ ተራክቦን መሠረት ያደረገ ንግግር ለማስተማር ቀርቧል፡፡ በመሆኑም፣ ተማሪዎችን አምስት አምስት አድርገው በቡድን በማደራጀት "ወደ ሆስፒታል መሄድ" በሚል ርእስ የቀረበውን ማህበራዊ ተራክቦ እንዲከውኑ ያድርጉ፡፡ በዚሁ ክፍል በተራ ቁጥር ፪ የቀረበውን ተግባር ለማከናወን በአካባቢያቸው ባሉ መገናኛ ብዙሃን የሚቀርቡ ድራማዎችን አዳምጠው እንዲመጡና በድራማዎች አማካኝነት የተላለፉ መልእክቶችን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡ ቀጥሎ በተራ ቁጥር ፫ ስር የቀረበውን ተግባር በትእዛዙ መሠረት እንዲከውኑ ያድርጉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

### ቴክኖሎጂ

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች ይገልጻሉ፡፡
- የምንባቡን ዝርዝር ማስረጃዎች ይመረምራሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- ባዮ ቴክኖሎጂ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና ሰው-ሰራሽ አእምሮ፡፡

## የክፍለ ትምህርቱ ለቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ክፍል ሦስት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ቀርቧል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት የምንባቡን ርዕስ ተማሪዎች ከመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ እንዲናገሩ ያድርጓቸው። ተማሪዎችን በየተራ በማስነሳት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። በመቀጠልም ተማሪዎቹ ምንባቡን በዝምታ እንዲያነቡ ያድርጉ። ከምንባቡ ውስጥ የሚከብዷቸውን ቃላት እንዲያወጡና እንዲመዘግቡ ያድርጉ። የእነዚህን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ፈልገው እንዲያመጡ በመንገር በዚህ ምዕራፍ ክፍል አምስት ላይ እንደሚያቀርቧቸው ይንገሯቸው። በመጨረሻም በዚሁ ክፍል ተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ስር የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሠሩ ያድርጓቸው።

## ክፍለ ትምህርት አራት: ጽሕፈት

### በክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- አመዛዛኝ አንቀጾችን ይጽፋሉ።
- አመዛዛኝ ድርሰቶችን ይጽፋሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ትዊተርና ፌስቡክ፣ ስልክና በይነ መረብ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጾች።
- በኢሜል መልዕክትን መላክና በፖስታ መልዕክትን መላክ፣ ቴሌ ብርና ሞባይል ባንክ በተሰኙት አገልግሎቶች በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ አመዛዛኝ ድርሰቶች።

## የክፍለ ትምህርቱ ለቀራረብ

በክፍለ ትምህርት አራት ጽሕፈት በሚለው ስር ስለቀረቡት ቴክኖሎጂ ነክ ርዕሰ ጉዳዮች አስመልክቶ ለሚከወኑት ተግባራት መረጃዎችን በበይነ መረብ አማካኝነት ከተለያዩ ድረ ገጾችና ሰነዶች እንዲያሰባስቡ ያድርጉ። በመቀጠል የሰበሰቧቸውን መረጃዎች በማደራጀት አመዛዛኝ አንቀጾችና ድርሰቶች እንዲጽፉ ያድርጉ። ምናልባትም የአቀራረቡን ቅቡልነት ለማጎልበት ይረዳ ዘንድ በአከባቢው የሚያገኙትን ባለሙያዎች በመጋበዝ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ዕድል ቢያመቻቹ የማስተማር ዘዴዎችን የተለያየ በማድረግ የተማሪዎቹን የመማር ተነሳሽነት ለመቀስቀስ ይጠቅማልና ይህን ዓይነቱን ዕድል መጠቀሙን እንዳይረሱ።

## ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- በቴክኖሎጂ ዘርፍ ያሉ የሙያ ቃላትን ፍች ይለያሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- የመረጃ ቴክኖሎጂ ቃላት ፍች::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት አምስት ቃላት በሚለው ርዕስ በተራ ቁጥር ፩ ስር “ቴክኖሎጂ” ከሚለው ምንባብ የወጡ ቃላት ቀርበዋል:: በተጨማሪም በተራ ቁጥር ፪ የመረጃ ቴክኖሎጂ ቃላት ቀርበዋል:: በሁለቱም ተራ ቁጥሮች የቀረቡትን ቃላት ፍችያቸውን ከተለያዩ ድረ-ገጾች በማፈላለግ እንዲያመጡ፣ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡና ፍችያቸውን የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች እንዲሠሩባቸው ያድርጉ::

## ክፍለ ትምህርት ስድስት: ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የአማርኛ የቃል ክፍሎችን ይዘረዝራሉ::
- የአማርኛ ቃላትን የቃላት ክፍል መግለጽ ይችላሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ግስ
- ስም
- መስተዋድድ
- ተውሳከ ግስ
- ቅጽል
- መስተአምር

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል ስድስት ሰዋስው በሚለው ርዕስ የአማርኛ ቃል ክፍሎችን አስመልክቶ ማስታወሻ አለ:: ማስታወሻው ስድስቱንም የቃላት ክፍሎች ከምሳሌ ጋር የሚያሳይ ነው:: ተማሪዎቹ ማስታወሻውን በደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ያድርጉ:: እርስዎ ደግሞ ቀድመው በቂ ዝግጅት በማድረግ በዚሁ ርዕስ ላይ ማብራሪያ ይስጧቸው:: በመቀጠልም የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሠሩ ያድርጉ::

### መርጃ መሣሪያዎች

- አነስተኛ ሞንታርቦ
- ቴፕ ወይም ኮምፒዩተር
- ሲዲ
- ፍላሽ ዲስክ
- በቴክኖሎጂ ዙሪያ የተጻፉ የተለያዩ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች
- ፖስተሮች

### ግምገማ

- የማዳመጥ ቴክኒኮችን በተግባር ላይ ማዋላቸውን ማረጋገጥ
- በቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚቀርብ ትረካን አዳምጠው ዝርዝር መረጃዎችን በማስታወሻ መልክ መያዝ መቻላቸውን ማየት
- ማህበራዊ ተራክቦን ተጠቅመው ንግግር ማድረጋቸውን መከታተል
- ቴክኖሎጂ ነክ የሆነ ንባብ አንብበው መረዳታቸውን በሚቀርቡት ጥያቄዎች አማካኝነት ማረጋገጥ
- በቴክኖሎጂ ነክ ርእሰ ጉዳዮች ላይ አመዛዛኝ አንቀጾችን እና ድርሰቶችን መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍቺ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ፍቻቸውን ፈልገው ማግኘት መቻላቸውን ማየት
- የአማርኛን የቃላት ክፍሎች መለየታቸውን ማረጋገጥ

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

**ክፍለ ትምህርት ስድስት: ሰዋሰው**

**፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት የቃል ክፍሎቻቸውን ለዩ።**

2. ግስ
3. ስም
4. ስም
5. ቅጽል
6. ቅጽል
7. ተውሳከ ግስ
8. ግስ
9. መስተአምር
10. መስተዋድድ

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከአነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. መ
5. ሠ
6. ሀ

## የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

ውድ መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። ስመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው።

# ምዕራፍ ሦስት፡ ሱስና አደንዛዥ ዕፅ ( 7 ክፍለ ጊዜ )

## ርእስ፡ ሱስና አደንዛዥ ዕፅ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- በሚያዳምጡት ጽሑፍ መሠረት ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ::
- የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም በቅድመ ማዳመጥ ወቅት ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ::
- ማህበራዊ መስተጋብርን መሠረት ያደረገ ንግግር ያደርጋሉ::
- በሚና-ተኮር ልምምድ ይሳተፋሉ::
- ተጨማሪ ጽሑፎችን ያነባሉ::
- በሚሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ድርሰት ይጽፋሉ::
- ለሚቀርቡላቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ::
- የሐረግና የዓረፍተ ነገር መዋቅሮችን ለይተው ያሳያሉ::

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

#### የአደገኛ እጾች መዘዝ

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ስለ አደንዛዥ ዕጽና ሱስ ስለሚያስይዙ መድሀኒቶች ጉዳት ጥቅልና ዝርዝር መረጃዎችን በማስታወሻዎቻቸው ይይዛሉ::
- በዝርዝር መረጃዎች ላይ ማብራሪያ ይሰጣሉ::
- አዳምጠው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ::

**የክፍለ ትምህርቱ ይዘት**

- ስለ አደንዛዥ ዕጽና ሱስ ስለሚያስይዙ መድሀኒቶችና አስከፊ ገጽታዎች ማዳመጥ::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት ሆይ፣

ማዳመጥን ለማስተማር የመጀመሪያው ክፍል "የአደንዛዥ ዕጾች መዘዝ" በሚል ርዕስ ቀርቧል:: በመጀመሪያ የክፍለ ጊዜውን ርዕስና ዓለማዎች በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ለተማሪዎች ያስተዋውቋቸው:: በተማሪው መጽሐፍ ከቀረበው ስዕል ውጪ በአደንዛዥ ዕጽ የተጠቁ ሰዎችን ምስል ፈልገው በማምጣት ለተማሪዎች ያሳዩዋቸውና የሚሰማቸውን ሀሳብ እንዲገልጹ ያድርጉ:: ተማሪዎች ትኩረታቸውን እንዲሰበስቡና ለማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጉ:: በመቀጠል ተማሪዎች በተማሪው መጽሐፍ ላይ በቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ በቃል ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ያድርጉ::

ለተማሪዎች "የአደንዛዥ ዕጾች መዘዝ" የሚል ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ በመንገር በሚያደምጡበት ጊዜ ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ:: ከዚያም ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማ በሚችል ድምጽና ሁሉንም ተማሪዎች ባማከለ ፍጥነት ከታች የቀረበውን ምንባብ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እስከሚለው ድረስ ያንብቡላቸው:: እንደተማሪዎችዎ የቋንቋ ዳራ የሚደመጠውን ይዘት ለሁለት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ሦስት ጊዜ ደጋግመው ሊያስደምጧቸው ይችላሉ:: ነገር ግን የሚደመጠውን ይዘት ከማስደመጥዎ በፊት የማዳመጥ ጥያቄዎችን ያንብቡላቸው:: ከዚያ በማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎቹን በመመለስ የማዳመጥ ክሂላቸውን ያዳብራሉ::

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከርዕሱ ተነስታችሁ ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ጽሑፍ ይዘት ገምቱ::
2. አደገኛ እጾችን የሚጠቀሙ ሰዎች ምን ምን እጾችን የሚጠቀሙ ይመስላችኋል? ከቀደመ እውቀታችሁ ተነስታችሁ የአደገኛ እጾች የሚያስከትሏቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ::

### የአደገኛ እፆች መዘዝ

አደገኛ ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችንና ዕጾችን መጠቀም እየተስፋፋ መምጣት ለሰው ልጅ አሳዛኝ ክስተት ነው:: አደገኛ ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችና ዕጾች ዝውውርና ከጥቅም ላይ መዋል በአንድ አካባቢ ያሉ የጥቂት ሰዎች ብቻ ችግር አይደለም:: ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን እና ዕጽን የሚጠቀም ሰው የማይበጅ ሥራ እንዲሰራ የሚገደድ፣ ሱስ ለሚያስይዝ መድኃኒት ተገዥ የሚሆንና በመጨረሻ ከማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴ የሚገታ ይሆናል:: ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን የመጠቀም ችግር በቤት ውስጥ፣ በሥራ ቦታና በትምህርት ቤት ውስጥ በመዝለቅ በማንኛውም የእድሜ ክልልና የትምህርት ደረጃ ያሉ ሰዎችን ችግር ላይ እየጣለ ይገኛል:: ይህ ሁኔታ እየዋለ እያደረ ከሥራ የተገለሉና ለቤተሰብ ብሎም ለሀገር ሸክም የሆኑ ዜጎች እየተበራከቱ እንዲሄዱ እንደሚያደርግ ግልጽ ነው::

በተጨማሪም ሰዎች ሱስ በሚያስይዝ መድኃኒትና ዕጾች ሱስና ጥገኝነት ምክንያት ከመጎዳታቸው ባሻገር የሰው ልጆች ባህላዊ እሴቶች፣ የአኗኗር መንገዶችና ብሔራዊ ሀብቶች ይጠፋሉ:: ችግሩ በማንኛውም ቦታ ባሉ ማሕበረሰቦች ላይ መራራ ጭንቀትንና ተስፋ መቁረጥን እየፈጠረ በመሄድ ላይ ይገኛል:: አደገኛ

ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችንና ዕጾችን መጠቀም በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በቤተሰብና በማሕበረሰብ ላይ የተለያዩ ችግሮችን በመፍጠር ላይ ይገኛል።

ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን የሚጠቀም ሰው በቤት ውስጥ ካለ ቤተሰቡን በማወክና ሥርዓት በማፋለስ ማንኛውንም የቤተሰብ አባል ያሰቃያል። ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት ሱሰኞችና ጥገኞች ሌሎችን የቤተሰብ አባላት ፍላጎትና ሁኔታ በመርሳት ሁልጊዜ የሚያስቡትና የሚያልሙት የለመዱትን ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት ወይም ዕጽ ስለመውሰድ ብቻ በመሆኑ ድርጊቱ የቤተሰብ መፍረስን ያስከትላል።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ያማዳመጥችሁት ምንባብ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?
2. ቀጥሎ የሚቀርበው ቅንጫቢ ጽሑፍ ምን ምን ጉዳዮችን የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ሱስ በሚያስይዙ መድኃኒቶችና በዕፁ ተጠቃሚዎች አማካኝነት ሊከሰቱ ከሚችሉ የቤት ውስጥ የወንጀለኛነት ባህሪ ጎን ለጎን ራሳቸውም ለተለያዩ አካላዊና ስነ- ልቦናዊ ስቃዮች ይዳረጋሉ። ቤተሰቦችም የቤተሰባቸውን የቀስ በቀስ ጉስቁልናና ከጥቅም ውጪ መሆን በማየት ጥልቅ ሀዘን ውስጥ ይገባሉ። ማንም ሰው የቤተሰቡ አባል ሲጎዳ ማየት ሰላሙን ይነሳዋል።

ተማሪዎች ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትንና ዕጽን የሚጠቀሙ ከሆነ የመማር ችሎታቸው ይቀንሳል። ጠቅላላ የትምህርት ክትትላቸው ይዳከማል። ለዚህ ምክንያቱ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን እና ዕፅን በመውሰድ ልምዳቸው የተነሳ ከትምህርት ቤት አዘውትረው ስለሚቀሩ ነው። በተጨማሪም በትምህርት ቤት ውስጥ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት/ዕፅ ተጠቃሚዎች መኖር ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት በማይጠቀሙ ተማሪዎች ላይ ያለው ጫና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ከዚህ ልምድ ጋር በተያያዘ ሌብነት፣ ዘረፋ፣ ልቅ ወሲብ፣ ሁከት፣ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን እና ዕፅን ማዘዋወርና መጠቀም በትምህርት ቤት ውስጥ ይስፋፋሉ።

ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን አላግባብ በመጠቀም ምክንያት ሕብረተሰብ ከሰው ኃይልና ከኢኮኖሚ አንጻር የሚደርስበት ኪሳራ ቀላል አይደለም። ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን አላግባብ የሚጠቀሙ የብዙ ሰዎች እድሜ ከ18-35 ዓመት በመሆኑ የችግሩ ሰለባዎች የአፍላ ጉልበት ባለቤቶች ናቸው። በመሆኑም ሂደቱን ለመግታት የሚደረጉ ሕጋዊ እንቅስቃሴዎች ሱስ ከሚያስይዝ መድኃኒት እና ዕጽ ተጠቃሚዎችና አዘዋዋሪዎች ዛቻንና የኃይል እርምጃዎችን ሲያስከትሉ ይስተዋላሉ።

በሥራ ቦታ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች ባሻገር የምርት መቀነስና የሥራ ላይ አደጋዎች የተለመዱ ናቸው። በአንድ በኢንዱስትሪ በበለጸገ ሀገር የተደረገ ጥናት ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት ተጠቃሚዎች ከማይጠቀሙት ጋር ሲነጻጸሩ ምርታማነታቸው በሦስት እጅ የቀነሰ መሆኑን፣ ከሦስት እጥፍ በላይ የሥራ ላይ አደጋ መንስኤዎች መሆናቸውንና ከሁለት እጥፍ

በላይ ከሥራ ገበታቸው እንደሚቀሩ አረጋግጧል። ሱስ ለሚያስይዝ መድኃኒትና ዕጽ ተጠቃሚዎች ለጤና እንክብካቤ የሚወጣው ወጪ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን ከማይጠቀሙት ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም የላቀ ነው። በአጠቃላይ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት ወይም ዕፅ ተጠቃሚዎች ጥራቱና መጠኑ የቀነሰ ምርት እንዲመረት ምክንያት መሆናቸውም ተረጋግጧል።

አደገኛ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒትን መጠቀም በኅብረተሰቡ ውስጥ ከተስፋፋ መንግስታት ወንጀልን ለመከላከል ይሳናቸዋል። ምንም እንኳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች አደገኛ ሱስ የሚያስይዝ መድኃኒት አቅርቦትና ዝውውር (ንግድ) የተገታ ቢመስልም አደንዛዥ ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶች እና ዕፅች የሚያስከትሉት ችግር ስፋት ሕግን ከማስከበርና ከጤና አንጻር ከቁጥጥር ውጭ በመሆን ለሀገሮች ፀጥታና ትብብር የሥጋት ጫናን ፈጥሯል።

(ከጌታቸው ገበየሁ። 2010። ከገጽ 76-78 የተወሰደ)

ንባቡን ካነበቡላቸው በኋላ ተማሪዎች በድህረ ማዳመጥ ስር የቀረቡ ተግባራትን በትእዛዛቱ መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ።

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በማህበራዊ አውድ መሠረት ሱስ ስለሚያስይዙ ነገሮች ንግግር ያደርጋሉ።
- ሱሶች  በሚያስከትሏቸው ችግሮች ላይ ይወያያሉ።
- የሱስ አስያዥ ነገሮችን አስመልክቶ ክርክር ያቀርባሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ሱስ አስያዥ ነገሮችን አስመልክቶ የሚሰሙና የሚነገሩ  ሐሳቦች።
- ሚና ነጠቃ ንግግር።
- በተዘጋጁ ርእስ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ንግግር።

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት ሁለት ንግግር በሚለው ክፍል በተራ ቁጥር ፩ ስር የቀረቡትን ተግባራት ለማከናወን አመቺ ነው በሚሉት መንገድ ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ይመድቧቸው። በመቀጠል የተወሰኑትን "በአካባቢያቸው ያሉ የአልኮል ሱሰኛ ግለሰቦች በሰፈር ውስጥ ወይም በቤታቸው ውስጥ ስለሚያሳዩዋቸው ባህሪያት ከአዩዋቸው ወይም ከሰሙት በመነሳት ንግግር እንዲያቀርቡ፣ ከፊሎቹን ደግሞ በአካባቢያቸው የሚገኙ ጫት ቤቶች፣ ሺሻ ቤቶች፣ አልኮል ቤቶች፣ ወዘተ በማህበረሰቡ ላይ የሚያደርሱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች መነሻ በማድረግ ንግግር እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው። በክፍሉ ውስጥ እየተዘዋወሩ ንግግራቸውን ይከታተሉ፤ ይደግፏቸውም።

በተራ ቁጥር ፪ ስር የቀረበው ተግባር "የቡና ሱስ እንደ አደገኛ ዕጽ ሊቆጠር ይችላል ወይም አይችልም" በሚል ርዕስ ክርክር እንዲያደርጉ የሚጠይቅ መልመጃ ሲሆን ተማሪዎችን አመቺ በሆነ ሁኔታ በቡድን ቡድን ይክፈሏቸውና በዚሁ ክፍል በቀረበው መመሪያ መሠረት ክርክር እንዲያካሄዱ ያድርጉ::

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

# ሱስና ማገገሚያ መንገዶች

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በጥልቅና ሰፊ የንባብ ስልቶች "ሱስና ማገገሚያ መንገዶቹ" በሚል ርዕስ በመጽሀፋቸው የቀረበውን ምንባብና ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ::
- ከምንባቡ ዝርዝር መረጃዎችን በመውሰድ ያብራራሉ::
- የጽሑፉን ድምጸት ይለያሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የተለያዩ ምንባቦች ::
- የምንባቡ ዝርዝር መረጃዎች::
- የጽሑፉ ድምጸትና ጭብጥ ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት ሦስት ንባብ በሚለው ክፍል "ሱስና ማገገሚያ መንገዶች" በሚል ርዕስ ቀርቧል:: የክፍለ ጊዜውን ትምህርት ርዕስ በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ያስተዋውቋቸው:: በዚህ ክፍል የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎችን ያነቃቁ:: ተማሪዎቹ ሁለቱን አንቀጽ ካነበቡ በኋላ ንባባቸውን ቆም አድርገው ከላይ ካነበቧቸው ሁለት አንቀጾች ያገኙትን ሀሳብ በቅድመ ንባብ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከሰጡት መልስ ጋር ምን ያህል እንደሚስማማ ሀሳባቸውን በቃል እንዲገልጹ ዕድል ይስጧቸው:: በመቀጠልም ከቀሪው ምንባብ ክፍል ምን እንደሚጠብቁ ሀሳባቸውን በቃል ያካፍሉ ዘንድ ዕድል ይስጧቸው:: ከዚያም የጀመሩትን ንባብ እንዲጨርሱ ያድርጉ::

ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ድህረ ንባብ ተግባራትን በትዕዛዙ መሠረት ያሠሩ:: ምንባቡን መሠረት አድርገው የወጡ "እውነት" ወይም "ሐሰት" ጥያቄዎች በእርስዎ መሪነት ሁሉንም ተማሪዎች በማሳተፍ ያሠሯቸው:: እንደሎተሪ ስለሚቆጠሩ የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት መለካት አያስችሉም:: ስለዚህ ተማሪዎቹ ባነበቡት መሠረት ጥያቄዎቹን እውነት ወይም ሐሰት ብለው ከመለሱ በኋላ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልገው መልሳቸውን እንዲያረጋግጡ ይርዷቸው:: ሁሉም ተማሪዎች በዚህ አግባብ ሲሳተፉ ትምህርቱ አጥጋቢና ተግባር-ተኮር ትምህርት ይሆናል::

በማስከተልም በተራ ቁጥር “፪” የተገለጹትን የምርጫ ጥያቄዎች ያሠሯቸው:: ይህንን መልመጃ የክፍል ሥራ በመስጠት ካሰሯቸው በኋላ ወደ ሚቀጥለው ሥራ ያሸጋግሯቸው:: በመመሪያው መሠረት በክፍል ሥራ መልክ ለየግል ካሠሯቸው በኋላ እንደ አቀማመጣቸው ቡድን መሥርተው በብጤ እርማት መልክ በመልሶቻቸው ላይ እየተወያዩ እንዲያርሙ ያድርጉ:: እርማት ስንል ግለ-እርማት፣ የብጤ እርማት፣ የቡድን እርማት፣ የመምህሩ እርማት፣ ወዘተ በማቀያየር እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀምና ተማሪ-ተኮር ትምህርት ማድረግ ይቻላል::

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- በሚሰጧቸው ርእሰ ጉዳዮች ላይ ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- በሚሰጧቸው ርእሰ ጉዳዮች ላይ  ድርሰት መጻፍ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህር አራት ጽሕፈት በሚለው ክፍል በቁጥር ፩  እና ፪  ተማሪዎች ድርሰት እንዲጽፉ የሚያደርጉ ተግባራት ቀርበዋል:: ተማሪዎች ወደ ድርሰት መጻፍ ከመግባታቸው በፊት ስለድርሰት አጻጻፍ በቀረበው ማስታወሻ ላይ ገለጻ ያድርጉላቸው:: በተጨማሪም ተማሪዎቹ እየተቀባበሉ የሚያነቡት ማሳያ ድርሰት አዘጋጅተው ይስጧቸው:: በመቀጠልም በተሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ድርሰቶችን እንዲጽፉ ያግዟቸው፤ ድርሰቶቻቸውን በመመልከትም ግብረ መልስ ይስጧቸው::

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ለቃላት አገባባቸውን መሠረት ያደረገ ፍች ይሰጣሉ::
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ይሰጣሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት::
- የቃላት ተመሳሳይ ፍች መፈለግ::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት አምስት ቃላት በሚለው ክፍል አገባባዊ ፍች ቃላት በሚገኙበት አውድ የሚኖራቸው ፍች መሆኑን ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው:: በመቀጠልም ተማሪዎች በቁጥር ፩ ስር የተሠመረባቸውን ቃላት አገባባዊ ፍች እንዲያወጡ ያድርጉ:: በቁጥር ፪ ደግሞ የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች (ተመሳሳይ ፍች) እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ያግዟቸውም::

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- ሰዋስዋዊ የአረፍተነገር ህጎችን ይለያሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- የአረፍተ ነገር መዋቅር መመስረት::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት ስድስት ሰዋስው በሚለው ክፍል አንድ አረፍተ ነገር ሊጠብቃቸው ስለሚገቡ ሰዋስዋዊ ሕጎች ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው:: የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የቀረቡትን ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው አረፍተ ነገሮች እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው፤ እንዲከውኑ ያግዟቸውም:: የሰሩትንም በመመልከት ግብረ መልስ ይስጧቸው::

### መርጃ መሣሪያዎች

- ፖስተሮች
- ጋዜጦች
- መጽሔቶች
- ጥናታዊ ጽሑፎች
- ሰዋስዋዊ መጻሕፍት

### ግምገማ

- የአዳመጡትን ምንባብ መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ
- በንግግር ተግባራት መሳተፋቸውን አቀራረባቸውን በክፍል ውስጥ መመልከትና ማረጋገጥ
- በንባብ ክፍል የቀረበውን አህድ አንብበው መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ
- ጽሑፉን አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን የጻፉትን እርማት ማድረግና ማረጋገጥ
- ድርሰት መጻፋቸውን ማስተወሻ ደብተሮቻቸውን መመልከትና ማረጋገጥ
- የቃላት አገባባዊ ፍችና ተመሳሳይ ፍች በትክክል ማውጣት እንደቻሉ መልመጃዎችን በማረም ማረጋገጥ
- ሰዋስዋዊ ህጎችን ማስተካከል መቻለቻውን በመመሪያው መሠረት መልመጃዎችን በማረም ማረጋገጥ

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነውን "እውነት"፣ ስህተት የሆነውን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. እውነት 2. ሀሰት 3. ሀሰት 4. እውነት

፪. በምንባቡ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን አማራጭ ምረጡ፡፡

1. ሀ 2. ለ 3.መ 4. ሐ 5. መ

ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፩. ቀጥሎ በቀረቡት አሀዶች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በሚገኙበት አውድ መሠረት ያላቸውን አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡

1. መያዝ (ያ ትጠብቃለች)
2. የከተታቸውን
3. ነጻነት
4. መኖር
5. ያለዕቅድ የሚከናወን

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

፩. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተት ይታይባቸዋል፤ ስለዚህ አስተካክላችሁ ጻፏቸው፡፡

1. ጎበዝ ተማሪዎች እንፈልጋለን፡፡
2. ተማሪዎች በጣም ጎበዝ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
3. ልቦለድ የፈጠራ ጽሑፍ ነው፡፡
4. ሦስቱ ልጆች ወንድምና እህት ናቸው፡፡
5. አንተ አባትህን ታከብራለህ?
6. አሁን መጽሐፍ ማንበብ ያስደስተኛል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር**

መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ለመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት: ልቦለድ ( 8 ክፍለ ጊዜ )

## ርእስ፡ ልቦለድ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፦

- የሚቀርቡ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በማዳመጥ ይወያያሉ::
- በልቦለድ ጽሑፎች ዓላማ ላይ ውይይት ያካሂዳሉ::
- የቀረቡ ቅንጫቢ ጽሑፎችን ጭብጥ ተንትነው ይጽፋሉ::
- መምህራቸው የሚጠቁሟቸውን መጽሐፎች በማንበብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ::
- ልቦለዶችን ያነባሉ::
- ሰፊና ጥልቅ የንባብ ብልሃቶችን በመተግበር መረጃዎችን ይፈልጋሉ::
- በልቦለድ ውስጥ የቃላትን አጠቃቀም በመጻፍ ያሳያሉ::
- የልቦለድን ጭብጥና ዋና ዋና ገጸባህሪያትን ይለያሉ::
- ያነበቡትን የልቦለድ ታሪክ ይተርካሉ::
- የራሳቸውን አጭር ጽሑፍ ያዘጋጃሉ::
- ሰዋስዋዊ ግድፈት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክለው ይጽፋሉ::

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

#### ሰዉመን

ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የሚያነቡላቸውን ምንባብ በማዳመጥ ማስታወሻ ይይዛሉ::
- የሚነበቡ ሥነጽሑፎችን በማዳመጥ ይወያያሉ::

#### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የተመረጡ ምንባቦችን ማዳመጥ፣ መግለጽ::
- በሚደመጡ ጽሑፎች ላይ መወያየት::

## የክፍል ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ማዳመጥን ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች የምእራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸው። በመቀጠል የክፍለ ትምህርቱን ዓላማ በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው። ከዚያም "ሰመመን" ከሚለው ረጅም ልቦለድ የተቀነጨበ ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ ይንገሯቸው። ማንበብ ከመጀመርዎ በፊት ግን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ጥቂት ተማሪዎች ከተናገሩ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች በጥሞና እንዲያደምጡና ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግዎን አይዘንጉ። አሁን ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ለሁሉም ተማሪዎች ሊሠማ በሚችል ድምጽ በዝግታ ያንብቡላቸው።

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ሰመመን የሚለውን ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ አንብባችሁታል?
2. መጽሐፉን ካነበባችሁት ከታሪኮቹ ውስጥ የመሰጣችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ንገሯቸው።

ጥቅምት 14 ቀን ፈጽሞ የማትረሳ በአቤል አዕምሮ የተቀረፀች ዕለት ናት። በዩንቨርሰቲው ውስጥ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የሚመዘገቡበት ዕለት ነበር። ተመዝጋቢዎቹ ለዩኒቨርሲቲው አዲስ በመሆናቸው በአዲስ ስሜት ፊታቸው በርቶ ምዝገባው በሚካሄድበት መስኮት በኩል ሥርዓት ባጣ ሁኔታ ተሠልፈዋል።

አቤል ለግል ጉዳዩ ምዝገባ ክፍል ደርሶ ሲመለስ ከተሠለፉት መሐል ከአንዲት ኮረዳ ጋር ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ። ሁለቱም በቅጽበት ዐይናቸውን ሰበሩ። አያውቃትም፤ አታውቀውም። ለጊዜው ለማያውቃት ልጅ መደንገጡ አላስገረመውም። ጥቂት ወደፊት ከተራመደ በኋላ አስልቶ ዘወር ብሎ ተመለከታት።

ጠይም ናት፤ ካውያ ያልነካው ጸጉሯ ከማጅራቷም ባያልፍ ለማበጠር የሚያስቸግር ዐይነት አይደለም። ቁመቷ አጭር ነው፤አለባበሷ እንደ ነገሩ ይመስላል፤ገና ሲያየት አጠገቧ ካሉት ልጃገረዶች ጋር በሆነ ጨዋታ ትሣሣቅ ነበር። ስትሥቅ ጉንጮቿ ሰርጉድ ይላሉ። በፈገግታ ጊዜ የሚሰረጉዱ ጉንጮች አቤል ከልጅነቱ ጀምሮ ይወዳል።

ያየት ዕለት፤ ያለ ምንም ሐሳብ ውሎ ማታ መኝታው ላይ አረፍ ሲል በሰመመን አጭር፣ጠይም ልጅ የሚሰረጉዱ ጉንጮቿን እያሳየች ልታጫውተው ከተፍ አለች። ያለምንም ማመንታት ተቀበላት። ቀን ያየውን ቁመናዋንና አለባበሷን በልቡ ደግሞ አደነቀላት። አንሶላውን ተኰናንቦ፤ዐይኑን ጨፍኖ ስትሥቅ በሰመመን ተመለከታት። "እየሣቀች የጉንጮቿን መሰርጐድ በማሳየት ብታስከፍል ዐይኑን የሚያሽ ያለ አይመስለኝም" ሲል በሐሳቡ ደመደመ። ልቡ ውስጥ ገብታ እንድትዝናና፤ እንድትጫወት፣ እንድትቦርቅ፣ እንድትተኛ እንድትነሳ፣እንደ ልቧ እንድትሆን ፈቀደላት።

ትዕግሥት ከዚያን ዕለት ጀምሮ በተፈቀደላት መሠረት ልቡ ውስጥ ገብታ፤እግሮቿን አኮራምታ ተቀመጠች፤ውላ ስታድር ተንፈራጣ ተቀመጠች። ስታሰልስ በጀርባዋ ጋደም አለች። ስትከርም ጭራሹን ሐሳብዋን ጠቅልላ ተኛች።

መጀመሪያ በአቤል ልብ ውሰጥ ትምህርቱና ትዕግሥቱ ጸብ ሲፈጥሩ፣ አቤል ዳኛ ሆኖ፣ ዕረፋና ተቀመጡ፤ለሁለታችሁም ይበቃል" አላቸው። ጠባቸው እየከረረ መጥቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ፤አቤል በትምህርቱ ፈረደና ትዕግሥትን አነገሣት…

"… ያን ዕለት ነው__ነገር የጠፋው!" አለ አቤል በልቡ ደጋግሞ፤በሐሳብ ወደ ኋላ ብዙ ከተጓዘ በኋላ። አንዳች ነገር የገፈተረው ይመስል፤ተፈናጥሮ ከመኝታው ላይ ወረደ። ወዴት እንደሚሄድ ሳያስብ ነበር የተነሣው ጫማውን አደረገና ክፍሉን ለቅቆ ወጣ። ወዴትም ይሁን፤ሰው ወዳለበት-ትዕግሥትን ሊያይ ወደሚችልበት። የሚነዘንዝ ሕሊናውን ለማሸነፍ ትዕግሥትን ማየት አለበት። ከዚያ ዕለት ጀምሮ ብቸኝነቱን መሸሽ እሚችለው ትዕግሥት ላይ ዐይኑን በማሳረፍ ሆነ።

ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ ደረጃውን ሲወርድ እስክንድር ማንደፍሮን አገኘው። "ታዲያስ አቤል፤ወዴት ነው ምትሄደው?" "እስኪ መጻሕፍት ቤት ልድረስ ብዬ ነበር።" እሱን ሲያይ በቅጽበት የመጣለት ሐሳብ ነበር። በመቀጠልም፤"ያንን የጥናት ጽሑፍ መምህሩን ላለማስቀየም ብዬ እንደገና ልሠራው ሞከርኩ። ነገር ግን ገና ወረቀቱን ስገልጠው ያቅለሸልሸኛል አለው።

"በርታ፤እንደ ምንም መወጣት ነው"" አለ እስክንድር__ ለማበረታታት ያህል። "እሱማ የት ይቀራል!"አለ አቤል፤ የውስጥ ስሜቱን ለመግለጽ በሚሞክር የደከመ አነጋገር። "በል እንግዲህ" ብሎት እስክንድር ሽቅብ ደረጃውን ወጣ። አቤልም ቁልቁል እየወረደ የእስክንድርን አረማመድ ዘወር ብሎ ተመለከተ። ሁለት ሁለቱን ደረጃዎች ነበር__ በአንድ እርምጃ የሚወጣቸው።

አቤል በማያስደንቀው ነገር በመደነቅ ትክ ብሎ ተመለከተው። ከራሱ ጋር አወዳድሮት ነበር ያደነቀው። አቤል ከጥቂት ሳምታት ወዲህ የሥራ ፍላጎቱ ላልቶ፤የወጣትነት ስሜቱ በሆነ ነገር በርዶ፣ ሲራመድ እንኳ እንደ ጎታታ ሽማግሌ ቀስ ብሎ ነበር የሚሄደው፤የመሰላቸት ዐይነት፤በዚህ አረማመድ ወደ መጻሕፍት ቤት አመራ። ዋናው መጻሕፍት ቤት ለመድረስ አጭር መንገድ እያለለት በጀርባ በኩል ለመዞር በዙሪያ ጥምጥም መንገድ ሔደ። በዋርካው በኩል ለማለፍ ፈልጎ ነበር።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ካዳመጣችሁት ጽሑፍ ተነስታችሁ አቤል በምን የተቸገረ ይመስላችኋል? በቡድን ሆናችሁ ተነጋገሩ።
2. እናንተ አቤልን ብትሆኑ ችግራችሁን እንዴት ትፈቱታላችሁ? በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ።

ቀስ ብሎ የዋርካውን አካባቢ ማተረ፡፡ ትዕግስትና ማርታ እዚያ አልነበሩም፡፡ ዋርካውን ባየ ቁጥር አንድ ነገር ትዝ ይለዋል፡፡ አሁንም በእግሩ ወደ ፊት እየተራመደ በሐሳቡ ብዙ ዓመት ወደ ኋላው ተጓዘ...

ከጎንደር ከተማ ውስጥ ነዋሪዎቹ እንደ ጣኦት የሚያመልኩበት አንድ ግዙፍ ዋርካ ነበር፡፡ አቤል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበረበት ጊዜ ከመኖሪያ ቤቱ የሚመላለሰው በዋርካው በኩል ነበር፡፡ ማታ ከትምህርት ቤቱ ሲመለስ፤አብዛኛውን ጊዜ ሁለት ወጣት ፍቅረኞች በዋርካው አካባቢ ይመለከት ነበር፡፡ ሰዓት ጠብቀው ነው የሚገናኙት፡፡ ብዙውን ጊዜ ወንድየው ቀድሞ ስለሚመጣ እየተንጎራደደ ይጠብቃታል፡፡ መምጣቷን ገና ከሩቅ ሲመለከት ፤ፊቱ በርቶ ጥርሶቹ ብልጭ ይላሉ፡፡ እሷም አጠገቡ ስትደረስ የመቅለስለስ ፈገግታ ታሳየዋለች፡፡

ደብተሯን ይቀበላትና ከንፈሯን ይስማታል፡፡ ተቃቅፈው በቀስታ ርምጃ መራመድ ይቀጥላሉ፡፡አቤል ያኔ ገና ልጅ ቢሆንም፤ሁኔታቸው ስለሚያስደስተው፤ሥራዬ ብሎ በደስታ ይከታተላቸው ነበር፡፡ ከትምርት ቤት ሲወጣ እንደ መክሰስ የሚናፍቀው እነሱን ማየት ነበር፡፡ ምናልባት ዋርካው አካባቢ ቀድሞ ከደረሰ እንኳ እስኪመጡ ድረስ ተደብቆ ይጠብቃቸዋል፡፡ ቆዳው ምኝ ቢመስልም ውስጡ ብልጣ ብልጥ ስለ ነበር፤እነሱን ለማየት እንደሚከታተላቸው እንዳያውቁበት ይጠነቀቅ ነበር፡፡ በዝግታ በሚራመዱበት ጊዜም ራቅ ብሎ የሚከተላቸው፤ራሱን እንደ ተራ መንገደኛ ወይም በየመንገዱ እየተጫወተ እንደሚሄድ ልጅ አስመስሎ ነበር፡፡ እየቆየ ሲመጣ ግን፣ እነሱም ሳይነቁበት አልቀሩም፡፡ ሆኖም አቤል ብቻ ሳይሆን በፍቅራቸው ሁኔታ የሚደነቁ ብዙ ተመልካቾች እንዳሏቸው ስለሚገምቱ ደንታም አይሰጣቸውም ነበር፡፡ ወንድየው ያማሩ ልበሶች እየለበሰ በተወሰነው ሰዓት ከዋርካው አካባቢ ከመምጣቱ በቀር ምን ሥራ እንዳለው አይታወቅም፡፡ እሷ ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበረች፡፡

(ሲሳይ ንጉሱ፡፡ 1978፡፡ ገጽ18-21፣መጠነኛ ማሻሻል የተደረገበት፡፡ )

## ክፍለ ትምህርት ሁለት: ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ባዳመጡት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተንተርሰው ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- ያነበቧቸውን የልቦለድ ታሪኮች ይናገራሉ፡፡
- ባዳመጡት ጽሑፍ ውስጥ የተገለጹ ገጸባህሪያትን ታሪክ በንግግር ይገልጻሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ስለአነበቡት ምንባብ ይዘት ንግግር ማድረግ፡፡
- ስለ ስለአነበቡት ገጸባህሪያት ተግባር ንግግር ማድረግ፡፡

## የክፍል ትምህርት አቀራረብ

የንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ሶስት ደረጃዎች አሉት፤ እነሱም፡-

መግቢያ፡- ትምህርቱን በአውድ በማቅረብ የአእምሮ ዝግጅት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

ማለማመጃ፡- የቀረበውን አውዱ መሰረት አድርገው በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ሆነው በቋንቋው የሚለማመዱበት ሂደት ነው፤

ማፍለቂያ፡- በተለማመዱት መሰረት የራሳቸውን ቃላትና ሰዋስው በማፍለቅ ሀሳባቸውን የሚገልጹበት ደረጃ ነው።

የንግግር ትምህርት ማስተማሪያ ስልቶች

የወል ንበት (ድምፀትን፣ ጥብቀትን፣ የዘዬ ቃላትን መምህሩ ሞዴል ይሆንና ተማሪዎች በህብረት እንዲሉ በማድረግ)

ማጠያየቅ (መምህሩ በሚሰጣቸው ሞዴል መሰረት ተማሪዎቹ እርስ በርስ እንዲጠያየቁ በማድረግ) (መምህሩ ጠያቂ ተማሪው መላሽ፣ ተማሪው ጠያቂ መምህሩ መላሽ፣ ተማሪዎቹን እርስ በርሳቸው ማጠያየቅ)

አስተያየት መስጠት

የሁነት ክወና

ውይይት

ክርክር

## ክፍለ ትምህርት ሦስት: ንባብ

### ሽክም

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ሽክም ስለሚለው ልቦለድ አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ።
- በምንባቡ የቀረቡ መረጃዎችን ይተነትናሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የልቦለድ ምንባብ።
- ተጨማሪ ልቦለዶችን ማንበብ።

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

መጽሐፉ የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳትና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በሚያዳብር መልኩ የተደራጀ በመሆኑ፣ እርስዎ በክፍል ውስጥ መልመጃዎችን ሲያሰሩ ክሂሎችን በቅንጅት መሥራት በሚችሉበት መንገድ ቢሆን ይመረጣል:: መጀመሪያ ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲሠሩ ማድረግ፣ ከዚያም በቃል የተነጋገሩበትን ሐሳብ ወደ ጽሑፍ እንዲቀይሩ ማድረግና የጻፉትን ደግሞ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ በማድረግ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር ይቻላል::

ንባብን ለማስተማር በቅድሚያ የሚነሱ ሶስት ጥያቄዎች፣

- የማነበው ምንድን ነው?
- የማነበው ለምንድን ነው?
- የማነበው እንዴት ነው? የሚሉት ይገኙበታል::

ንባብ በዕድሜ ተወስኖ፣ በዕውቀት ተመጥኖ የሚተገበር ክሂል ነው:: ስለዚህ ተማሪዎች ማንበብ ያለባቸው በዕድሜያቸውና በዕውቀት ደረጃቸው መጠን ስለሆነ፣ የሚያነቡትን ሲመርጡ የንባብ ፍቅራቸውን የሚጨምር ይዘት ያለው እንዲሆን ያድርጉ:: ንባብን ለተማሪዎቹ የማስተማር ዋና ዓላማ ሶስት ነጥቦችን መሰረት ያደረገ ነው::

እነሱም፤

1. ለፊደል ወይም ለምልክት፦ መነጠልን፣ መለየትን፣ መቁጠርን ለማስቻል፤
2. ለአንደበት ማፍለቅ፦ ንበትን፣ የድምጽ አወጣጥን፣ መናገርን ለማስቻል፤
3. ለመገንዘብ፦ መረዳትን፣ ትርጉም መጨበጥን፣ ስሜት መከተልን ስለሚያዳብር ነው::

ውድ መምህር/ት፣

"በሌላ በኩል መምህራችሁ አንድ ልቦለድ መጽሓፍ መርጠው በንባብ ቤት ያስቀምጡላችኋል፤ እናንተም ለንባብ በተሰጣችሁ ጊዜ ውስጥ በመጠነ ሰፊ የንባብ ስልት አንብባችሁ ለክፍል ጥያቄ/ሙከራ ትዘጋጃላችሁ" ለሚለው ጥያቄ እንደሚከተለው ማስፈጸም ይችላሉ::

ይኸውም የንባብ ስልቶች/ዓይነቶች ስንል የገረፍ ገረፍ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብ ፣ የትንበያ ንባብ፣ የጥልቀት ንባብ፣ መጠነ ሰፊ ንባብ፣ ኂሳዊ ንባብ፣ ወዘተ ናቸው:: ተማሪዎቻችንን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ስናሰራ የተለያዩ የንባብ ዓይነቶች እንጠቀማለን:: ለምሳሌ ከአንድ ምንባብ ውሰጥ የአንድን ሰው የልደት ዘመን ጠያቂ ሐሳብ ሲኖር መልሱን ወዲያው በገረፍ ገረፍ ንባብ ስልት ማግኘት ይቻላል:: የሌሎች የንባብ ስልቶቸም እንዲሁ የየራሳቸው ጥቅም አላቸው::

መጠነ ሰፊ ንባብ ደግሞ በክፍል ውስጥ ለመተግበር ስለሚያስቸግር በመምህሩ/ርቷ ክትትል መተግበር ይቻላል:: በመጀመሪያ አንድ አጭር ልቦለድ መጽሐፍ መርጠው በንባብ ቤት ውስጥ ያስቀምጡ:: ከዚያ ተማሪዎችዎ በመጠነ ሰፊ ንባብ ስልት በቤት ሥራ መልክ እንዲያነቡ ይዘዙዋቸው:: የሚሰጣቸው ጊዜ እንደ ተማሪዎች የቋንቋ ዳራና የተመረጠው ልቦለድ መጽሐፍ ተዳራሽነት ለሁለት ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል:: የተሰጣቸው ጊዜ ሲያበቃ በልቦለዱ ይዘት የተመሠረቱ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ፈተና አዘጋጅተው ከ10 ወይም ከ15 የሚታሰብ ይፈትኑዋቸው:: ውጤቱ እንደ ወርኃዊ ወይም መንፈቃዊ ፈተና ዋጋ ይኑረው፤ ያነበበ ተማሪ ውጤት ያገኛል ያለናበበ ደግሞ የተቀራኒው ይሆናል፤ ጥሩ ቁጥጥር ነውና:: ስለዚህ በዚህ የማስተማር ዘዴ መጠነ ሰፊ ንባብ መተግበርና ተማሪዎቻችን የማንበብ ፍቅር እንዲያድርባቸው ማገዝ እንችላለን ማለት ነው::

### ክፍለ ትምህርት አራት: ድርሰት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- አጫጭር ጽሑፍችን ይጽፋሉ::
- አንቀጾችን አደራጅተው ድርሰት ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- አጫጭር ጽሑፎችን መጻፍ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት!

መፃፍን፣ የምንለማመደው በመፃፍ ነው:: ልቦለድ ለመፃፍ ልምምድ ከማድረጋችን በፊት ግን ስለልቦወለድ ምንነት የተወሰኑ ነጥቦች ማንሳት ይገባናል:: ዘሪሁን ስኩላችን ጠቅሰው /1996፤153/ "ልቦለድ በመባል የሚታወቀው የሥነጽሑፍ ዘርፍ አያሌ ገፅታዎች አሉት:: አይነቶቹም ብዙ ናቸው:: ይህ የሥነጽሑፍ ዘርፍ በእርግጥ ዘመናዊና በዝርው የሚቀርብ የፈጠራ ድርሰት ነው::" ይላሉ:: አማረ (1976 ) ደግሞ እንዲህ ይዘግቡታል:- "ልቦለድ ድርሰት የሚባለው ደግሞ አንድ ደራሲ ከአዕምሮው አንቅቶ፣ ከልቡ አመንጭቶ የሚያቀርበው ድርሰት ነው:: እንዲህ ሲባል ልቦለድ ድርሰት ከሀቅ የራቀ ነው ማለት አይደለም::"

ልቦለዱ፣ ገፀ ባህሪያት የእውኑ አለም ሰዎችን ባህሪ ተላብሰው የመኖሪያ ስፍራና ጊዜ ተበጅቶላቸው ሲንቀሳቀሱና ድርጊት ሲፈጽሙ የሚያዩበት ደራሲው በራሱ ምናብ በፈጠረላቸው ታሪክ ውስጥ የሚኖሩበት ዓለም ነው:: ልቦወለድ ከሚያስተናግዳቸው ይዘትና ቅርፅ አንጻር ለሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል- አጭርና ረጅም ልቦለድ:: አጭር ልቦለድ በነጠላ ታሪክ፣ በጥቂት ገፀ ባህሪያት፣ በጠባብ መቼትና በአንድ የትረካ አንጻር መሰረትነት ስለአንድ የሕይወት ገጽ የሚቀርብበት የፈጠራ ጽሑፍ ነው:: በአንጻሩ በረጅም ልቦለድ ውስጥ ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች የሚታዩበት፣ ብዙ ገጸ ባህሪያት፣ ሰፊ መቼት፣ አብይና ንዑስ ታሪክ የሚቀርብበት፣ ከሁለት በላይ ግጭቶች ሊከሰቱ የሚችሉበትና ሌሎች አላባውያንም

በስፋት የሚታዩበት የልቦወለድ ክፍል ነው:: የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ወይም የልቦለድ አላባውያን በአንድ ልቦለድ ውስጥ ተሰናስነውና ተቀናጅተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለእያንዳንዳቸው ሰፊ ገለጻ ለማግኘት ዘሪሁን አስፋው የሥነጽሑፍ መሰረታውያን የሚለውን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል፡፡

ስለዚህ እርስዎ ስለ ልቦለድ አጻጻፍ ጥቂት ማስታወሻ ለተማሪዎች እንዲያጽፏቸው ይመከራል፡፡ ከተቻለም በቤት ሥራ መልክ አጭር የልቦለድ ድርሰት እንዲጽፉ ቢያደርጉ ትምህርቱ የበለጠ በተማሪዎች እንዲሰርጽ ይረዳል፡፡

**ውድ መምህር!** ከታች በቀረቡት የልቦለድ አለባውያን ላይ አጭር ማብራሪያ ለተማሪዎች ቢሰጧቸው፦

ልቦለድ ለመፃፍ ስንነሳ ልናተኩርባቸው የሚገቡ ፍሬ ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም፡-

1. ታሪክ
2. ገፀ ባህሪያት
3. መቼት
4. የትረካ አንፃር
5. ግጭት
6. ትልም
7. ጭብጥ

**መፃፍን ማስተማር**

አንድን ጽሑፍ በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ለማለማመድ የሚያስችሉ ብልሃቶችን ራይምስ (1983) እንደሚከተለው ይጠቅሳሉ፡፡

**መገልበጥ፤**

- ግጥምጥምነትን መመርመር፤
- የሥርዓተ ነጥብና የሰዋስው አጠቃቀምን መፈተሽ፤
- የአረፍተ ነገር አደራደርን መፈተሽ፤
- ማጠቃለል፤
- ማሟላት፤
- መገመት፤
- መመለስ፤ የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን ብልሃቶች በመጠቀም ተማሪዎችን ጽሕፈት ያለማምዷቸው፡፡ ከነዚህ የማለማመጃ መንገዶች መካከል ለዚህ የክፍል ደረጃ የሚያገለግሉ አሉ፡፡ ለእርስዎ ጠቅላላ ዕውቀትና ለተማሪዎቹ በምርጫ ማስተማር እንዲችሉ ሰፊውን ነገር ለማሳየት ተብሎ የተገለጹ ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ መጠቀም ያለብዎት ግጥምጥምነትን መመርመር፣ የአረፍተ ነገር አደራደርን መፈተሽ፣ ማጠቃለልን፣ ማሟላትን መገምገምንና መመለስን ነው፡፡ እርስዎ ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርዕስና የተጻፉና ለክፍሉ በሚመጥን መልኩ የተደራጁ ጽሑፎችን በመስጠት ማጻፍና የተጻፈውን እንዲገመግሙ በማድረግ ጽሕፈትን ማስተማር ይችላሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- ቃላትን በትክክለኛ ቦታቸው ይጠቀማሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- የቃላት ትክክለኛ አጠቃቀም።

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል አምስት ቃላት በሚለው ክፍል አገባባዊ ፍች ቃላት በሚገኙበት አውድ የሚኖራቸው ፍች መሆኑን ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠልም ተማሪዎች በቁጥር ፩ ስር የተዘረዘሩትን ቃላት አገባበዊ ፍች እንዲያወጡ ያድርጉ። በቁጥር ፪ ለቀረቡት ፈሊጣዊ/ጥምር ቃላትም አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ያግዟቸውም።

## ክፍለ ትምህርት ስድስት: ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- የተሟላ/ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር ይጽፋሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር መጻፍ።

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል ስድስት ሰዋስው በሚለው ክፍል አንድ አረፍተ ነገር ሊጠብቃቸው ስለሚገባ ሰዋስዋዊ ሕጎችን ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው። የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የቀረቡትን ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው አረፍተ ነገሮች እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው፤ እንዲሰሩም ያግዟቸው። የሰሩትንም በመመልከት ግብረ መልስ ይስጧቸው።

### መርጃ መሣሪያዎች

በየትኛውም ምዕራፍ አስፈላጊ የሚባሉ መርጃ መሳሪያዎችን መምህራን አዘጋጅተው መጠቀም እንደሚገባቸው እንደሚያውቁ እንገምታለን። እንደዚሁም ራሳቸው ከማዘጋጀት በተጨማሪ ከታች የተዘረዘሩትን መጠቀም እንደሚችሉ እንጠቁማለን።

- አጭርና ረዥም ልቦወለዶች

- ግጥሞች
- መጣጥፎች
- ጥናታዊ ጽሑፎች

### ግምገማ

- የአዳመጡትን አህድ መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ::
- በንግግር ተግባራት መሳተፋቸውን አቀራረባቸውን በክፍል ውስጥ መመልከትና ማረጋገጥ::
- በንባብ ክፍል የቀረበውን አህድ አንብበው መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ::
- ጽሑፉን አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን የጻፉትን እርማት ማድረግና ማረጋገጥ::
- አጭር ድርሰት መጻፋቸውን ማስታወሻ ደብተሮቻቸው መመልከትና ማረጋገጥ::
- የቃላትን ትክክለኛ አጠቃቀም መተግበራቸውን መልመጃዎችን በማሰራትና በማረም ማረጋገጥ::
- ሰዋስዋዊ ሕጎችን ተከትለው አረፍተ ነገር መስራታቸውን መልመጃዎችን በማረም ማረጋገጥ::

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍል ትምህርት አራት: ጽሕፈት

መምህር/ት! የአንደኛው ጥያቄ አንቀጹን ሰማሚሳት ቢቸገሩ የአወዳዳሪ ድርሰት አጻጻፍን መርህ ተከትለው መስራታቸውን ለማረጋገጥ ከመጽሐፉ የተወሰደውና የሚሞላው መልስ ይህ ነው::

መልስ

ትምህርት ቤት፣ ትምህርት የሚሰጡትንና ትምህርት የሚፈልጉትን አንድ ላይ አገናኝታ ተማሪዎች የሚፈልጉትን ትምህርት በተወሰነ ጊዜ ባንድ ቦታ እንዲያገኙ ታደርጋለች (ሐዲስ ፣1975)

ክፍል አምስት: ቃላት

በትዕዛዝ ቁጥር ፩ እና ፪ ስር ለተዘረዘሩት ቃላት መልስ የሚሆኑ ተስማሚ ቃላትን ማግኘት የሚቻለው ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ስለሆኑ ትኩረት ሰጥተው እንዲያነቡና አውዳዊ ፍች እንዲፈልጉ ማድረግ ያስፈልጋል::

### የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ:: ለመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው::

# ምዕራፍ ስምንት፡ እንግዳ ተቀባይነት (8 ክፍለ ጊዜ )

## ርዕስ፡ እንግዳ ተቀባይነት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩትሁ በኂላ፦

- የማዳመጥ ስልቶችን ተከትለው ያዳምጣሉ::
- ጭብጥ ተኮር ንግግሮችንና የሰላምታ ልውውጦችን በማዳመጥ ይተነትናሉ::
- የግል ልምዳቸውን በማወዳደር ይጽፋሉ::
- የንግግርን ጠቀሜታ በንግግር ይገመግማሉ::
- የታሪኮችን ማጠቃለያ  ይጽፋሉ::
- የተሰጣችውን ጽሑፍ ካነበቡ በኂላ ጭምቅ ሀሳቡን ይናገራሉ::
- ቃላዊ ንግግር ያደርጋሉ::
- ስለእንግዳ ተቀባይነት የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን ያነባሉ::
- ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚያሳዩትን የቃል ክፍል ለውጥ ያሳያሉ::

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት

#### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- “ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት” በሚል ርእስ መምህሩ/ሯ የሚያነቡላቸውን ምንባብ በማዳመጥ ማስታወሻ ይይዛሉ
- የሚነበቡ ጽሑፎችን በማዳመጥ ይወያያሉ::

#### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የተመረጡ ምንባባትን ማዳመጥ፣ መግለጽ::
- በሚቀርቡ ጽሑፎች ላይ መወያየትና ማዳመጥ::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ማዳመጥን ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች የምዕራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸው:: የማዳመጥ ርዕሱን በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው:: ከዚያም "ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት" በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ ይንገሯቸው:: ማንበብ ከመጀመርዎ በፊት ግን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው:: ጥቂት ተማሪዎች ከተናገሩ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች በጥሞና እንዲያደምጡና ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግዎን አይዘንጉ:: አሁን ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ለሁሉም ተማሪዎች ሊሠማ በሚችል ድምጽ በዝግታ ያንብቡላቸው::

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. እቤታችሁ እንግዳ መጥቶ ያውቃል? ምን ምን ተደረገለት?
2. እናንተ ሌላ ሀገር በእንግድነት ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? በሄዳችሁበት ሀገር ምን አጋጠማችሁ?

‹‹ እንግዳ ሲመጣ አገው ምድር ሲደርስ

አዲናስ ይላሉ ቀልብን በሚሰርቁ በሚያማምር ፈረስ››

ኢትዮጵያዊነት ማፍቀር፣ ማክብር፣ ስለእውነት መኖር፣ ለአሸናፊነት መፈጠር፣ በፀጋ መክበር፣ ለሰውና ለነገ መኖር ነው:: ኢትዮጵያዊነት ሰውነት፣ እውነት፣ እኛነት፣ አርቆ አሳቢነት፣ ቀደምትነት፣ ጀግንነት፣ አዛኝነት፣ ደግነት እንግዳ ተቀባይነትና አስተዋይነት ነው::

የኢትዮጵያን የመከራ ቀንበር የሚሸከም፣ ጨለማን የሚያሻግር አገራዊ ስማችን ኢትዮጵያዊነት ነው:: በኢትዮጵያዊነት ውስጥ ከላይ የዘረዘርናቸው ማንነቶች ጎልተው ይታያሉ:: ኢትዮጵያዊነት አመፀኛን ያሸንፋል፣ መከራን ያሳልፋል፣ የተደፋን አንገት ያቃናል፣ ህብር ነው:: የተሠሩ አኩሪ ታሪኮች ሁሉ መነሻቸው ኢትዮጵያዊነት ነው::

አገዎች በቀያቸው ሰው በእንግድነት ሲሄድ ‹‹አዲናስ›› ወይም እንኳን ደህና መጣችሁ እያሉ ይቀበላሉ:: በእነሱ ምድር ብቻን መብላት፣ ሰውን መጥላት፣ ከአንዱ አንዱ ማዳላት አይታወቅም፤ ይህ መገለጫቸው ነው:: በአገው ምድር እንግዳ ተቀባይነት፣ ሰው ወዳድነት፣ የማይደበዝዝ የኢትዮጵያዊነት ሕይወት ነው:: በሰፊው እያረሱ፣ ሳያጎድሉ በበረከት እያፈሱ፣ ሳይሰስቱ እያጎረሱ፣ እያለበሱ፣ ሀገር ሲነካ ወገን ሲደፈርም አነጣጥረው እየተኮሱ በበረከት ምድር በበረከት የሚኖሩ ናቸው::

በዚች ምድር ከደጎች የወጡ ደግ ሰው አግኝተናል:: ብዙነህ ቦጋለ ይባላሉ ። ነዋሪነታቸው እንጅባራ ከተማ ነው:: የተሰማሩበት ሙያ ንግድ ነው:: እኒህ ሰው ከምንም በላይ ኢትዮጵያዊነት ይቅደም የሚሉ ናቸው:: የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የመማር ማስተማር ሥራ ሲጀምር በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ ተማሪዎችንና ኢትዮጵያዊነትን ይመለከታሉ:: አስቀድመው ኢትዮጵያዊነትን የሚወዱት ብዙነህ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ሲያይዋቸው የልባቸውን አገኙ:: አንድ አጋጣሚም የበርካታ ኢትዮጵያዊያን አባት እንዲሆኑ አደረጋቸው::

መምህር/ት፣

ማንበቡን እዚህ ላይ ገታ ያድርጉና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ተማሪዎች ውይይት እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ካዳመጣችሁት ጽሑፍ ምን እንደተገነዘባችሁ ተነጋገሩበት፡፡
2. ቀደም ባሉት አንቀጾች ከቀረቡት ሀሳቦች ጋር የሚመሳሰል ነገር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

ታሪኩም እንዲህ ይተርኩታል‹‹ በአንድ ወቅት በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ አመሻሽ ላይ ለሽርሽር ወጥቼ ነበር፤ ዕለቱም ዓመታዊ በዓል ነበር፣ ልጆች ሲጨናነቁ አየኋቸው፡፡ ምን ሆናችሁ ነው? ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ ከዚያም እንጅባራ እኮ ጥሩ ሀገር ነው፤ ሕዝቡ እንግዳ ተቀባይ ነው፣ እንዳትፈሩ ትምህርታችሁን ጠንክራችሁ ተማሩ አልኳቸው፤ ተግባባን፤ ቤቴ እንድትመጡ አልኳቸው፣ ወደቤቴ መጡ፣ አስተናገድኳቸው፣ ከዚያ በኋላ አባትና ልጅ ሆን፣ ሊጠይቁኝ ይመጣሉ፤ በቃ አብረን ከረምን›› ብለዋል፡፡

‹‹ልጆቹ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመጡ መሆናቸውን ነግረውኛል፣ በአንደኛ ዓመት የጀመረው ወዳጅነት እስከ ምርቃት ጊዜ ዘልቋል፡፡ ጊዜው ደርሶ ልጆቹ የምርቃት ዝግጅታቸውን በኢትዮጵያዊ አባታቸው ቤት ሊያከብሩ ሽርጉድ ላይ ናቸው፡፡ ግንኙነታችን የአባትና ልጅ ነው፣ ጓዳ የለም፣ መኝታ ቤት የለም፣ ቤቴ ቤታቸው ነው›› ይላሉ አቶ ብዙነህ፡፡

ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአካባቢው ባለ ዩኒቨርሲቲ ከሚመጡ ተማሪዎች አራት አምስት ልጅ ይዞ በዓል አብሮ ቢውል፣ ሁሉም ቤተሰብ ሆኖ ቢተጋገዝ መጥፎውን ሀሳብ በአጭሩ መቅጨት እንችላለን›› መልካምነትና አቃፊነት ካለ ግጭቶች አይኖሩም፡፡ መለመድ ያለበትም ነገር ይሄ ነው ብለዋል፡፡ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ማመን አለበት፣ ድሮም አባቶቻችን የምናውቀው ተባብረው፣ ተቀራርበው፣ ተጠራርተው ሲያበሉ ነው ፣ ሲያባርሩ ሲጋደሉ አላየንም፡፡

የአገው ምድር ህዝብ በእንግዳ ተቀባይነቱ የታወቀ፣ ብቻን መብላት የማይወድ ሕዝብ ነው፡፡ ስስት የለም፣ በሰፊው ደግሶ ነው የሚያበለው፡፡ በዚህም እሳቸውን አይተው ሌሎችም ተሞክሯቸውን እየወሰዱ መሆኑንም ነግረውኛል፡፡ ኢትዮጵያዊ አባትነታቸው ዘንድሮ በሚመረቁት ተማሪዎች ብቻ እንደማያበቃና ሌሎች ተተኪ ልጆችም እንዳሏቸው ነግረውኛል፡፡ ይሄም ይቀጥላል ነው ያሉት፡፡ ለሦስት ዓመት አባትና ልጅ ሆነው የዘለቁ በርካታ ተማሪዎችን እንደሚያስመርቁ ነው የነገሩኝ፡፡

(ታርቆ ክንዴ፡፡ 2014 ዓ.ም፡፡ አሚኮ)

ውድ መምህር/ት! ይህን ምንባብ ደግመው ካነበቡላቸው በኋላ በተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ ክትትልዎም አይለያቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለ ሀገር ፍቅር ውይይትና ክርክር ያደርጋሉ፡፡
- ስለሀገር ፍቅር ልምድ መለዋወጥ የሚያስችል ንግግር ያደርጋሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- እንግዳ ተቀባይነትን  በሚመለከት ውይይት ማካሄድ፡፡
- እንግዳ ተቀባይነትን በሚገልጽ ተግባር መሳተፍ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ንግግርን ማስተማር የሚቻለው በንግግር ነው፡፡ ስለዚህ ውድ መምህር/ት! ከዚህ በፊት በቀረቡት ምዕራፎች የተሰጡትን የንግግር ማስተማሪያ መንገዶች በመከተል ተማሪዎች ንግግር እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለእንግዳ ተቀባይነት ተጨማሪ ምንባብ ያካሂዳሉ፡፡
- ምንባቦችን በተለያየ ስልት ያነባሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- በእንግዳ ተቀባይነት ዙሪያ ሀሳብ በንባብ መሰብሰብ፡፡
- እንግዳ ተቀባይነትን የሚመለከቱ ተጨማሪ ጽሁፎችን ማንበብ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት! ለተማሪዎች ንባብን የምናስተምርበት ዋና ዋና ምክንያቶች፦

1. ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን የማግኘት ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፡፡
2. ለማዳመጥ፣ ለመናገርና ለመጻፍ ክሂሎች መሰረት ለመጣል፡፡
3. በራስ የመተማመን ችሎታን ለማዳበር ሲባል ነው፡፡

የንባብን መልመጃ በጽሑፍ ከተዘጋጁ ምንጮች በማንበብ የምንለማመድ ሲሆን፣ የማዳመጥን ደግሞ በንግግር የቀረቡትን ሃሳቦች በማዳመጥ ነው:: ሁለቱም ክሂሎች በትክክለኛው መንገድ ከተተገበሩ የሚከተሉትን ችሎታዎች ያስጨብጣሉ::

- የመገመት ችሎታን፤
- የተወሰኑ መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት፤
- አጠቃላይ ግንዛቤን ማግኘት መቻል፤
- ያልተለመዱ ቃላትን ፍች ከምንባቡ አውድ መረዳት መቻል፤
- የፅሁፍን አደረጃጀት መረዳት፤
- የደራሲውን ስሜት መረዳት፤
- ፍሬሃሳብን መረዳት፤
- የቀደመ እውቀትን ከአዲሱ እውቀት ጋር ማያያዝ መቻል፤
- አላስፈላጊና ዝርዝር ጉዳዮችን መተው፤
- በተዘዋዋሪ መንገድ የቀረበን መልዕክት መረዳት፤
- ዝርዝር መረጃን መረዳት፤
- መልዕክቱ የቀረበበትን ሁኔታ (አውድ) መረዳት፤

ስለዚህ በተማሪዎች መጽሐፍ የቀረበውን ምንባብ በለሆሳስና በጥሞና በግላቸው አንብበው ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ::

## ክፍለ ትምህርት ስራት: ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አጫጭር ጽሑፎችን ይጽፋሉ::
- ሁሉንም የጽህፈት ደረጃዎች በመጠቀም አንቀጾችን አደራጅተው ድርሰት ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ አጫጭር ጽሑፎችን መጻፍ::
- የጽህፈት ሂደትን ተከትሎ ድርሰት መጻፍ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

የጽሕፈት ትምህርትን ማስተማር የሚያስፈልገው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣ ለሌሎች ክሂሎች መዳበር መሰረት ለመጣል፣ በጽሑፍ አማካይነት ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመግባባት እንዲችሉና፣ በተለያዩ የስራ መስኮች ሲሰማሩ በደረጃቸው ከጽሕፈት ጋር ተያያዥነት ላለው ስራ ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ሲባል ነው::

ተማሪዎች የፅህፈት ትምህርትን ተምረው የሚያዳብሯቸው ችሎታዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የቋንቋውን ስርዓተ ፅህፈት አውቆ ባግባቡ መጠቀም መቻል፤
2. የማያስፈልጉ መረጃዎችንና አገላለፆችን ማስወገድ መቻል፤
3. የቋንቋውን ሥርዓተ-ነጥብ ባግባቡ መጠቀም መቻል፤
4. ሀሳብን አንባቢ እንዲረዳ አድርጎ በጽሑፍ መግለፅ፤
5. በአንድ ጽሑፍ የተለያዩ ክፍሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ማሳየት መቻል፤
6. በዲስኩር ውስጥ አመልካች ቃላትን ተጠቅሞ የተለያዩ ጉዳዮችን ማሳየት መቻል ናቸው፡፡

   (ትክክለኛ አመልካች ቃላት በመጠቀም ሀሳብን አያይዞና ፍሰቱን ጠብቆ አንባቢው በቀላሉ በሚረዳው ሁኔታ ማቅረብ)፡፡

ተማሪዎች ወደፍን እንዲለማመዱ የማድረግ ዋና ዓላማዎች፦

- የቋንቋውን  የጽሕፈት ሥርዓት አውቀው በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማስቻል፤
- የሚፈለጉና የማይፈለጉ መረጃዎችን መርጠው እንዲጠቀሙ ለማስቻል፤
- የቋንቋውን ሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም እንዲረዱ ለማድረግ፤
- ጽሑፍን አንባቢው በሚረዳው መልክ ማደራጀት እንዲችሉ ለማድረግ፤
- መልዕክትን በተገቢው መንገድ ለማስተላለፍ እንዲችሉ ለማበረታታት፡፡

በአጠቃላይ ጽሕፈትን በሁለት የማስተማሪያ ዘዴ ማስተማር ይቻላል፡፡ እነሱም ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር ናቸው፡፡ ሂደት ተኮር የሚባለው የማስተማሪያ ዘዴ መጻፍን ለማስተማር ሥራ ላይ በሚውሉ ሞዴሎች አማካኝነት ጽሕፈትን ማስተማር ሲሆን፣ ሂደቱም ከቀላሉ በመጀመር ወደ ከባዱ የጽሕፈት ሥራ የሚዘልቅ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የማስተማሪያ ስልት ለተማሪዎቹ የሚመች ስለሆነ በሂደት ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

ውድ መምህር/ት፣

ተማሪዎቹ ከላይ ለተመለከተው ችሎታ እንዲበቁ በተከታታይና ያለመሰልቸት ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡

| ክፍለ ትምህርት ስምስት፡ ቃላት |
|---|
| **ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት**<br>• ቃላትን ተጠቅመው ትክክለኛ አረፍተ ነገሮች ይጽፋሉ፡፡ |

**የክፍለ ትምህርቱ ይዘት**

- ቃላትን ተጠቅሞ ትክክለኛ ዐረፍተነገር መጻፍ፡፡

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል አምስት ስለ ዋና ቃላት የሚጠይቀውን ፭ኛ ትዕዛዝ ሲሰሩ ተማሪዎች የሚጽፏቸው ቃላት የተለያዩ እንደሚሆኑ ቀድሞ በማወቅ ማገዝና ምክንያታቸውን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች በቁጥር ፪ ስር የተዘረዘሩትን ውስብስብ ቃላት ተጠቅመው ዓረፍት ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- ሐረጋትን በመለየት የተሟላ አረፍተ ነገር ይጽፋሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- ሀረጋትን መለየት፡፡

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል ስድስት ሰዋስው በሚለው ክፍል አንድ አረፍተ ነገር ሲዋቀር ሊኖሩት ስለሚገባ ሰዋስዋዊ ህጎች ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በቀረቡት ሀረጋት ዓረፍት ነገር እንዲመሰርቱ በማድረግ ያለማምዷቸው፡፡

### መርጃ መሣሪያዎች

- አጭርና ረዥም ልቦለዶች
- ግጥሞች
- መጣጥፎች
- ጥናታዊ ጽሑፎች

### ግምገማ

- የአዳመጡትን ምንባብ መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡
- በንግግር ተግባራት መሳተፋቸውን አቀራረባቸውን በክፍል ውስጥ መመልከትና ማረጋገጥ፡፡
- በንባብ ክፍል የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡
- ጽሑፉን አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን የጻፉትን እርማት ማድረግና ማረጋገጥ፡፡
- አጭር ድርሰት መጻፋቸውን ማስታወሻ ደብተሮቻቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፡፡

- ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀም እንደቻሉ መልመጃዎችን በማሰራትና በማረም ማረጋገጥ፡፡
- ሰዋስዋዊ ህጎችን ተከትለው ዓረፍተ ነገር ሥራት መቻላቻውንየተሰጧቸውን መልመጃዎች በማረም አረጋግጦ ግብረ መልስ መስጠት፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

**ክፍለ ትምህርት ስምስት፡ ቃላት**

በተራ ቁጥር ፩ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ የአረፍተ ነገሩ ዋና የሚባለውና አዲስ የሆነውን ቃል እንዲያወጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ምሳሌ፣ ከመጀመሪያው አንቀጽ የሚነሽጥ፣ ከሁለተኛው አንቀጽ ፅጌረዳ፣ እሾህ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ሊወጡ ይችላሉ፡፡ ቀሪውን ደግሞ ተማሪዎች እንዲያወጡና ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃል እንዲፈልጉ ያግዟቸው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች ስተገባበር

መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ ስጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ስመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት: ባህላዊ ክንውኖች (8 ክፍለ ጊዜ )

## ርእስ፡ ባህላዊ ክንውኖች

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩትሁ በኋላ፦**

- አዳምጣው ሰፋፊ እውነታዎች ላይ ይወያያሉ::
- ተማሪዎች አዳምጠው ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን ከጽሑፉ ውስጥ ያወጣሉ::
- አዳምጠው ለጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ::
- በሚሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ያደርጋሉ::
- በርስ በርስ ንግግር ይሳተፋሉ::
- በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያሉ ማስተዎሻዎችን አንብበው ይመዝናሉ::
- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተሟላ አንቀጽ ይጽፋሉ::
- በተጨባጭ ርእሰ ጉዳች ላይ ይጽፋሉ::
- የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይለያሉ::
- ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ::
- ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ይለያሉ::

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

### የዘመን አቆጣጠር

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የሚነበብላቸውን ምንባብ በንቃት ያዳምጣሉ፤
- የማዳመጥ ጥያቄዎችን ይሠራሉ፤

**የክፍለ ትምህርቱ ይዘት**

- የጊዜ አቆጣጠርን የተመለከተ መረጃ::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት መጀመሪያ የክፍለ ትምህርቱን ርዕስና ዓላማዎች በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ለተማሪዎች ያስተዋውቋቸው:: ተማሪዎች ለማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ያነሳሱዋቸው:: የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማንሳት የተማሪዎች ትኩረት እንዲሰበሰብ ያድርጉ::

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ንገሩ::
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የዘመን አቆጣጠሮችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ::
3. ርእሱን ተመልክታችሁ ስለ ዘመን አቆጣጠር ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

   ግምታችሁን በደብተራችሁ አስፍሩና ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ምን ያህል ትክክል እንደነበረና እንዳልነበረ አረጋግጡ::
4. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት "የዘመን አቆጣጠር" ከሚለው ጽሑፍ የተወሰዱ ናቸው::

   ስለ ፍችያቸው የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

   ሀ. ዓውድ ለ. መከንዳት ሐ. ባህረ ሐሳብ

ከዚያም ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን በማስታወሻ ደብተሮቻቸው እንዲይዙ ይንገሯቸውና ቀጥሎ የቀረበውን አዉድ ጥርት ብሎ ለሁሉም ተማሪዎች ሲሰማ በሚችል ድምፀ በርጋታ ያንብቡላቸው::

## የዘመን አቆጣጠር

የዘመን አቆጣጠርን ዘዴ በኛ ሀገር ባሕረ ሐሳብ ("የሀሳብ" ወይም "የሂሳብ ባሕር" ይሉታል:: አንዳንድ ቦታ ሐሳብ ብርሃን፡ መጽሐፈ ሐሳብ የሚል ስም ሲሰጠውም ይስተዋላል:: ዘዴውን (ለሁለተኛ ወይም ለሦስተኛ ጊዜ) ያገኘነውና እኛ ያስፋፋነው በ13ኛ ምእት ዓመት የኖረ አቡ ሻክር የሚባል አንድ ግብጻዊ በዐረብኛ ካቀነባበረው ባሕረ ሐሳብ ስለሆነ ራሱን አቆጣጠሩንም አቡሻክር (አቡሻኽር) እንለዋለን:: ድርሰትን በደራሲው መጥራት አዲስ ነገር አይደለም:: እኛ ኢትዮጵያዊያን መቼ ወደ እኛ እንዳመጣነው አይታወቅም:: ግን መጀመሪያ ራሳችን የደረስንበት የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት እንደነበረን የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች አሉ:: በዛ ላይ የውጭውን እውቀት በተደጋጋሚ በተለያየ ዘመን እንዳመጣነው አያጠራጥርም:: አንደኛ የስያሜ ጉዳይም አለ::

በግእዙም የባሕረ ሐሳብ መጻሕፍት ውስጥ እንደሚታየው ለአንዱ ነገር (ሐሳብ)፣ ለራሱ ለትምህርቱ ሳይቀር፣ ብዙ የተለያዩ ስሞች ተሰጥተውት ይገኛል፤ይህ ከሆነ ምንጩ የተለያየ ለመሆኑ ክብደት ያለው ማስረጃ ነው:: ሁለተኛ አቡ ሻክር የኖረው በዓሥራ ሶስተኛው ምእተ ዓመት ውስጥ ሆኖ ሳለ "አቡሻክር" ብለን በስሙ በምንጠራው የግዕዝ መጽሐፍ ውስጥ ስለዘመን አቆጣጠር ችግር በአስራ ስድስተኛው ምእተ ዓመት የነበረ ክርክር ይገኝበታል::

ዘመን እንዴት (ለምን) ይለካል?

እስካሁን እንደምናውቀው ዘመን መጀመሪያም መጨረሻም የለውም:: ታድያ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለውን ነገር መለካት (መከንዳት) እና መቁጠር ይቻላልን? ከየት ጀምረን፣ እንደምንስ አድርገን፣ እንከንዳው? እንዴት እንቁጠረው? ዘመን ሳይቆጠር የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የገጠማቸው ችግር ይህ ነበር:: ሕዝቦች በየመሰላቸው በተለያየ መንገድ ሞክረውታል:: የዘመን አቆጣጠር ባህል (ትውፊት) ነው የሚባለው ለዚህ ነው:: የሞከሩትም በሁለት መንገድ ነው (በሰው ሠራሽ ነገሮችና በተፈጥሮ ክሥተቶች እየተመሩ)::

መምህር/ት ፣ ማንበብዎን ለአፍታ ከዚህ ላይ ቆም አድርገው ተማሪዎች ምን ያህል በንቃት እየተከታተሉ እንደሆነ ቀጥሎ የቀረቡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በማንሳት ይፈትሹ::

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምን ተረዳችሁ?
2. ቀጥሎ ያለው ቅንጫቢ ጽሑፍ ስለምን ጉዳይ ሊያነሳ ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

መምህር/ት፣ የተማሪዎችን መልሶች ከሰሙና ግብረመልስ ከሰጧቸው በኋላ ቀጣዩን ክፍል ማንበብ ይቀጥሉላቸው::

ዘመን መጀመሪያም መጨረሻም ባይኖረውም በዓለማችን ውስጥ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሰው የሚመጡና የተወሰነ ጊዜ ቆይተው የሚሄዱ ነገሮች ወይም የተፈጥሮ ክስተቶች አሉ:: መሬት ሲለካ ወንዞች፣ ተራራዎች የድንበር ምልክቶች እንደሚደረጉ እነዚህም የተፈጥሮ ክስተቶች ዘመን ሲለካ የመነሻና የመድረሻ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: እንዲያውም ዘመንን መለካትና መቁጠር ካስፈለገበት ምክንያቶች አንዱ የእነዚህ ክስተቶች እየተመላለሱ መምጣት ነው:: ምክንያቱም ክስተቶች ምልክት ከመሆናቸውም በላይ እየተመላለሱ እየመጡ ሕይወታችንን ይነኩብናል:: ምልልሳቸው ከቁጥጥራችን ውጪ ስለሆነ ተመልሰው የሚመጡበትን ጊዜ ማወቅና እየጠበቁ መታዘዝ ወይም ተጽእኖዋቸውን ለማምለጥ ዘዴ መፈለግ አለብን:: ሕይወታችንን የምንመራው እነሱ በሚያዝዙን መሠረት ነው፤ ሙሉ ነፃነት የለንም:: ለምሳሌ በተወሰነ ጊዜ ቀኑ ይጀምራል፤ ይኸ አንድ ክስተት ነው:: ቀን ጀመረ ብለን ለሥራ እንጣደፋለን:: በተወሰነ ጊዜ ቀኑ ያልቃል፤ ማለትም፣ የተወሰነ ጊዜ ቆይቶ ይሄዳል፤ ይህም አንድ ሌላ ክስተት ነው:: ሥራ እንድናቆም የቀኑ ማለቅ ያስገድደናል:: በተወሰነ ጊዜ አየሩ ይሞቃል -- ሌላ ክስተት:: እርሻ ለማረስ (ሰብል ለመሰብሰብ) እንጣደፋለን:: በተወሰነ ጊዜ አየሩ ይቀዘቅዛል፤ ዝናብ ይዘንባል:: አየሩ የሚቀዘቅዘው፣ ዝናብ የሚዘንበው መቼ እንደሆነ አስቀድመን ማወቅ አለብን፤ ቀዝቃዛውን ዘመን በሕይወትና በጤና ለማለፍ፣ በዝናቡ ለመጠቀም ብዙ ዝግጅት ያስፈልገናል:: አለበለዚያ በብርድም ሆነ በእህል እጦት እናልቃለን:: ተዝናንተን ቁጭ ብለን ሁለተኛውን ዙር መጠበቅ አንችልም፤ አቅሙ የለንም::

እነዚህ በዓለማችን ውስጥ ያሉ ተመላላሽ ክሥተቶች ጌቶቻችን (ተጽእና የሚያመጡብን) ከሆኑ እንድንታዘዛቸው ወይም እንድንቋቋማቸው እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ማወቅ ግዴታችን ነው::

ተመላላሾቹ ክሥተቶች (የተፈጥሮ ምልክቶች) በመከሠት ላይ የሚፈጁት ዘመን ወይም ጊዜ በግዕዝ ቋንቋ “ዓውድ” ይባላል። “ዓውድ” ማለት “ዙሪያ”፣ “ክብ”፣ “እንደቀለበት ዞሮ የሚገጥም ጊዜ” ማለት ነው።

ከዘመን ቆጠራ ጥቅም ዋናው ታሪክን ለመመዝገብ ስለሆነ አባቶቻችን የውጭ ታሪክ ጸሐፊዎችን፣ በተለይም 13ኛው ምእተ ዓመት የኖሩትን አቡ ሻክርንና ጊወርጊስ ወልደ ዓሚድ (ጂርጂስ ኢብን አል-ዓሚድን)፣ አርአያ በማድረግ የኢትዮጵያን ነገስታት ታሪክ በባሕረ ሐሳብ መጽሐፋቸው ይመዘግባሉ።

ሁለተኛ:- የባህረ ሐሳብ ሊቃውንት የዘመን መለዋወጥ ከከዋከብት (በተለይም ከፕላኔቶቹ) ሂደት ጋር የተያያዘ መሆኑን እንደደረሱበት ግልጽ ነው። ግን መምህራኑ ከዚህ አልፈው በተፈጥሮ ክስተቶች ሁሉ አንዳንድ ኮከብ እያሰለጠኑባቸው ነፋስን፣ ድርቅን፣ ቸነፈርን ክዋክብት መሆናቸውን ያመለክታሉ።

(ምንጭ:- ጌታቸው ኃይሌ። 1993። ከገጽ 19-21 ለመማሪያ እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

ውድ መምህር/ት!

አንዴ ተማሪዎችን አስደምጠው ከጨረሱ በኋላ የተወሰኑ ደቂቃዎችን በመውሰድ ተማሪዎች የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሠሩ ይንገሯቸው። ከዚያም ለጥያቄዎች ያላገኙዋቸው መልሶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ቀደም ባነበቡላቸው መንገድ ለሁለተኛ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸውና ቀሪ መረጃዎችን ከቅንጫቢ ጽሑፉ እንዲያወጡ ያድርጉ። በመጨረሻም በተሰጡት ትእዛዛት መሠረት ተማሪዎችን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ያሠሯቸው፤ ለተማሪዎች መልሶች ግብረ መልስ በመስጠት ያግዟቸውም።

## ክፍለ ትምህርት ሁለት: ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በየአካባቢያቸው ባሉ ባህላዊ ክንውኖች ላይ መረጃ በመሰብሰብ ለክፍሉ በንግግር ያቀርባሉ፤
- በየአካባቢያቸው ባሉ የባህላዊ ህክምና ጥበብ ተስተላልፎትና ምስጢራዊነት ላይ መረጃ በመሰብሰብ በቡድን ይወያያሉ፤
- በየአካባቢያቸው ባሉ ባህላዊ ጋብቻን በተመለከተ የቃል ዘገባ ያቀርባሉ፤

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ባህላዊ ክንውኖችን አስመልክቶ የሚቀርብ ንግግር።
- አካባቢያዊ የባህል ህክምና ጥበብን የተመለከተ መረጃ።
- ባህላዊ ጋብቻን የተመለከተ መረጃ።

### የክፍለ ትምህርት ስቀራረብ

በክፍለ ትምህርት ሁለት ንግግር የሚለውን ክፍል ዓለማዎች ለተማሪዎች ያስተዋውቋቸው:: በዚህ ክፍል ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ወደመስክ በመውጣት መረጃ እንዲሰበስቡ የሚያዝዙ ተግባራት ቀርበዋል:: እነዚህን ተግባራት ለማሰራት እርስዎ አመቺ በሚሉት መንገድ ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ይከፋፍሏቸው:: ተማሪዎች እንደሚገኙበት አካባቢ ባህል ከታላላቆቻቸው፣ ከወላጆቻቸውና ከአካባቢ ሽማግሌዎች ወይም አረጋዊያን ጋር እንዴት መረጃ ማግኘት እንዳለባቸው ይጠቁሟቸው:: መረጃዎችን ሲወስዱ ፈቃድ መጠየቅ እንዳለባቸውም ያስታውሷቸው:: ያገኙዋቸውን መረጃዎችም እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ይንገሯቸው:: የሰበሰቧቸውን አሳጥረው መረጃዎች ክፍል ውስጥ በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው:: በዚሁ ክፍል በተራ ቁጥር ፩፣ ፪፣ ፫ እና ፬ ላይ የቀረቡትን ተግባራት በመመሪያዎቹ መሠረት እንዲሠሯቸው ያግዟቸው::

### ክፍለ ትምህርት ሦስት: ንባብ

## ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለሀገረሰባዊ ህክምና ጥበብ ምንነት፣ ቅመማ ሂደት፣ እና ትኩረት አንብበው በመረዳት ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን ይዘረዝራሉ፤
- የተዘረዘሩትን መረጃዎች ይተነትናሉ፤

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- አንብበበው በመረዳት ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን መዘርዘር::
- የተዘረዘሩትን መረጃዎች መተንተን::

### የክፍለ ትምህርቱ ስቀራረብ

ክፍለ ትምህርት ሦስት ንባብን ለማስተማር “ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ” በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቧል:: እንደተለመደው ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት የክፍለ ትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቋቸው:: ስለ“ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ” ከዚህ ቀደም ያላቸውን እውቀት ለመረዳት ያመችዎ ዘንድ በተማሪዎች መጽሐፍ የቀረቡትን ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው:: በመልሶቻቸው ላይ የእርስዎን አስተያየትና ሀሳብ በመጨመር ወደማንበብ እንዲሸጋገሩ ያነቃቋቸው:: ምንባቡን ተማሪዎች በለሆሳስና በእርጋታ በየግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ:: ስለ “ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ” ምንነትና መድሀኒቶቹ ሲዘጋጁ ስለሚደረጉ ጥንቃቄዎች የሚያወሱትን የመጀመሪያዎቹን ስድስት አንቀጾች ከአነበቡ በኋላ ንባባቸውን ቆም አድርገው በንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ላይ ሀሳባቸው እንዲሰጡ ያድርጓቸው:: በመቀጠልም “ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ” ተስተላልፎት፣ ለባህላዊ መድሀኒትነት የሚውሉ ግብዓቶች፣ ሊሰጥ ስለሚገባው ትኩረት የሚያነሱትን ቀጣይ የምንባቡ ክፍል እንዲያነቡ ያድርጉ::

የዕለቱ ምንባብ በግንዛቤ ይገባደድ ዘንድ የንባብ እንቅፋቶችን በተቻለዎት መጠን እንዲቀረፉ ያድርጉ:: ተማሪዎችዎ ምንባቡን እንደጨረሱ ጊዜ ሳይሰጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በክፍል ሥራ መልክ በቃል ያሠሯቸው:: ተማሪዎችዎ አንብበው መረዳት አለመረዳታቸውን ማረጋገጥዎትን ቸል አይበሉ:: በመጨረሻም ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሠሩ ያግዟቸው:: በመልሶቻቸውም ላይ ግብረ መልስ ይስጧቸው::

## ክፍለ ትምህርት አራት: ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተሟላ አንቀጽ ይጽፋሉ::
- በተጨባጭ ርእሰ ጉዳች ላይ ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተሟላ አንቀጽ መጻፍ ::
- በተጨባጭ ርእሰ ጉዳች ላይ ድርሰት መጻፍ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

በክፍለ ትምህርት አራት ጽሕፈት በሚለው ክፍል በአካባቢያቸው በሚከናወኑ ባህላዊ ልምምዶች ላይ አንቀጽና ድርሰቶች እንዲጽፉ ያድርጉ:: በተራ ቁጥር ፩፣ ፪፣ ፫ እና ፬ ላይ ከቀረቡት ተግባራት መካከል በዕጣ ለተማሪዎች ከፋፍለው በመስጠት በመመሪያዎቹ መሠረት እንዲሠሯቸው ያግዟቸው:: ተማሪዎች የጻፏቸውን አንቀጾችና ድርሰቶች በጥንቃቄ በመመርመር ግብረ መልስ ይስጧቸው::

## ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያስረዳሉ::
- ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች::
- ተመሣሣይ ቃላት::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ቃላት የሚለው ክፍል በተመሳሳይ ቃላትና በቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችዎች ላይ አተኩሯል:: ቃላት ሁለት ዓይነት ፍቺዎችን ሊሸከሙ ይችላሉ:: አንደኛው ቀጥተኛ ወይም መዝገበቃለዊ ፍች ሲሆን ይህም የሚገቡበትን ዓውድ መሠረት ያለደረገ ፍች ነው:: ይህ ዓይነት ፍች እማሬያዊ ፍች ይሰኛል:: በሌላ በኩል ተደራቢ ፍች ሊይዙ ይችላሉ:: ይህኛው የፍች ዓይነት በሥነ ልሳናዊ ወይም ንግግሩ በሚደረግበት ጊዜ ባለው ሥነ ልሳናዊ ባልሆነ አውድ ላይ የተንጠለጠለ ነው:: ፍካሬያዊ ፍች በመባልም ይታወቃል:: ለምሳሌ:- "መሬት" የሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺው "ምድር" ሲሆን ፍካሬያዊ ፍችው "ቻይ" ሊሆን ይችላል:: "መብረቅ" የሚለው ቃል "ብልጭታ ነጎድጓድ" የሚል እማሬያዊ ፍች ሲኖረው "ኃይለኛ አስደንጋጭ" የሚል ፍካሬያዊ ፍች ይኖረዋል:: በእነዚህ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ገላጻ ካደረጉላቸው በኋላ በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ስር የቀረቡትን ተግባራት በትዕዛዛቱ መሠረት እንዲሠሩ ያግዟቸው::

## ክፍለ ትምህርት ስድስት: ሰዋስው

### የክክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን ይለያሉ::
- ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የነጠላና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮች ምንነት ::
- የውስብስብ ዐረፍተ ነገሮች መዋቅር ::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

በክፍለ ትምህርት ስድስት ሰዋስው በሚለው ክፍል የውስብስብ አረፍተ ነገሮችን አወቃቀር ለማስተማር ቀርቧል:: በመጀመሪያ ስለ ውስብስብ አረፍተ ነገር መዋቅር ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው:: ለተግባራዊ ልምምዱ ደግሞ በተራ ቁጥር ፩ ላይ የቀረቡትን ተራ አረፍተ ነገሮች በማቀናጀት ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሠርቱ ያድርጉ፣ ያግዟቸውም:: በተጨማሪም በተራ ቁጥር ፪ ላይ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ያካተተ አንቀጽ ቀርቧል:: ተማሪዎች ከአንቀጹ ውስጥ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዲለዩ ያግዟቸው:: በተራ ቁጥር ፫ ስር ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው ያፈለቋቸውን ውስብስብ አረፍተ ነገሮች እንዲመሠርቱ ያድርጓቸው:: በመጨረሻም በመሠረቷቸው አረፍተ ነገሮች ላይ ግብረ መልስ ይስጧቸው::

### መርጃ መሣሪያዎች

- ጋዜጦች
- መጽሔቶች
- የአማርኛ መዝገበ ቃላት
- የአማርኛ ሰዋስው መጻሕፍት

### ግምገማ

- ተማሪዎች ያዳመጡትን ምንባብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎች ያቅርቡላቸው::
- በመመሪያዎቹ መሠረት የግል ንግግር፣ ውይይትና ጭውውቶችን ማቅረብ መቻላቸውን ያደረጓቸውን ቃላዊ ተግባቦቶች በመከታተል ያረጋግጡ::
- ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክንውንን በተግባር ላይ ማዋለቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎች ያቅርቡላቸው::
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አንቀጾችና ድርሰቶች መጻፋቸውን መልመጃዎችን በማረም ያረግግጡ::
- ተማሪዎች የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቾች መለየታቸውን መልመጃዎችን በማረምና በቃል ጥያቄዎች ያረጋግጡ::
- ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መለየትና መመሥረት መቻላቸውን መልመጃዎችን በማረም ያረጋግጡ::
- በተማሪዎቹ ትግበራ ውጤት ላይ ቅሬታ የሚኖርዎት ከሆነ ቅር ያለዎትን ክፍል እንደገና በማሠራት የተማሪዎቹን የትግበራ ውጤት ለማጎልበት ጥረት ያድርጉ፤ እንደዚሁም እዚህ የተሰጡት ናሙና መልሶች ፍጹም በማይሆኑበት ጊዜ አማራጭ መልሶችን መስጠት እንደሚችሉ አይርሱ::

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍል ትምህርት ሦስት: ንባብ

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን “እውነት” ስህተት የሆኑትን ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ::

| | | |
|---|---|---|
| 1. እውነት | 2. እውነት | 3. ሀሰት |
| 4. እውነት | 5. ሀሰት | 6. ሀሰት |

ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፩. ቀጥሎ በቀረበው ሰሀድ ውስጥ በጉልህ የተጻፉ ቃላት አሉ፡፡ የእነዚህን ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከታች በ "ለ" ምድብ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች ትክክለኛውን ለዛምዱ፡፡

1. ሠ 2.ለ 3. ሐ 4. መ 5.ሀ

፪. ቀጥሎ በተዘረዘሩት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በምሳሌው መሠረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችያቸውን ስጡ፡፡

1. እሷ <u>አርፋለች</u>፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡- እረፍት አድርጋለች

   ፍካሬያዊ ፍች፡- ሞታለች

2. <u>ወንበር</u> ላይ ወጣች፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡- መቀመጫ

   ፍካሬያዊ ፍች፡- ስልጣን

3. እሷ <u>ተፋችው</u>፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡- ከአፏ ውስጥ አውጥታ ጣለችው

   ፍካሬያዊ ፍች፡- ጠላችው

ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ተራ ዓረፍተ ነገሮች በአንድ አረፍተ ነገር ጻፏቸው፡፡

1ሀ. አብሮ መብላት የደስታ ምንጭ ነው

1ለ. የእርቅ ምልክት ነው፡፡

1. <u>አብሮ መብላት የደስታ ምንጭና የእርቅ ምልክት ነው</u>

2ሀ. ወንድሜ ጎበዝ ጋዜጠኛ ነው፡፡

2ለ. ወንድሜ አንጋፋ ደራሲ ነው፡፡

2. <u>ወንድሜ ጎበዝ ጋዜጠኛና አንጋፋ ደራሲ ነው፡፡</u>

3ሀ. በእጅ መመገብ ባህላችን ነው፡፡

3ለ. በእጅ መመገብን እንኮራበታለን፡፡

3. <u>በእጅ መመገብ የምንኮራበት ባህላችን ነው፡፡</u>

## የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

ውድ መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ለመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት፡ ስካቶ ትምህርት (8 ክፍለ ጊዜ)

## ርዕስ፡ ስካቶ ትምህርት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፦

- አዳምጠው ያልተሟላ አንቀጽ ያሟላሉ፡፡
- አዳምጠው የራሳቸውን ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡
- በተለያዩ ይዘቶች ላይ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡
- ጽሑፍ አዘጋጅተው ያሳያሉ፡፡
- የቃላት ፍች ይሰጣሉ፡፡
- በተወሰነ ርእስ ጉዳይ ላይ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- ቅድመ፣ውስጠና ድህረ ቅጥያዎች ይለያሉ፡፡
- ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ መዋቅሮችን ይመሠርታሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ፈተናን ወደ መልካም ዕድል መለወጥ

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- አካል ጉዳተኛ ባለታሪኳ ስላላት ጥንካሬ ዝርዝር መረጃዎችን በማታወሻዎቻቸው ይይዛሉ፡፡
- አዳምጠው ያልተሟላ አንቀጽ ያሟላሉ፡፡
- አዳምጠው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች**

- አስቸጋሪ ፈተናዎችን ወደ ጥሩ ዕድል መለወጥ ከሚለው ምንባብ መረጃ ማውጣት፡፡
- ያላለቁ አንቀጾችን መሙላት፡፡

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

የመጀመሪያው ክፍል “ፈተናን ወደ መልካም ዕድል መለወጥ” በሚል ርዕስ ማዳመጥን ለማስተማር ቀርቧል:: በመጀመሪያ የክፍለ ጊዜውን ርዕስና ዓለማዎች በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ለተማሪዎች ያስተዋውቋቸው:: ተማሪዎች ትኩረታቸውን እንዲሰበስቡና ለማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጉ:: በመቀጠል ቀጥሎ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ በቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቃል እንዲገልጹ ያድርጉ::

ውድ መምህር/ት፣ ለተማሪዎች “መሰናክልን ወደ ዕድል መለወጥ” የሚል ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ በመንገር በሚያደምጡበት ጊዜ ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ:: ከዚያም ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማ በሚችል ድምጽና ሁሉንም ተማሪዎች ባማከለ ፍጥነት ከታች የቀረበውን አሀድ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እስከሚለው ድረስ ያንብቡላቸው::

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በአካባቢያችሁ እናንተ የምታደንቋቸውንና ውጤታማ ናቸው የምትሏቸውን አካል ጉዳተኞች ለመምህራችሁ ንገሩ:: የሠሯቸውንም ሥራዎች በቃል ተናገሩ::

፪. ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ስለሚባሉት ኢትዮጵያዊት ከአሁን ቀደም ሰምታችሁ የምታውቁት ነገር አለ? ሰምታችሁ የምታውቁ ከሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ::

### ፈተናን ወደ መልካም ዕድል መለወጥ

የትነበርሽ ንጉሴ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ እና የአካል ጉዳተኛ መብቶች ተሟጋች ናት:: እ.ኤ.አ በ2017 "የአካል ጉዳተኛ መብቶችን እና ማካተቶችን በማስተዋወቅ እንዲሁም በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአእምሮ ውቅርን መለወጥ የሚያበረታታ ሥራዋ" ራይት ላይቭሊሁድ አዋርድን ተሸልማለች::

የትነበርሽ ንጉሴ ጥር 16፣ 1974 ዓ.ም በወሎ ክፍለ ሀገር አማራ ሳይንት ተወለደች:: በአጋጣሚት የማጅራት ገትር ህመም ምክንያት የዐይን ብርሃንዋን ያጣችው በ5 ዓመቷ ነበር:: ፈጣሪዋን ከማማረርና ከመውቀስ ግን ይህን አጋጣሚ በተወለደችበት በአማራ ክልል በስፋት ይፈጸም ከነበረው ያለዕድሜ ጋብቻ የማምለጫ ዘዴ አድርጋ ቆጠረችው::

አስራ ሁለት አመት እስኪሞላት ድረስ የነበረባት የአካል ጉዳት በሌሎች ዘንድ ተቀባይነትዋን ሊቀንሰው እንደሚችል አስባው አታውቅም ነበር:: ነገር ግን እየዋለ እያደረ የዕድሜ እኩያዎቿ የነበሩ ልጆች ጓደኛዋ ከመሆን ሲቆጠቡ ታስተውል ጀመር:: በዚህም በክፍለ ሀገር ውስጥ ዐይነ ስውር ሴት መሆኗ ብዙ እንቅፋቶች ሊያጋጥሟት እንደሚችሉ ተገነዘበች:: ለስድስት ወራት ጓደኛ አልነበራትም:: ሁሉም በጨዋታ

ሜዳ ላይ እየዋለ እሷን ልብ የሚላት አልነበረም:: በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ስትጀምር ግን የእርሷን ርዳታ በመፈለግ ሁሉም ጓደኛዋ መሆን ፈለጉ:: ይህ ደግሞ “ለራሴ በልጬ ከተገኘሁ፣ ራሴ ላይ ለውጥ ማምጣት ከቻልኩ ሌሎችን መርዳት እችላለሁ” ብላ እንድታስብ አደረጋት::

የትነበርሽ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በሻሸመኔ ካቶሊክ የዐይነ ስውራን ት/ቤት ተከታትላ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (አካታች ትምህርት ቤት) ገብታ እስከ 12ኛ ክፍል እዚያው ተማረች:: በትምህርት ቤቱ ካላት አካዳሚክ ተሳትፎ በተጨማሪ የተማሪዎችን አማካሪ ጨምሮ ከ6 በላይ የክለቦችን ክበባት መርታለች::

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. እስካሁን ከአዳመጣችሁት የየትነበርሽ ታሪክ የእናንተን ትኩረት የሳባችሁ ምኑ ነው?

፪. ከቀጣዩ ክፍል ምን ምን ታሪኮች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለጓደኞቻችሁ በቃል አጋሩ::

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያጠናች ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪዋን በህግ፣ የማስተርስ ዲግሪዋን ደግሞ በማህበራዊ ሥራ ይዛለች:: በተለያዩ የዩኒቨርስቲ ክበቦች ላይ ትሳተፍ ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ የጸረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ክበብ አንዱ ነው:: በዚህም የመኢአድ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን ከ2004 - 2005 በመምራት፣ በ2006 የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (አአዩ) ሴት ተማሪዎች ማህበርን በመመስረት እንዲሁም የማህበሩ የመጀመሪያ ፕሬዝዳንት በመሆን አገልግላለች::

በሴት ልጆች ትምህርት ላይ አጥብቃ በመስራቷ እ.ኤ.አ. በ2003 በደቡብ አፍሪካ የተቀበለችውን “የአማኒታሪ” ሽልማትን (አፍሪካዊ አጋርነት ለወሲባዊ እና ስነተዋልዶ ጤና እና የሴቶች መብቶች) ጨምሮ ለፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ባገለገለችበት ወቅት በርካታ ብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን አግኝታለች:: ለአብነትም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

- የጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ተሟጋቾች “የአማኒታሪ” ሽልማት ፣ እ.ኤ.አ. 2003 ፣ ጆሃንስበርግ ፣ ደቡብ አፍሪካ ፡
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአዲስ አበባ ኤች.አይ.ቪ / ኤድስ መከላከያና ቁጥጥር ጽህፈት ቤት (ኤች.ፒ.ኮ.) ጋር በመተባበር እጅግ በጣም ጥሩ የኤች.አይ.ቪ / ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ ማስተባበር የግለሰብ ሽልማት :: ጥቅምት 7 ቀን 2005 አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ ::
- በጄኔራል ሜዲካል ሐኪሞች ማህበር የተሰጠው ምርጥ የኤች.አይ.ቪ / ኤድስ ብሔራዊ አክቲቪስት ፣ 2005 ፣ አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ ::
- ራይት ላይቭሊሁድ ኣዋርድ እ.ኤ.አ. 2017

ወ/ሮ የትነበርሽ ከአካዳሚክ ህይወቷ ባሻገር በበጎፈቃደኝነት ከ20 በላይ ድርጅቶች ውስጥ ያገለገለች ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በኢትዮጵያ ዓይነ ስውራን የሴቶች ክንፍ ማህበር ለ4 ዓመታት (እ.ኤ.አ. ከ2003 እስከ 2007) መርታለች፡፡ ከዚያም በመቀጠል የአካል ጉዳተኞች ኢኮኖሚያዊ መብትን ጨምሮ በተለያዩ የልማት መርሃ ግብሮች ውስጥ እንዲካተቱ ለማበረታታት የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞችና የልማት ማዕከል (ኢ.ሲ.ዲ.ዲ.) የተባለ አገር በቀል ድርጅት ለማቋቋም ወሰነች፡፡ ከ2016 ጀምሮ ደግሞ ቀደም ሲል በዓለምአቀፍ አምባሳደሮች ቦርድ አባልነት ወክላው ከነበረው የአካል ጉዳተኞች እና ልማት ብርሃን ለዓለም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ላይ ትሰራለች፡፡

(ምንጭ፡- https://peoplepill.com/people/yetnebersh-nigussie፤ (የተገኘው ታህሳስ 25፣ 2014ዓ.ም)

በመጨረሻም በድህረ ማደመጥ ስር የቀረቡ ተግባራትን በትእዛዛቱ መሠረት ተማሪዎች እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በተዘጋጁ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ንግግር ያደርጋሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መናገር፡፡
- የተለያዩ ሚናዎችን ተላብሶ ንግግር ማድረግ ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት ሁለት ንግግር የሚለው ክፍል በአካቶ ትምህርት ሥር ባሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች፣ ክርክሮችና ንግግሮች እንዲያደርጉ ቀርቧል፡፡ ይህንን ለማከናወን በውይይትና በክርክር ጊዜ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ ነጥቦችን ከሌሎች የቀደሙ ምዕራፎች በማስታወስ ለተማሪዎች ያስረዱ፡፡ በመቀጠል የቀረቡትን ተግባራት ለማሠራት ለእርስዎ አመቺ በሚሉት መንገዶች ተማሪዎችን በቡድን ይከፋፍሉ፡፡ በዚህ ክፍል በተራ ቁጥር ፩፣ ፪፣ እና ፫ ስር የቀረቡትን ተግባሮች በመመሪያው መሠረት እንዲሠሩ ያግዟቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

# የአይበገሬነት ተምሳሌት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- "የአይበገሬነት ተምሳሌት" በሚል ርዕስ በመጽሀፋቸው የቀረበውን ምንባብ አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ::
- ከምንባቡ ዝርዝር መረጃዎችን በመውሰድ ይዘረዝራሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- አይበገሬነትን የተመለከተ መረጃ::
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መሥራት::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት ሦስት ንባብ በሚለው ክፍል “የአይበገሬነት ተምሳሌት ” በሚል ቀርቧል:: የክፍለ ጊዜውን ትምህርት ርዕስና ዓላማ በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ያስተዋውቋቸው:: በዚህ ክፍል የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎችን ያነቃቁ::

ውድ መምህር/ት፣

ጥሩ ያልሆኑ የንባብ ልምዶች ምን ምን እንደሆኑ ይጠይቋቸው:: ከተማሪዎችዎ መልስ ከተቀበሉ በኋላ በማጠቃለያ መልክ የሚከተሉትን ሐሳቦች ሊነግሯቸው ይችላሉ፤

- ማጉተምተም (ድምጽ እያሰሙ) ማንበብ
- ሲያነቡ በጣት መጠቆም
- እየተዘናጉ ማንበብ፣ ወደኋላ መመለስ
- ሲያነቡ በሓሳብ ወደ ሌላ መሽፈት፣ ወዘተ

ተተኳሪው የቋንቋ ትምህርት 2ኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች አሉታዊ ልምዶች ናቸው:: እነዚህ ልምዶች የተጠናወታቸው ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸው ደካማ ከመሆኑም በላይ የመረዳት አቅማቸውም ደካማ ነው:: ስለዚህ ታላሚ ተማሪዎች አማርኛን የሚማሩት እንደ 2ኛ ቋንቋ መሆኑን ተረድተው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያድርጉ::

ተማሪዎቹ አራቱን አንቀጾች ካነበቡ በኋላ ንባባቸውን ቆም አድርገው ከላይ ካነበቧቸው አራት አንቀጾች ያገኙትን ሀሳብ በቅድመ ንባብ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከሰጡት መልስ ጋር ምን ያህል እንደሚስማማ ሀሳባቸውን በቃል እንዲገልጹ እድል ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ከቀሪው ምንባብ ክፍል ምን እንደሚጠብቁ ሀሳባቸውን በቃል ያካፍሉ ዘንድ እድል ይስጧቸው፡፡ ከዚያም የጀመሩትን ንባብ እንዲጨርሱ ያድርጉ፡፡ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ድህረ ንባብ ተግባራትን በትዕዛዙ መሠረት መልሱ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የድርሰት ዓይነቶችን ይለያሉ፡፡
- በአካቶ ትምህርት ላይ በሚሠጡ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ድርሰት ይጽፋሉ ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የድርሰት ዓይነቶች፡፡
- በአካቶ ትምህርት ላይ በሚሠጡ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ድርሰት መጻፍ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት አራት ጽሕፈት በሚለው ክፍል የድርሰት ዓይነቶች በማስታወሻ መልክ ቀርበዋል፡፡ በዚህ ላይ ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል በተሰጧቸው ርዕስ ጉዳይ ላይ ድርሰቶች እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ በተራ ቁጥር ፩፣ ፪፣ ፫ እና ፬ ላይ የቀረቡትን ተግባራት በመመሪያዎቹ መሠረት እንዲሠሯቸው ያግዟቸው፡፡ ተማሪዎች የጻፏቸውን ድርሰቶች በጥንቃቄ በመመርመር ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በቅድመ እና ድህረ ቅጥያ መሃከል ያለዉን ልዩነት ይገልጻሉ፡፡
- ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላትን ይመሠርታሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ቅድመ እና ድህረ ቅጥያዎች፡፡
- ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላት ምሥረታ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት አምስት ቃላት በሚለው ክፍል የቅድመ ገብና ድህረ ገብ ቅጥያዎችን ምንነት እና እነዚህን ቅጣዮች በመጠቀም ቃል መመሥረት እንዲችሉ ለማድረግ ቀርቧል:: በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለተማሪዎች ማብራሪያ ይስጧቸው:: በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ሥር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሠሩ ያድርጓቸው:: ሥራዎቻቸውን በማረምም ግብረ መልስ ይስጧቸው::

### ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የንግግር ክፍሎችን ለይተው ያስረዳሉ::
- ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ ዐረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- የንግግር ክፍሎች::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል ስድስት ሰዋስው በሚለው ክፍል ቃላትን በአውዳቸው መሠረት የቃል ክፍሎቻቸውን እንዲለዩ ለማስቻልና ሰዋስዋዊ ሕጎችን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሠርቱ ለማስቻል ቀርቧል:: በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለተማሪዎች ገለጻ ካደረጉ በኋላ በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በትእዛዛቱ መሠረት እንዲሠሩ ያድርጓቸው::

### የመርጃ መሣሪያዎች

- ፖስተሮች
- ፎቶግራፎች
- በአካቶ ትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ አተኩረው የተዘጋጁ በራሪ ጽሑፎች
- ጋዜጦች፣ መጽሔቶች

### ግምገማ

- አዳምጠው መረዳታቸውን ማረጋገጥ፡፡
- አንብበው መረዳታቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ካዳመጡትና ካነበቡት መረጃ መያዛቸውን መከታተል፡፡
- ንግግር ማድረጋቸውን፣ በውይይትና ክርክር መሳተፋቸውን መከታተል፡፡
- ቅድመና ድህረ ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላት መመሥረት መቻላቸውን የሠሯቸውን መልመጃዎች በማረም ማረጋገጥ፡፡
- ከገቡበት አውድ በመነሳት የቃላትን የቃል ክፍል መለየታቸውን የሠሯቸውን መልመጃዎች በማረም ማረጋገጥ፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፪. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ቅድመና ድህረ ቅጥያዎችን አውጡ፡፡

1. -ኣዊ የሚለውን ድህረ ቅጥያ በመጠቀም
2. -ነት የሚለውን ድህረ ቅጥያ በመጠቀም
3. -ነት የሚለውን ድህረ ቅጥያ በመጠቀም
4. ኢ- የሚለውን ቅድመ ቅጥያና -ኣዊ የሚለውን ድህረ ቅጥያ በመጠቀም
5. መ- የሚለውን ቅድመ ቅጥያ በመጠቀም
6. -ኦሽ የሚለውን ድህረ ቅጥያ በመጠቀም

ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

፩. በምዕራፍ ሁለት የተማራችሁትን በማስታወስ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በጉልህ ተጽፈው የተሰመረባቸውን ቃላት የቃል ክፍላቸውን ለዩ፡፡

1. ግስ
2. ተውሳከ ግስ
3. ግስ
4. ስም
5. ቅጽል
6. ግሥ
7. መስተዋድድ

## የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

ውድ መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። ስመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው።

# ምዕራፍ ስምንት: ሥነግጥም ( 8 ክፍለ ጊዜ)

## ርእስ: ሥነግጥም

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩችሁ በኋላ፦

- የቀረበውን ግጥም በማዳመጥ ማብራሪያ ይሰጣሉ።
- የተሰጣቸውን ግጥም ተጠቅመው በግጥሙ ላይ ውይይት ያደርጋሉ።
- ግጥሞችን በመሰብሰብ ያነባሉ።
- የመማሪያ ክፍላቸውን በተመለከተ አጭር ግጥም ይጽፋሉ።
- የሥነግጥም ቃላት አጠቃቀምን ያብራራሉ።
- ሥነግጥም የሚያካትታቸውን ይዘቶች ይዘረዝራሉ።
- የቃላትን የፍች ልዩነት ያሳያሉ።
- እማሬያዊና ፍካሪያዊ ፍች አብራርተው ይጽፋሉ።

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

#### ሀገሬ ዋርካ ናት

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- "ሀገሬ ዋርካ ናት" በሚል ርእስ መምህሩ/ሯ የሚያነቡላቸውን ግጥም በማዳመጥ ማስታወሻ ይይዛሉ።
- በሚነበቡ ሥነጽሑፎች ላይ ውይይት ያካሂዳሉ።

**የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች**

- የተመረጡ ግጥሞችን ማዳመጥ፣ መግለጽ።
- በሚቀርቡ ግጥሞች ላይ መወያየትና መከራከር።

## የክፍል ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት፣

ሥነ ግጥም በባህሪው ዜማዊ ስለሆነ ግጥሞቹን ሲያነቡ ድምጽዎትን ከፍ በማድረግ ያንብቡላቸው:: ተማሪዎችዎም እንዲሁ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጉ:: እንደዝርው ጽሑፍ በለሆሳስ በፍጹም ሊነበብ አይገባም:: ግጥም ከሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘርፎች ይልቅ ቁጥብና ጥብቅ ነው:: የተብራራና ዝርዝር ነገር አይቀርብበትም:: ሰፊ የሆነ ሃሳብ፣ ግን ጥልቀት ያለው ጉዳይ እጥር ምጥን ባለ መንገድ የሚቀርብበት ዘርፍ ነው:: በስነ ግጥም የሰው ልጅ ህይወት ይዳሰሳል፤ ይቃኛል:: በዚህ ምክንያት የግጥም ትምህርት አስፈላጊነት ስለሚታመን ተማሪዎች ግጥም በመጻፍ እንዲለማመዱ ይርዷቸው:: ለዚህ እንዲያግዝዎ መጻፍን ለማስተማር የሚያግዙ ማስተማሪያ ዘዴዎች በዚህ የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ተካተዋል:: ጥቂት የግጥም ባህሪያትን በተመለከተ ለማስታወሻነት ከታች ቀርበዋል::

### የግጥም ባህሪያት

የቃላት ምርጫ

ሥነግጥም ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘርፎች ይልቅ ምርጥ ቃላትን ይሻል:: በመሆኑም በግጥም ውስጥ ያገኘነውን ቃል ሁሉ አንጠቀምም:: የምንጠቀማቸው ቃላት ለቁጥብነቱ፣ ለእምቅነቱና ለምስል ከሳችነቱ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን ነው:: በቃላት አጠቃቀማችን ውስጥ ልንገልፅ እንደፈለግነው ጉዳይ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቃላት አሉ::

ቃላት ምሁር፣

ድምፀ ቀድ ቃላት፣ ምሳሌ፦ ፏፏቴ ሿሿቴ፣

ፍጥር ቃላት፣ ምሳሌ፦

1. ጠጃጠጅ አምቡላ (ፈቃደ አዘዘ)፣
2. ተበጫጮት ቅልቅል ተቅላሎትሽ

   ማን ኮረዳ ነበርሽ ነበር ይላል

   አሁን

   (ሰይፉ መታፈሪያ፣"ሰባ ሰማኒያ")
3. ልጅቱ የዘመነችቱ

   ፊቷን ትጥብ እሽት

   ፍትግ ፍትግትግ

   ዳሩላዋን ልቅቅ ጥፍት

   ሌላ ምና ምንዱቅት እያለ ይቀጥላል

   (ሰይፉ መታፈሪያ፣ )

### ዘይቤ ቃላት፣

ዘይቤ ቃላት በጣም ብዙ መሆናቸው ይታወቃል። ከዚህ ውስጥ ሰውኛ፣ አያዎ፣ አነጻጻሪ፣ ለዋጭ፣ወዘተ. መሆናቸው ይታወቃል። ግጥምም ዘየዎችን እንዴት እንደሚጠቀም ጥቂት ምሳሌ እናሳይዎትና ቀሪውን እርስዎ ግጥሞችን እያነበቡ ለተማሪዎችዎ ይግለጹላቸው። ምሳሌ፦

1. ነፋሱም ፀጥ አለ ድምፁን አጥፋና
2. ባህርዛፉም ቆመ አደገደገና
3. ስትሰግድ ሳለች ወደምዕራብ ፊቷ
4. ተደፍቶ፣ እንዳዘዛት (ፀሐይ) ሃይማኖቷ፤

(ብርሃኑ ገበየሁ፣1999፣)

**ጉራማይሌ ቃላት፣** ምሳሌ፦ ከሰለሞን ደሬሳ ግጥም

አያቀናት ቅኔ

አያገጣጥማት ግጥም

አይጠልቃት ወለሎ

ዳፊ ዳፊ ማሎ ማሎ

ፈጠን ፈጠን ቶሎ ቶሎ። ተጠቃሽ ናቸው።

### ማፈንገጥ

ማፈንገጥ- አንዱ የግጥም መለያ ባህሪ ነው። አንድ ቋንቋ የራሱ የሆነ መዋቅር አለው። መዋቅር ድምጾች ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላት ተቀናጅተው ሐረጋትን፣ ሐረጋት ደግሞ አረፍተ ነገርን የሚመሠርቱበት ስልት ነው። በመደበኛ ጽሑፍ ውሰጥ ይህን ተከትለን ነው የምንጽፈው። ከዚህ በተለየ በግጥም ውስጥ ማፈንገጥ፣ ለቋንቋ ሥርዓት አለመገዛት ይታያል፤ ይህ የሚደረገው ያለ ዓላማ ሳይሆን ረቂቁን ለማጉላት፣ የማይታየውን ለማሳየትና ትኩስና ያልተለመዱ አገላለጾችን ለማሰማት ይቻል ዘንድ ነው።

### ድግግሞሽ

ገጣሚያን ለመልዕክታቸው ውበትና ጥንካሬ ሲሉ ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ስንኞችን እንዲሁም ከዚያ ባለፈ ያሉ መዋቅሮችን ከአንድ ጊዜ በላይ ይደግማሉ።

### ምስል ከሳችነት

በሥነግጥም ውስጥ የሚነሱ ጉዳዮች ለስሜት ህዋሶቻችን ቅርብነት እንዲኖራቸው ተደርገው ይቀርባሉ። ብርሃኑ /1999፤299/ ስለ ምስል ከሳችነት ሲገለፅ “ሥነግጥም የሚታዩና የሚሰሙ ብቻ ሳይሆን የሚነኩ፣ የሚዳሰሱ፣ የሚቀመሱ፣ የሚሸተቱ ነገሮች ወደ አንባቢ ስሜቶች ለማድረስ የሚችል ጥበብ ነው።” ይላሉ።

ምት

ምት ደግሞ በአንድ ዓይነት ሥርዓት አንድ ስልት መደጋገሙን የሚያሳይ ነው። በግጥም ውስጥ ምት አለ። ተፈጥሮ ራሷ የምት መገለጫ ናት። በእኛ ውስጥ ብዙ አይነት ምቶች አሉ። ስንተነፍስ፣ ልባችን ሲመታ፣ ስንበላ፣ ስንተኛ፣ ስንነሳ፣ ተመሳሳይ የሆነ ሥርዓት አለን። ከእኛም ውጭም ቢሆን ምቶች ይስተዋላሉ። ቀንና ማታ፣ የውሃዎች ድምፅ፣ የሰዓት ድምፅ፣ የወፎች ዝማሬና የወቅቶች መለዋወጥም ቢሆን በምት ውስጥ ይጠቃለላሉ። ግጥምም ሲጻፍ እንዲሁ የተመጠኑ ቃላት ሥርዓታዊ በሆነ መልኩ በተለካ ጊዜ ውስጥ መቀመጥ ሲችል ግጥሙ ምት አለው እንላለን።

ዘይቤዊ አገላለጾች

ብርሃኑ /1999፣89/ ዘይቤያዊ አገላለጽ በግጥም ውስጥ እንደምን እንደሚታይ ሲያስረዱ ሥነግጥም የአንድን ነገር ባህሪ፣ ተፈጥሮ፣ ቅርጽ፣ ቀለም ወዘተ ለማሳየት፣ ነገሮችን ከሌላ ነገር ጋር ያመሳስላል። ተቃራኒዎችን ያዛምዳል፣ ዘመዳሞችን ያፋታል። የአንድን ነገር ባህሪይ ወይም ይዞታ ለሌላ ነገር ያወርሳል፤ አንድን ነገር በሌላ ነገር ይወክላል፣ ይተካል። ይላሉ።

የበለጠ እውቀት ለማግኘት የብርሃኑ ዘሪሁንንና የብርሃኑ ገበየሁን መጻሕፍት ቢያነቡ መልካም ነው።

ሥነግጥም ዘሪሁን አስፋው፣ (1996) የሥነጽሑፍ መሰረታውያን፤ ብርሀኑ ገበየሁ፣ (1999)፣ የአማርኛ ሥነግጥም።

ውድ መምህር/ት!

ማዳመጥን ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች የምዕራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸው። በመቀጠል የግጥሙን ርዕስ በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው። ከዚያም አንድ አጭር ግጥም ሊያነቡላቸው እንደሆነ ይንገሯቸው። ማንበብ ከመጀመርዎ በፊት ግን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ ይጠይቋቸው። ጥቂት ተማሪዎች ከተናገሩ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች በጥሞና እንዲያደምጡና ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግዎን አይዘንጉ። አሁን ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማ በሚችል ድምጽ በዝግታ ያንብቡላቸው።

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ስለ ሀገር ፍቅር የተገጠመ የምታውቁት ግጥም ካለ ወይም ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሟቸው።

## ሀገሬ ዋርካ ናት!!!

ገና በጥዋቱ፣ ለስሟ መጠሪያ

ኢትዮጵያ ብሎ፣ ሲሰጣት መለያ

አንዳች ዕምቅ ሚስጥር፣ ለኛ ያልተገለጠ

ፈጣሪም አድልቶ፣ ከአርያም ሰጠ

ከአባይ ከወንዙ፣ ከዳሎል ዝቅታ

ከኤርታሌ ረመጥ፣  ከዳሽን ከፍታ

አክሱም አናቱ ላይ፣  ከላሊበላ ስር

ሀገሬ ተገምዷል፣  በወፍራም የደም ክር::

መምህር! የግጥሙን ንባብ እዚህ ላይ ገታ ያድርጉና ተማሪዎች እርስዎን እየተከታተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ከታች የቀረበውን ጥያቄ ይጠይቋቸው:: ግጥሙን ጨርሰው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው::

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

በቀረቡት ስንኞች ላይ የሩሳችሁን ስንኞች በመጻፍ ግጥሙን አሳድጉት፤ ኢትዮጵያን በግጥም ሳሉ::

ከአባይ ከወንዙ፣  ከዳሎል ዝቅታ

ከኤርታሌ ረመጥ፣ ከዳሽን ከፍታ

አክሱም አናቱ ላይ፣ ከላሊበላ ስር

ሀገሬ ተገምዷል፣ በወፍራም የደም ክር

*          *          *

የተማሪዎችን ያስቀውን ግጥም እንዲያነቡት ያድርጉና በሴላ ክፍለ ጊዜ ቀጣዩን ግጥም ያንብቡላቸው:: የእርስዎንም የማዳመጥ ጥያቄም ያሰፎቸው::

በዚህ የጭንቅ ወቅት ምጧ እንዲህ ሲጠና

አዋላጅ ፈልጉ  ሳይጠናባት ገና

ለምን ካላችሁኝ

ከራስጌም ከግርጌም  ቢታጣ እንኳ ትራስ

ይጋረዳል እንጂ  ይፈናቀላል ወይ፣ ያልጠነከረ አራስ

አደራ!

አደራ!

አንቺ ብቻ ታገሽ

አንገት እንዳትደፊ ከቶ እንዳትይ ዘንበል~ መጠንከር ነው ደጉ

በጨርቅ ተከልለሽ~ እስኪሰዋ ድረስ ~ የመስዋዕት በጉ

ቢያድለን ኑሮማ ~ ሀገር ጨርቃችን ናት~ ሁሉን ተሸካሚ

የውስጣችን ጉድፍ~ ሸፍና ያስቀረች ~ ዛሬም አስታማሚ

አዎ ሀገር ጨርቃችን ናት

እንደ እፉኝት ልጆች~ ገመናዋን ሸፋኝ ~ማብቀል የተሳናት

የመጣው የሄደው ~ ቆርጦ ዕጣ ሊጣጣል ~ ሰርክ የሚመኝላት

ሀገር ጨርቃችን ናት።

(ገብረ ክርስቶስ ደስታ። 1963። መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የተወሰደ)

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ውይይት ያደርጋሉ።
- ግጥሞችን በቃል ይናገራሉ።
- በታሪኩ ውስጥ የተገለጹትን የግጥሙን ገጸባህሪያት ይገልጻሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የግጥሙን ጭብጥ መለየት ።
- ግጥሞችን በቃል በመያዝ መናገር ።

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

መጽሐፉ የተማሪዎቹን አዳምጦ የመረዳትና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎታቸውን በሚያዳብር መልኩ የተደራጃ ቢሆንም እርስዎ የሚያዘጋጁት ተጨማሪ መልመጃ የግንዛቤ፣ ያስተሳሰብና ተግባራዊ ባሕርያትን በአራቱም ክሂሎች አማካኝነት በቅንጅት ማስተማርና ማዳበር በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም፤

- ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ወደ ተፈጥሮኣዊ የቋንቋ አጠቃቀም ያመራል።

- ሁሉም ተማሪዎች በቋንቋ ክሂሎች ላይ ሚዛናዊና ሁለንተናዊ ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
- የተማሪዎችን ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ይጨምራል፡፡
- የአዕምሮ እድገትን ያፋጥናል፡፡
- በቡድንና በጥንድ በሚሰሩ ተግባራት ላይ ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል፡፡
- ቋንቋ የመማር እድላቸውን ያሰፋል፡፡

የክፍሉን ተማሪዎች ስውይይት ምቹ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም ግጥሞችን አንብበው በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚከሰቱ ግድፈቶችን ያርሙ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## የግጥም ጥግ

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የግጥም ጥግ የሚለውን አጭር ግጥም አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ፡፡
- በምንባቡ የቀረቡ ግጥሞችን ይተነትናሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የግጥሙን ጭብጥ መገንዘብ ፡፡
- የግጥሙን ጭብጥ መተንተን፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ቀደም ሲል በተለያዩ ምዕራፎች ሥር በተገለጸው ንባብን የማስተማሪያ ዘዴ በመጠቀም በመጽሐፉ የቀረበውን ምንባብ እንዲያነቡና ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያደርጉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- አጫጭር ግጥሞችን ይጽፋሉ፡፡
- የግጥሞችን ሀሳብ አደራጅተው ይተነትናሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- አጫጭር ግጥሞችን መጻፍ፡፡
- የግጥምን ሀሳብ መተንተን፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

የመግቢያ ክፍላችን በሚለው ርዕስ አጭር ግጥም ጽፈው ለክፍል ተማሪዎች ያነባሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሰባት፡ ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- በግጥሙ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይለያሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘት

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺዎችን መለየት፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

የግጥም ቃላት ከዝርው ጽሑፍ ቃላት በቅርጻቸው፣ በፍቻቸውና በአጠቃቀማቸው የሚለዩ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ግጥም እንዲጽፉ በማድረግ ያሰሯቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- የግጥም ቃላት ከሌላው ጽሁፍ ቃላት እንዴት እንደሚለዩ ይገልጻሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘት

- የግጥም ቃላትን ፍች መለየት፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

የግጥም ቃላት ፍች መለያየት እንዴት እንደሚከሰት የተለያዩ ግጥሞችን በማምጣትና በማንበብ ያሳዩአቸው፡፡

### መርጃ መሣሪያዎች

- አጭርና ረዥም ልቦለዶች
- ግጥሞች
- መጣጥፎች
- ጥናታዊ ጽሑፎች

### ግምገማ

- የአዳመጡትን ምንባብ መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡
- በንግግር ተግባራት መሳተፋቸውን አቀራረባቸውን በክፍል ውስጥ መመልከትና ማረጋገጥ፡፡
- በንባብ ክፍል የቀረበውን ግጥም አንብበው መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡
- ግጥም አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን የጻፉትን በማረም ማረጋገጥ፡፡
- አጭር ግጥም መጻፋቸውን ማስታወሻ ደብተሮቻቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፡፡
- በግጥማቸው ውስጥ ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀም መተግበራቸውን ግጥም በማጻፍና በማረም ማረጋገጥ፡፡

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍለ ትምህርት አራት: ፎሕፊት

ህመምሽን ታመው ፣ ስቃይሽን ተጋርተው
ትንሳኤሽን ሊያዩ ፣ መቃብርሽን ከበው፡፡
ለሚጠባበቁት ፣ ዛሬ ብርሃን ነው፡፡
የትንሳዔሽ ብስራት ፣ከጉባ ተራራ
ጨለማውን ገፎ ፣ ብርሃን ሊያበራ
ማታ ፈልቋልና ፣ የአባይ ግድብ ጮራ፡፡

(ሃማኖት አዘነ:: 2013::)

### የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

ውድ መምህር/ት፣
ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ለመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ: አንድነትና ብዝሃነት (8 ክፍለ ጊዜ )

## ርዕስ: አንድነትና ብዝሃነት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩትሁ በኋላ፦

- ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ተነስተው የአካባቢያቸውን ማህበራዊ አውድ ይገልጻሉ::
- ያዳመጡትን ጽሑፍ ወደ ንግግርና ውይይት ለውጠው ያቀርባሉ::
- የክፍል ውስጥ ንግግራቸውን ከጓደኞቻችው ንግግር ጋር በማነጻጸር ልምድ ይለዋወጣሉ::
- በመምህሩ/ሯ ወይም በተጋባዥ እንግዶች የሚቀርቡ ንግግሮችን ይተነትናሉ::
- የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ተጠቅመው መረጃዎችን ይናገራሉ::
- በተለያዩ ይዘቶች ላይ ጽሑፎችን ከአዘጋጁ በኋላ ከጓደኞቻቸው ሥራ ጋር ያወዳድራሉ::
- የጽሕፈት ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ::
- ሲያነቡ ያገኟቸውንና ያዳመጧቸውን አዳዲስ ቃላት ተጠቅመው ድርሰት ይጽፋሉ::

### ክፍለ ትምህርቶች

#### ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

## አንዱ ለሌላው ምንድን ነው?

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- "አንዱ ለሌላው ምንድን ነው?" በሚል ርእስ መምህሩ/ሯ የሚያነቡላቸውን ጽሑፍ በማዳመጥ ማስታወሻ ይይዛሉ::
- በሚነበቡ ጽሑፎች ላይ ውይይት ያካሂዳሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የቀረቡ ምንባባት ማዳመጥ ::
- በቀረቡ ምንባቦች ላይ ሀሳብ መስጠት::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት!

ማዳመጥን ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች የምእራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱና ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል የክፍለ ትምህርቱን ርዕስ በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም “አንዱ ለሌላው ምንድን ነው?” በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በጥሞና እንዲያደምጡና ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግዎን አይዘንጉ፡፡ አሁን ከዚህ በታች የቀረበውን ጽሑፍ ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማ በሚችል ድምጽ በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በእናንተ እይታ አንድነት ማለት ምን ማለት ነው? መልሳችሁን ለጓድኞቻችሁ ንገሩ፡፡
2. ስለብዝሃነት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## አንዱ ለሌላው ምንድን ነው?

በዚህ ርዕስ ውስጥ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል አንድነትና ብዝሃነት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ሁለቱም ተቃራኒ ቢመስሉም የሚያስተሳስራቸው የጋራ ጠባይ አላቸው፡፡ ሁለቱም እንከን አለባቸው፡፡ ይህን እንከን ተከትሎ ኣንዳንዶቹ አንዱን በሌላ ውስጥ ማየት አይፈልጉም፡፡ በሁለቱ መካከል በሐሳብ በተሰራ የልዩነት ግድግዳ አንድነትን ከወዲህ፤ ብዝሃነትን ደግሞ ከወዲያ ማዶ ያስቀምጣሉ፡፡ በእነርሱ እምነት አንዱ በሚገኝበት ቦታ ሌላኛው መኖር ወይም መገኘት አይችልም፡፡ ፍላጎታቸው አንዱን በመወገን ሌላውን አዳክሞ ይመስላል፡፡

የተወሰኑ ዜጎች አንድነትን ያንቆለጳጵሳሉ፤ ብዝሃነትን ግን ያንኳስሳሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ስለ ልዩነት እንጂ ስለአንድነት ማሰብ አይመቻቸውም፡፡ ለምን ይሆን ብዙ ኢትዮጵያዊያን ከሁለቱ ስለአንዱ እንጂ ስለሁለቱም አፋቸውን ሞልተው መናገር የሚፈሩት? ለምንድን ነው አንዱን በመፍቀድና በማቀፍ ሌላውን መንቀፍና አለመፍቀድ የተፈጠረው? በግልጽ የሚታየውን ልዩነት መደበቅ ወይም የሌለ ማስመሰል ምንድን ነው ፋይዳው? አንድነትን በጭፍን መግፋትስ ምንና ማንን ይጠቅማል? ሰዎች በአንድነት ውስጥ ልዩነቶች መኖራቸውን፤ በልዩነቶች ውስጥ አንድነት መኖሩን መረዳት ለምን ይሳናቸዋል? አንድነትን ከፍ አድርጎ ልዩነትን ዝቅ ማድረግ የተፈጠረውስ ለምንድን ነው?

አንድነትም ሆነ ብዝሃነት በተፈጥሮ ችግር የላቸውም፡፡ በአግባቡ ካልተያዙ ወይም በሰዎች አስተሳሰብ፤ ፍላጎትና ትርጉም ግን በቀላሉ ወደ ችግር መቀየር የሚችል ባሕርይ አላቸው፡፡ በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ጉዳይ እምብዛም ሲቸገር አልታየም፡፡ ኢትዮጵያ የብዝሃነት መናኸሪያ መሆንዋ ይታወቃል፡፡ ይህ በሀገራችን የተፈጥሮ ሥርዓት፤ በሕዝቦች ሕይወትና ግንኙነት ውስጥ ይታያል፡፡

መምህር /ት ! ንባቡን እዚህ ላይ ይግቱና ከላይ በቀረቡት አንቀጾች የተነሱ ጥያቄዎችን እያነሱ ይጠይቋቸው፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በብዝሃነትና በአንድነት ላይ ያላቸውን አመለካከት ይፈትሹ::

2. ንግግራቸው የተሟላ ሀሳብ የሚሰጥ እንዲሆንና ስሜታቸውን እንዲገልጹ ይደግፏቸው::

የሚያፍን ኃይልና ሥርዓት ባለበት ሀገር ውስጥ ላለመታፈን (በነፃነት፤ በሥልጣን፤ በመብትና በጥቅም ጥያቄ ላይ) የሚንቀሳቀስ ኃይል ይፈጠራል:: ብዝሃነት በባሕርይው ለተቀናቃኝ መፈጠር ምቹ ነው:: በተለይ ጨቋኝ ሥርዓት በሚገዛው ብዝሃዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ተቀናቃኝነት ብሎም ጠላትነት፤ አመፅ ብሎም ጦርነት ይከሰታል:: ገዢዎች የተቀናቃኝን አቅም የሚያዳክም ወይም የሚያጠፋ አካላዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ጥቃት ይፈፅማሉ:: የራሳቸውን ተቀባይነት ለማጠናከርና ተቀናቃኝን ድጋፍ ለማሳጣት የሚያስችሉ አስተሳሰቦችን ሕዝብ ውስጥ ያሰርፃሉ:: የጭቆና ሰለባ የሆኑ ወገኖች በበኩላቸው የገዢዎችን አስተሳሰብ፤ እምነትና የመጨቆኛ ኃይል ለመስበር መታገል የግድ ይሆንባቸዋል:: ስለእውነት አንድነት ያለ ልዩነት ኖሮ አያውቅም:: ልዩነትም ያለ አንድነት ልዩነት አይሆንም:: አንዱ ያለ ሌላው ትርጉም የለውም፤ ሕልውናም አይኖረውም:: ያለ ልዩነት እንዴት ስለአንድነት ማውራት ይቻላል? ያለ አንድነት እንዴት ስለልዩነት ማሰብ ይቻላል? ባጭሩ አንዱ ያለ ሌላው አይታሰብም::

ብዝሃነት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ስራ ውጤት ነው:: እያንዳንዱ ሰው የት፤ መቼና ከማን እንደሚወለድ መወሰን ወይም መምረጥ አይችልም:: ጥቁር ወይም ነጭሆኖ መወለድ የራሱ ምርጫ ሳይሆን የተፈጥሮ ውሳኔ ነው:: ሰው ሰራሽ የሚሆነው ደግሞ ሰው የሚፈልገውን የትምህርት ዓይነት፤ ሙያ፤ የመኖሪያ ሥፍራ፤ እምነት፤ ርዕዮተ ዓለምንና የመሳሰሉትን መርጦ መሆን ወይም መከተል ይችላል::

የሰው ልጅ ብዝሃነት ዘርንና ቋንቋን፤ እምነትን (ሃይማኖትን) እና ባሕልን፤ አመለካከትንና እሴትን፤ ርዕዮተ ዓለምንና ሥነ-ልቡናን መሠረት አድርጎ በመፈጠሩ ከማንነት ጋር የተያያዘ ነው:: በፖለቲካና በርዕዮተዓለም ትግል አኳያ በተለይ በብዝሃ ሕብረተሰብ ውስጥ የማንነት ጉዳይ እጅግ በጣም ቁልፍ ነው::

## ክፍለ ትምህርት ሁለት: ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ውይይት ያደርጋሉ::
- ስለተነበበው ጽሑፍ ይዘት ይናገራሉ::
- በጽሑፉ ውስጥ የተገለጹ የምንባቡን ይዘቶች ይገልጻሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ውይይት ማካሄድ::
- ስለአንድነትና ብዝሃነት ንግግር ማድረግ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

መጽሐፉ የተማሪዎቹን አዳምጦ የመረዳትና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በሚያዳብር መልኩ የተደራጀ በመሆኑ እርስዎ የሚያዘጋጁት ተጨማሪ መልመጃ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማርና ማዳበር በእጅጉ ይጠቅማል:: የርስዎ ዝግጅትና አቀራረብ ወሳኝ መሆኑ ቢታመንበትም ሥራዎን ለማገዝ ይረዳ ዘንድ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፤ ስለዚህ መጀመሪያ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው:: ምንባቡን ካዳመጡ በኋላ፣ ደግሞ መማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የሚገኙ የንግግር መልመጃዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ::

### ክፍለ ትምህርት ሦስት: ንባብ

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ::
- በምንባቡ የቀረቡ ጭብጦችን ያብራራሉ::

### የክፍለ ትምህቱ ዝርዝር ይዘቶች

- አንድነትና ብዝሃነት፦ የተፈጥሮ መንታ ገጽታዎች የሚለውን ምንባብ ማንበብ::
- ጭብጦችን መለየት::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ንባብ የአንድን ጽሑፍ መልዕክት በመከተል ምላሽ ለመስጠት የምንሞክርበት አዕምሯዊ ተግባር ነው:: ተግባሩም ግላዊ ነው:: ስለዚህ መምህር/ት! ተማሪዎችን ንባብ በሚያስተምሩበት ወቅት በለሆሳስና በግል እንዲያነቡና እያንዳንዳቸው የሚሰሩትን ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ከዚህ ሌላ ንባብ ሰፊ ክሂል በመሆኑ የሚያልፍባቸው ደረጃዎች አሉት:: እነዚህ ደረጃዎች በምእራፍ አንድ በስፋት ለማብራራት እንደተሞከረው ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ናቸው:: ሁሉም ደረጃዎች አንብቦ መረዳትን ለማፋጠን የራሳቸው የሆነ ጉልህ ድርሻ አላቸው:: ስለዚህ መምህር/ት፣ ተማሪዎችን ንባብ ለማስተማር በሚዘጋጁበት ወቅት ከላይ የተጠቀሱትን ደረጃዎች ጠብቀው እንዲተገብሩ ይመከራል::

### ክፍለ ትምህርት አራት: ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለአንድነትና ብዝሃነት የተረዱትን ይጽፋሉ::
- የምንባቡን ሀሳብ ከተረዱ በኋላ በጽሑፍ ያብራራሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- አጫጭር ጽሑፎችን መጻፍ::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

የጽሕፈት ክሂል ተማሪዎች በፍጥነት በቀላሉ የሚተገብሩት አይደለም:: የረዥም ጊዜ ሂደት ውጤት ነው:: በርካታ ተግባራትን ማከናወን ይጠይቃል:: ስለዚህ የጽሑፍ መልመጃ ለተማሪዎች በሚቀርብበት ወቅት ይህ ባህሪው ግምት ውስጥ መግባት አለበት:: ጽሕፈት በአብዛኛው ተግባራዊ ልምምድን የሚሻ ክሂል ነው:: ስለዚህ የጽህፈት ክሂልን ለማበልጸግ ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል ማከናወን ይጠበቃል:: ተማሪዎች የተለያየ መጠን ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮች በራሳቸው አገላለጽ እያዋቀሩ፤

- እንዲጽፉ ማበረታታት፤
- ተማሪዎች በአንድ ሐሳብ የተደራጀ አንቀጽ እንዲጽፉ ማበረታታት፤
- ተማሪዎች ለምን እንደሚጽፉ መግለጽና በቂ ማብራሪያ መስጠት፤
- ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርእሰ ጉዳይ እንዲመርጡና እንዲያውቁ ማድረግ፤ወዘተ. ናቸው::

ውድ መምህር/ት፤

የተማሪዎችዎን የእጅ ጽሑፍ መሻሻሉን መከታተልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ማለማመድ እንደቀላል ነገር ገምተው ለተማሪዎችዎ መተው የለብዎትም::

### ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን መጠቀም::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ውድ መምህር/ት!

አዳዲስ ቃላትን ለማስተማር ቅደምተከተሉ ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም መልካም ነው::

- መዝገበ ቃላትን መጠቀም
- ምሳሌ እየሰጡ በአውድ ማብራራት
- ቃላትን በተዛምዶ መንሰራፋትን መመልከት
- በቃላት መካከል ያለን ዝምድና ማስለየት፡-
- የፍች ተዛምዶ (ቃላት በሚሸከሙት መልዕክት ረገድ)
- የአውድ ተዛምዶ (ስለአንድ ነገር በሚገልፅ አንቀጽ ውስጥ አብረው መሰለፍ)
- ቃላቱን ተጠቅሞ ማውጣጣት
- ከገቡበት አውድ ተነስቶ መገመት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- የቃላት ምስረታ ህግጋትን ተጠቅመው ቃላት ይመሰርታሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- የቃላት መመስረቻ ድምጾችን በመጠቀም ቃላትን መመስረት::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት!

የተማሪዎች የቃላት እውቀት እንዲዳብርና በቋንቋው ቃላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በቅድሚያ በመጽሐፋቸውና በመምህር መምሪያው ከቀረቡ ምንባቦች ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ይሰበስባሉ:: ከዚያም ተማሪዎች ከዚህ በታች በሰፈረው መንገድ እንዲጠቀሙባቸው ቢያደርጉ የተማሪዎችን የቃላት እውቀትና የአጠቃቀም ችሎታ ሊያዳብሩ ይችላሉ::

1. ማቅረቢያ
    - ምልልስ

- የተለያዩ ሁኔታዎችን በመጠቀም
- ማብራሪያ መስጠት
- ገለፃ ማድረግ

2. ማውጣጣት
3. ገለፃ
4. አፍዕሞ ማፍለቅ
5. ከአእምሮ ማፍለቅ

## መርጃ መሣሪያዎች

1. በተለያዩ  ርዕሶች ላይ የተጻፉ ጽሑፎች
2. ጋዜጦች
3. መጣጥፎች
4. ጥናታዊ ጽሑፎች

## ግምገማ

- የአዳመጡትን ምንባብ መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡
- በንግግር ተግባራት መሳተፋቸውን አቀራረባቸውን በክፍል ውስጥ መመልከትና ማረጋገጥ፡፡
- በንባብ ክፍል የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው መረዳታቸውን በቃል መጠየቅና ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት ማረጋገጥ፡፡
- የመጻፍ ችሎታቸውን ለማረጋገጥ ጽሑፉን አሳጥረው እንዲጽፉ በማድረግ ሥራቸውን መገምገም፡፡
- የመጻፍ ልምዳቸውን ለማዳበር አጭር ድርሰት በማጻፍ መመልከትና አስተያየት መስጠት፡፡
- የቃላት አጠቃቀም ችሎታቸውን እንዲዳብር ከላይ ቃላትን ለማስተማር የቀረቡ መነሻ ዘዴዎችንና የእርስዎን ልምድ በመጨመር መልመጃዎችን በማሠራትና በማረም ማረጋገጥ፡፡
- የቃላት አመሰራረት ሕግጋትን ተከትለው ቃላት መመስረታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

ትዕዛዝ አንድ፡- እነውነት/ሀሰት

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. ሀሰት
6. እውነት
7. ሀሰት
8. እውነት

ትዕዛዝ ሁለት፡ ምርጫ

1. መ
2. ለ
3. ሐ
4. ሠ
5. ሐ
6. ሀ

## የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

መምህር/ት፣

ይህን ምዕራፍ አጠናቀው ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ለመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ አስር፡ ስደት (8 ክፍለ ጊዜ)

## ርዕስ፡ ስደት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩችሁ በኋላ፦

- ከሚያዳምጡት አሀድ ተነስተው የአካባቢያቸውን ማህበራዊ አውድ ይገልጻሉ፡፡
- ቀለል ባሉ ንግግሮችና ውይይቶች ላይ ይሳተፋሉ፡፡
- ለተለያዩ ሀሳቦች የማጠቃለያ ሀሳብ ያመነጫሉ፡፡
- በተለያየ ማህበራዊ አውድ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ ይዘቱን ይተነትናሉ፡፡
- መምህሩ የሚጠቁሟቸውን አጋዥ መጻሕፍት ያነባሉ፡፡
- አጭር ጽሑፍ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ያነባሉ፡፡
- በተመረጡ ርዕሶች ላይ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- በዓረፍተ ነገሮች ላይ ትክክለኛ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡
- የቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ሰዋስዋዊ ትክክለኝነቱን የጠበቀ አንቀጽ በመጻፍ ያሳያሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርቶች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ስደትና መከራው

#### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- “ስደትና መከራው” በሚል ርእስ የሚነበብላቸውን  ጽሑፍ በማዳመጥ ማስታወሻ ይይዛሉ
- በሚነበበው ጽሑፍ ላይ ውይይት ያካሂዳሉ፡፡

#### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ፡፡
- ካዳመጡት ተነስተው ስለ ጭብጡ ውይይት ማድረግ፡፡

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

የማዳመጥን ክሂል ለማለማመድ የሚከተሉትን አቀራረቦች በቅደም ተከተል ተግባራዊ ማድረግ ይረዳል፡፡

- ማስተዋወቅ (ስለሚደመጠው ጉዳይ ራስን ለማስተዋወቅ የሚዘጋጁበት ነው፡፡ ዋና ዓላማውም ተማሪዎች በሚያዳምጡት ጉዳይ ላይ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው)፡፡
- የግንዛቤ ክንውኖችን መቆጣጠር (ተማሪዎቹ አድምጠ የመረዳት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤ ያልተሟሉ ሐሳቦችን አሟልተው ያቀርባሉ፤ ያዳመጡትን በራሳቸው አባባል መግለጽ ይችላሉ)፡፡
- ተማሪዎች በመተንበይ ያዳምጣሉ፡፡

ውድ መምህር/ት!

ማዳመጥን ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች የምእራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱና ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል የክፍለ ትምህርቱን ርዕስ በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም "ስደትና መከራው" በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ ሊያነቡላቸው እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በጥሞና እንዲያደምጡና ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግዎን አይዘንጉ፡፡ አሁን ከዚህ በታች የቀረበውን ጽሑፍ ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማ በሚችል ድምጽ በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1.ስደት ስለሚያስከትለው መከራና እንግልት የምታውቁትንና የሰማችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

2.ሰው ለምን ሀገሩን ጥሎ ይሰደዳል? ምክንያቶችን ዘርዝሩ፡፡

### ስደትና መከራው

ስደትን መከራ ለመረዳት የግድ ተሰዳጅ መሆን አይጠይቅም፡፡ ይህን ለማወቅ በዓለማችን ላይ እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት ጥቂቱን በምሳሌነት ማየት ይቻላል፡፡ የምንኖርባት የአፍሪካ አህጉር ደካማ መንግስት ያላቸውንና መንግስት አልባ ሀገራት፤ ስደተኞችን የሚያባርሩ ሀገራት፣ ስደተኛ ላለማስገባት የሚከላከሉ ሀገራት ወዘተ በምሳሌነት እያነሳን እንነጋገር፡፡ ምሳሌ፡- ሶማሊያ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የላትም፡፡ ሊቢያ የአሸባሪዎች፤ የወሮበሎችና የዘራፊዎች መናኸሪያ ሆናለች፡፡ በየመን በጦርነት፤ በረሐብና ኮሌራ ሚሊዮኖች ይረግፉባታል፤ ይራቡባታል፤ ይታመሙባታል፡፡ ከኬንያ እስከ ደቡብ አፍሪቃ የተዘረጋው መስመር የአውሬ፤ የዘራፊና አጭበርባሪ መፈንጫ ነው፡፡

አረቦች ስደተኛ ያባርራሉ፡፡ አሜሪካኖችና አውሮፓዊያን ሥደተኛ እንዳይገባባቸው በራቸውን ይዘጋሉ፡፡ የገባውን ወደየሀገሩ ያግዛሉ፡፡ ኢትዮጵያዊያን ግን ወደ ሁሉም ሥፍራ፤ በሁሉም አቅጣጫ ይሰደዳሉ፡፡ ካሰቡት ሳይደርሱ ይሞታሉ፤ ይገደላሉ፤ ይደፈራሉ፤ ይገረፋሉ፡፡

የካቲት 2007 የአይ.ኤስ.ኤስ አሸባሪዎች ናቸው የተባሉ ታጣቂዎች ሊቢያ የገቡ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን በካራ ገዝግዘው መግደላቸው፤ ከአዲስ አበባ እስከ ዋሽግተን፤ ከለንደን እስከ ዱባይ የሚገኝ ኢትዮጵያዊን በቁጣ፤ ሐዘን፤ አሳድሞ ነበር:: ኢትዮጵያውን ግን ዛሬም ወደ ሜድትራኒያን ባሕር በገፍ ይሰደዳሉ::

በ2004 ታንዛኒያ ውስጥ በአንድ የጭነት መኪና ኮንቴነር ውስጥ የታጨቁ አርባ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች በሙቀት ተቀቅለው ማለቃቸው ሲሰማ ያለዘነ፤ ያልደነገጠ፤ ቀሪዎችን ያላስጠነቀቀ አልነበረም:: በ2002 ከሶማሊያ የወደብ ከተማ ወደ የመን ሲቀዝፉ የተሳፈሩባት ጀልባ ሰምጣ በሙቶ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንና የሶማሊያ ዜጎች ማለቃቸው ለቀሪዎች ጥሩ ማስጠንቀቂያ በሆነ ነበር:: ግን አልሆነም:: ኢትዮጵያዊያን በስደተኛ ወገኖቻቸው ሞት አዝነው ሳያበቁ የሌሎች ስደተኞችን መገደል፤ መደፈር፤ የሰውነታቸውን መተልተል፤ በረሐ ላይ መቅረት፤ ባሕር ውስጥ መስመጥ ይሰማሉ:: ግን ሌሎች ይሰደዳሉ::

መምህር/ት! ንባቡን እዚህ ላይ ደግቱና ከላይ በቀረቡት አንቀጾች መነሻነት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ውይይት በማድረግ ተማሪዎች የመፍትሄ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው::

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ኢትዮጵያዊያን በስደተኛ ችግሩን እየሰሙና እያወቁ ስደትን የማያቆሙት ለምንድን ነው?
2. ስደትን ለማቆም ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ሶማሊያ፤ ኬንያ፤ ሱዳን፤ ደቡብ አፍሪቃ፤ የመን፤ ሊቢያ፤ግብፅ፤ እስራኤል፤ሌላው ቀርቶ ሮምና ካሌ የሚገኙ ስደተኞች የሚደርስባቸውን በደል እና ግፍ ዘግናኝነት ይዘረዝራሉ:: ከችግሩ ለመላቀቅም ድጋፍ ይማፀናሉ:: ሌሎች ግን ይሰደዳሉ::

በአንድ ወቅት ወደ የመን ይቀዝፉ የነበሩ 280 ኢትዮጵያዊያንና ሶማሊያዊያን ስደተኞች በአሻጋሪዎቻቸው ከጀልባ ተወርውረው ባሕር ውስጥ ሰምጠዋል::

(ነጋሽ መሐመድና ልደት አበበ:: 2017::)

## ክፍለ ትምህርት ሁለት:- ንግግር

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ውይይት ያደርጋሉ::
- ስለተነበበው ጽሑፍ ይዘት ይናገራሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- ስለስደት ምንነትና አስከፊነት ንግግር ማድረግ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

በክፍል ሁለት መናገር በሚለው ክፍል ስር የቀረቡትን ተግባራት ለማከናወን አመቺ ነው በሚሉት መንገድ ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ይመድቧቸው፡፡ ከዚያም ጥያቄዎችን ለየቡድኑ በመስጠት ቃላዊ ተግባቦት እንዲያከናውኑ ይርዷቸው፡፡ ንግግራቸው አጭር እንዳይሆን የተግባቦት ማራዘሚያ ቃላትን ማለትም፦ እሺ! ከዚያስ? በምን ምክንያት እንዲህ የሆነ ይመስላችኋል? ወዘተ. እያሉ ሰፊ ንግግር በማድረግ ሀሳባቸውን እንዲያብራሩ ያግዟቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## ስደት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስደት በሚለው ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ፡፡
- በምንባቡ የቀረቡ ጭብጦችን ይጽፋሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- ስደት የሚለውን ምንባብ ማንበብ፡፡
- ጭብጦችን መለየት፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

በንባብ ትምህርት አቀራረብ ጊዜ ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች

- በመማሪያ ክፍል ውስጥ ድምፅን ከፍ አድርጎ ከማንበብና ተማሪዎችንም ከማስነበብ መቆጠብ፤
- የንባብ ትምህርቱ ወደቃላት ትምህርት እንዳይለወጥ በፅሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ ለማስተማር አለመሞከር፤
- በተወሰኑ የጥያቄ አይነቶች (እውነት ውሸት፣ ምርጫ...) ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ የተለያዩ የጥያቄ አይነቶችን ማካተት፤
- የሚቀርቡት ጥያቄዎች እንዲዳብር የሚፈለገውን ክሂል (ንኡስ ክሂል) በሚገባ ማዳበር የሚችሉ መሆናቸውን በእርግጠኝነት ማወቅ፤

- ያለግንዛቤ ቃላትን በማዛመድ ሊመለሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን አለመጠየቅ፤
- ተማሪዎቹ የቃላት ፍች እንዲገምቱ ማበረታታት የቃላት እውቀታቸውን ያዳብረዋል
- ተማሪዎች ሲያነቡ የማይረዷቸውን ቃላት ትኩረት እየሰጡ እንዳይሄዱ ማስገንዘብ፤
- ትኩረቱ አንብበው በመረዳትና ባለመረዳት ላይ ስለሆነ ምንባቡን ተረድተው መለስ ሲሰጡ የሰዋስው ግድፍት ቢኖር ስህተቱን ከመግለፅ መቆጠብ፤
- የግድ የተሟላ ዓረፍተነገር ካልመለሳችሁ ብሎ አለማስጨነቅና በንግግር መልክ የሚቀርቡ አጫጭር መልሶችንም ቢሆን መቀበል::

## ክፍለ ትምህርት ስራት: ጽሕፈት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለስደት የተረዱትን ይገልጻሉ::
- የምንባቡን ሀሳብ ከተረዱ በኋላ ሀሳባቸውን ለሌሎች ያጋራሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች

- አጭር ጽሑፍ መጻፍ::
- ሀሳብን በጽሑፍ ማጋራት::

### የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

በምዕራፍ አራትና አምስት የተሰጡትን ማብራሪያዎችና የእርስዎን ልምድ በመከተል ጽሕፈትን ማስተማር ይቻላል::

## ክፍለ ትምህርት ስምንት: ቃላት

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- ድርብ ቃላትን ይጽፋሉ::

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- በዓረፍተ ነገር ምስረታ ወቅት ድርብ ቃላትን መጠቀም::

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ቀደም ሲል  በተመለከቱ ምዕራፎች የቀረቡ አቀራረቦችን በመከተል ቃላትን ማስተማር ይቻላል።

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት

- በተቀናጀ መንገድ ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።

### የክፍለ ትምህርቱ ይዘት

- ሰዋስዋዊ ቅንጅታቸው የተሟላ ዓረፍተ ነገር መመስረት።

## የክፍለ ትምህርቱ አቀራረብ

ቀደም ሲል  በተመለከቱ ምዕራፎች የቀረቡትን አቀራረቦች በመከተል ሰዋስውን ማስተማር ይቻላል።

### መርጃ መሳሪያዎች

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በመረጃ መሳሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም፣ ጥቂቶቹ ፤

- ስዕሎች
- ግራፎች
- ቻርቶች
- የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆች ወዘተ. ናቸው።

ከእለቱ የትምህር ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን ማገዝና ትምህርቱን በትጋት እንዲከታተሉት ማድረግ ይቻላ

### ግምገማ

- የአዳመጡትን አሀድ መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ ማረጋገጥ፣
- በንግግር ተግባራት መሳተፋቸውን አቀራረባቸውን በክፍል ውስጥ መመልከትና ማረጋገጥ፣
- በንባብ  ክፍል የቀረበውን አሀድ አንብበው መረዳታቸውን በቃል በመጠየቅ  ማረጋገጥ፣
- ጽሑፉን አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን የጻፉትን እርማት ማድረግና ማረጋገጥ፣
- በግልና በቡድን መጻፍ መቻላቸውን መመልከትና ማረጋገጥ፣
- የቡድን ውይይታቸውን ውጤት ማቅረብ መቻላቸውን  ማረጋገጥ፣
- ምሳሌዎችን በመጠቀም ገለጻ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፣

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ትእዛዝ አንድ፡ እውነት/ሀሰት

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሀሰት
6. እውነት
7. ሀሰት
8. ሀሰት

ትእዛዝ ሁለት፡- ምርጫ

1. ሠ
2. መ
3. ለ
4. ሀ
5. ሐ

## የክለሳ ጥያቄዎች አተገባበር

መምህር/ት፣

ተማሪዎች የክለሳ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ስመልሶቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ማጣቀሻዎች


ሀብታሙ ግርማ:: (2011):: የሥነ ጽሑፍ ሰዎችና ሥራዎቻቸው:: አዲስ አበባ::

ሀማኖት አዘነ:: (2013):: ህመምሽ አመመኝ::

ሲሳይ ንጉሱ:: (1978):: ሰመመን:: (ገጽ18_21)፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣አዲስ አበባ::

ብርሀኑ ገበየሁ:: (1999):: የአማርኛ ስነግጥም:: አልፋ አታሚዎች፣ አዲስ አበባ::

ታርቆ ክንዴ:: (2014):: እንግዳ ተቀባይነትና ኢትዮ ጵያዊ አባትነት:: አሚኮ::

ነጋሽ መሐመድና ልደት አበበ:: (2017):: ስደትና መከራው:: በጀርመን ራዲዮ ጣቢያ የተላለፈ::

ከበደ ሚካኤል:: (1999):: ታሪክና ምሳሌ፤ አንደኛ መጽሐፍ:: ሁለተኛ ዕትም:: አዲስ አበባ፡ ሜጋ::

ገብረክርስቶስ ደስታ:: (1963):: የገብረ ክርስቶስ ደስታ ግጥሞች::

ጌታቸው ኃይሌ:: (1993):: ባሕረ ሐሳብ፤ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ::
ሚኒሶታ፤ ኮልጅቪል::

ጌታቸው ገበየሁ:: (2010):: አደገኛ ድራጎችና ዕፆች የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች:: አዲስ አበባ::

ዘሪሁን አስፋው:: (1992):: የሥነጽሑፍ መሰረታውያን:: (የታተመበተ ያልተጻፈ) ፣ አዲስ አበባ::

www.peoplepill.com/people/yetnebersh-nigussie፤ (የተገኘው ታህሳስ 25፣ 2014 ዓ.ም)

www.allfamousbirthday.com/yetnebersh-nigussie/ (የተገኘው ታህሳስ 25፣ 2014 ዓ.ም)

# የፌደራል ቋንቋ የ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት
# የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት

**ምዕራፍ አንድ፡ የሥራ ባህልና ምርት (8 ክፍል ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- ✓ አዳምጠው መረጃዎችን ይናገራሉ።
- ✓ በአዳመጡት መሠረት የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።
- ✓ የሥራ ባህልና ምርት ከሚለው ይዘት ያዳመጡትን ፍሬ ሀሳብ ያብራራሉ።
- ✓ ውይይት ያደርጋሉ።
- ✓ በተመረጡ ይዘቶች ላይ ውይይት ያካሂዳሉ።
- ✓ አውድን መሠረት ያደረገ ንግግር ያደርጋሉ።
- ✓ በሚና-ተኮር ልምምድ ንግግር ያከናውናሉ።
- ✓ ምንባብ አንብበው የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።
- ✓ ሀሳቦችን አፍልቀው ይጽፋሉ።
- ✓ የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ።
- ✓ ቃላት ምንባብን ለመረዳት ያለቸውን አስተዋጽኦ ይገልጻሉ።
- ✓ የቃላትን ቀጥተኛና አውዳዊ ፍችዎች ይሰጣሉ።
- ✓ በቃል ውስጥ የሚገኙ ምእላዶችን ይለያሉ።

| ክሂል | የመማር ብቃት | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| **ማዳመጥ** | በሥራ ባህልና ምርት ያዳመጡትን ወደ ቋንቋ ትምህርት በማምጣት መተግበር። | ስለሥራ ባህልና ምርት የተደረገውን ገለጻ ማዳመጥ<br><br>ጥያቄውችን ማዳመጥ ጅምር ምንባቦችን ያሟላሉ<br><br>በ ሥራ ባህል እና ምርት ላይ ውይይት እና ክርክር ማድረግ | በ ደምጽ እና ምስል የታገዘ ትምህርት<br><br>ግላዊ መማር<br><br>አሳታፊ የ ማዳመጥ ልምምድ | ተማሪውች ያደመጡትን ሁኔታ ይገልጽሉ<br><br>ጅምር ምንባቦችን ካዳመጡት ገላጻ ላይ እንዲሞሉ መጠየቅ<br><br>ከ ካዳመጡት ገለጻ ላይ ቁልፍ ቃላቶችን መጠየቅ |
| **ንግግር** | • ከነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተነስቶ የተለያዩ ንግግሮችን ማድረግ | በመረጃ የተደገፈ ንግግር<br><br>በ ውይይት ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ<br><br>የተለያዩ ሚናውችን ተላብሶ ንግግር ማደረግ | ውይይት<br><br>ቃለመጠይቅ እና የ አቻ ላአቻ ውይይቶች<br><br>የ ቡድን ውይይቶች እና የተለያዩ ሚናው ችን ተላብሶ የመናገር ማስተማር ዘዴ | ተማሪውች ካዳመጡት ንግግር ላይ ተነስትው<br>የምርጫ ጥያቄውችን ይመልሳሉ<br><br>ግላዊ ግምገማ እና የአቻ ለአቻ ግምገማ<br><br>የቡድን ግምገማ |
| **ንባብ** | • አንቀጾችን መተንተን፤ | ጽሁፎችንና መመሪያውችን ማንበብ | ግላዊ ንባብ፡ ገለጻ፡ እና ውይይት | ተማሪውች የጽሁፉን መመርያውች እንዲለዩ መጠየቅ |
| **ጽሕፈት** | • የተለያዩ የደብዳቤ አይነቶችን መጻፍ፤ | የግል ደብዳቤና የሥራ ማመልከቻ መጻፍ<br><br>ስለ ተመረጡ ግለሰቦችና ሃገር ፍቅር ጉዳይ ላይ መጻፍ | የቡድኖች ሥራዎች<br>ስለ ሰዎች፡ ቦታውችና ነገሮች ገለጻ መጻፍ<br><br>የአቻ ለአቻ ውይይቶች | የቡድንና<br>የአቻ ለአቻ ግምገማ<br>ተማሪዎች የጻፉትን በመማርያ ክፍል ውስጥ ያነባሉ እንዲሁም ባቀረቡት ላይ እርስ በርስ አስተያየት ይሰጣጥሉ<br>የዳሽ ሙላ ጥያቄዎች |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ቃላት** | • ለቃላት መዝገበ ቃላዊፍች መስጠት፤ | ቃላትን መጻፍ<br><br>ቀጥተኛ ትርጉም | አሳታፊ የማስተማር ዘዴ<br><br>ተግባር ተኮር የማስተማር ዘዴ | ግላዊና<br>የአቻ ለአቻ ግምገማ<br>ግለ ጽብረቃ |
| **ሰዋስው** | ቅድመ ምዕላዶች በመለየት ማሳየት | ምዕላዶችን | ከ አጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከ ዝርዝር ወደ አጠቃላይ የትንተና ዘዴ | መምህር መር |

## ምዕራፍ ሁለት፡- የሕይወት ክህሎቶች (8 ክፍል ጊዜ)

### የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- በመቅረጸ ድምጽ የተቀረጸ የሕይወት ታሪክ አዳምጠው ጥቅልና ዝርዝር መረጃዎችን ይሰጣሉ።
- በሚያደምጡት ምንባብ ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።
- ማህበራዊ ተራክቦትን ተጠቅመው ንግግር ያደርጋሉ።
- የምንባቡን ይዘት ያብራራሉ።
- አመዛዛኝ አንቀጾችን ይጽፋሉ።
- በ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍቺ ያብራራሉ።
- የአማርኛ የቃል ክፍሎችን ይለያሉ።

| ክሂል | የመማር ብቃት | ይዘት | ስነ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| ማዳምጥ | የግለሰቦችን የሕይወት ልምድ አዳምጠው ማብራራት፤ | ትእዛዛትንና አቅጣጫዎችን ማዳመጥ<br><br>የግለሰቦችን የሕይወት ታሪክ ማዳመጥ<br><br>የተለያዩ የተቀረጹ ታሪኮችን ማዳመጥ | ተማሪዎች ለማዳመጥ ዝግጁ ማድረግ<br><br>የግለሰቦችን የሕይወት ታሪክ በአሳታፊ ማዳመጥ ማቅረብ<br><br>በቴክኖሎጂ የታገዘ ክፍለ ጊዜ ማድረግ | ታላሚ መርሆችን መጠየቅ<br><br>የግለሰቦችን ታርክ መጻፋና ማቅረብ<br><br>ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ |
| ንግግር | • በቃላዊ ተግባቦት ሂደት የሚከናወኑ የማህበራዊ መስተጋብር ህግጋትን መጠቀም፤ | በማህበራዊ መስተጋብር መናገር | የአንድ ለአንድ መስተጋብር<br><br>የተወሰኑ ተማሪዎችን መርጦ በተለያዩ አውዶች ንግግር እንዲያደርጉ መጋበዝ | ለውይይት በቀረቡት ርእሰ ጉዳዮችን እንዲተነትኑ፣ እንዲገልጹና እንዲያብራሩ ማድረግ<br><br>ድህረ ንግግር ጥያቄዎችን መጠየቅ |
| ንባብ | የምንባቡን ይዘት ይዘት መግለጽ፤ | በ21ኛው ክፍለ ዘመን ክሂሎችን አስመልክቶ የሚቀርቡ ምንባቦችን | ዝምታ ንባብ<br>ግለ ንባብ ንባቡን መድገም<br><br>የጋራ ንባብ, የቃላትንና የአረፍተ ነገሮችን ፍች ለማግኘት የቡድ ውይይት | ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችንና በራሪ ወረቀቶችን እንዲያነቡ ቤት ወሰድ ሥራ መስጠት<br><br>የብጤ፣ የቡድን፣እና የክፍል ግምገማ |
| ጽሕፈት | የሌሎችን ጽሑፎች መገምገም፤ | አወዳዳሪና አነጻጻሪ ጽሑፍች<br>መጻፍ፤<br>እያዳመጡ መጻፍ፣ | ችግር ፈች፣ ተግባር-ተኮር፣ አፍላቂ ትምህርት<br><br>ተማሪዎችና መምህሩ በጋራ መሥራት | የፕሮጀክት ሥራ (ሂደታዊና ጠቅላይ) እና የሰዎች፣ የቦታዎችና የነገሮች ገለጻ<br><br>ተማሪዎች መረጃዎችን ሲገልጹና ሲያብራሩ መገብመገም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቃላት | • ያልተሟሉ ዓረፍተነገሮችን በአዳዲስ ቃላትማሟላት፤ | የቃላት እውቀት | አርአያን መሠረት ያደረገ ዘዴን በመጠቀመወ ምልልስ ማድረግ | የቡድን ግምገም |
| ሰዋስው | • የዓረፍተ ነገሮችን ባለቤቶች መለየት፤ | የቃል ክፍሎችን ማስተማር (ስሞች፣ ቅጽሎች፣ ግሶች፣ | ገለጻ፣ ጥያቄና መልስ | በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የቃል ክፍሎችንና ቃላትን መጠየቅ |

**ምዕራፍ ሦስት፡ ሱስና አደንዛዥ ዕጽ (7 ክፍል ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፦**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- በሚያዳምጡት ጽሑፍ መሠረት ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።
- የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም በቅድመ ማዳመጥ ወቅት ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።
- ማህበራዊ መስተጋብርን መሠረት ያደረገ ንግግር ያደርጋሉ።
- በሚና-ተኮር ልምምድ ይሳተፋሉ።
- ተጨማሪ ጽሑፎችን ያነባሉ።
- በሚሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ድርሰት ይጽፋሉ።
- ለሚቀርቡላቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ።
- የሐረግና የዓረፍተ ነገር መዋቅሮችን ለይተው ያሳያሉ።

| ክሂል | የመማር ብቃት | ይዘት | ስነ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| ማዳምጥ | በሚያዳምጡት ንባብ ንበት መነሻነት የዓረፍተ ነገሮችን ትርጉም መለየት፤ | የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን በተለያየ ንበት ማዳመጥ፤ | አሳታፊ ማደመጥን መተግበር | ቅድመ ማዳመጥ፣ ደሚጣ ጊዜና ድህረ ማዳመጥ የሚነሱ ጥያቄዎችን መርዳት |
| ንግግር | ሱስ ስለሚያስይዙ ነገሮች ንግግር በማድረግ<br>የሱስ አስያዥ ነገሮችን የማጠቃለያ ማቅረብ፤ | ሱስ አስያዥ ነገሮችን አስመልክቶ የሚሰሙትንና የሚያደምጡትን አስመልክቶ ንግግር ማድረግ፤<br><br>በተዘጋጁ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ማድረግ፤ | የቡድን ጽብረቃና ውይይት<br><br>ጨዋታ-ተኮርና ተግባር-ተኮር ትምህርት | ተማሪዎች የግል ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ<br><br>የቃልና የጽሑፍ ግምገማ<br><br>አጭር ጥያቄና መልስ ተግባራት |
| ንባብ | • ለምንባቦች መልዕክት ማጠቃለያ መስጠት፤ | በመጽሀፋቸው የቀረበውን ምንባብና ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን ማንበብ | በየግላቸው ማንበብ | የቤት ሥራና ድንገቴ ፈተና ተጨማሪ ምንባቦች ላይ መስተጠት |
| ጽሕፈት | በተመረጡ ርዕሶች በማነጻጸርና በማወዳደር የድርሰት አጻጻፍ ስልት ጽሑፍ ማዘጋጀት፤ | ስለ ሱስ የሚያውቁትንና የሚሰማቸውን ይጽፋሉ | የግል መጻፍ<br><br>በሚጽፏቸው ጽሑፎች ላይ መወያየት | ተማሪዎች አንቀጾችንና ድርሰቶችን እንዲጽፉ ማዘዝ<br><br>ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት መገምገም |
| ቃላት | በክፍል ውስጥ በሚኖር መስተጋብ አዳዲስ ቃላትን በአውድ መጠቀም፤ | ተግባቦታዊ የቃላት አጠቃቀም፤ | ውይይትና መምህር መር አሳታፊ ትምህርት | • የክፍል ውስጥ ተግባራት |
| ሰዋስው | • ጥገኛና ነጻ ሀረጋትን መመስረት፤ | ጥገኛና ነጻ ሀረጋት፤ | ገለጻ፣ የግልና የቡድን ሥራ | የአረፍተነገር አወቃቀርንና የአንቀጽ እንደገና ማደረጀትን መገምገም |

**ምዕራፍ አራት፡- ልቦለድ (8 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- ✓ የሚቀርቡ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በማዳመጥ ይወያያሉ::
- ✓ በልቦለድ ጽሑፎች ዓላማ ላይ ውይይት ያካሂዳሉ።
- ✓ የቀረቡ ቅንጫቢ ጽሑፎችን ጭብጥ ተንትነው ይጽፋሉ::
- ✓ በመምህራቸው የሚነገራቸውን መጽሐፍ በማንበብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።
- ✓ ልቦለዶችን ያነባሉ::
- ✓ ሰፊና ጥልቅ የንባብ ብልሃቶችን በመተግበር መረጃዎችን ይፈልጋሉ::
- ✓ በልቦለድ ውስጥ የቃላትን አጠቃቀም በመጻፍ ያሳያሉ::
- ✓ የልቦለድን ጭብጥና ዋና ዋና ገጸባህሪያት ይለያሉ::
- ✓ ያነበቡትን የልቦወለድ ታሪክ ይተርካሉ።
- ✓ የራሳቸውን አጭር ጽሑፍ ያዘጋጃሉ።
- ✓ ሰዋስዋዊ ግድፈት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክለው ይጽፋሉ።

| ችሎታ | የመማር ብቃት | ይዘት | ማስተማሪያ ዘዴ | የግምገማ ሂደት |
|---|---|---|---|---|
| **ማዳመጥ** | • የተጻፉ አሀዶች በማዳመጥ መወያየት፤ | የተመረጡ ጽሑፎችን ማዳመጥ፣ መግለጽ፣ መተረክ፣ መወያየት | ተሳትፏዊ በሆነ መልኩ ውይይት ማካሄድ፣ማንበብ፣ | በቡድን ውይይት ያካሂዳሉ፣ የውይይት ውጤታቸውን ያንጸባርቃሉ፣ ጽብረቃውን በቡድን ይገመግማሉ ፤በጥንቃቄ የተደራጀ ተግባራትን መፈጸም |
| **ንግግር** | • የቀረቡ ጽሑፎችን ገጸባህሪያትንና ጭብጦችን መገምገም፤ | ረዥም ታሪኮችን መናገር፤ በታሪኩ ውስጥ የተገለጹ ገጸባህሪያትን ደረጃ መግለጽ፣ በእነሱ ላይ ውይይት ማድረግ፣ | ክፍሉን የሚያሳትፍና ንቁ ተሳትፎ/ውይይትማድረግ፤ ማንበብና መወያየት | የቡድን ውይይትና ጽብረቃ ፣ በመምህሩ የተደራጀ ተግባር ፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| **ንባብ** | • በቤት ውስጥ የሚከናዎን የተራዘመ ንባብ ማከናወን፤ | አጫጭር ልብወለዶችን ማንበብ፣በተነበበው ላይ መወያየት፤<br><br>የተመረጡ ምንባብትን ማንበ፤ | በቋንቋንዎች፣በባህሎችና በግል አስተዳደጎች ወዘተ ላይ መወያየት፤<br>የሚያነቃቁጽሑፎችን ወደ ክፍፍል በማምጣት ተማሪዎች እንዲነቃቁ፣ እንዲሳተፉና እንዲወያዩ ማድረግ፤ | የንባብ ችሎታቸውን ለመገምገም የሚያስችሉ የመተግበሪያ ቅጾችን ማዘጋጀት፣<br>በተግባር ሥራ፣በምርጫ ጥያቄ ፣ አጫጭር ፈተናና የቃል ጥያቄን መጠቀም፤ |
| **ጽሕፈት** | • አጫጭር ጽሑፎችን መጻፍ፣ | አጫጭር ጽሁፎችን መጻፍ፤ | በቡድን መጻፍ፤ | የቡድን ግምገማ |
| **ቃላት** | • በክፍል ውስጥ በሚከናዎን መስተጋብር የሚጠቀሟቸውን የንግግር ቃላተ መገምገም፡ | ትክክለኝነትን ማስተማር | መደጋገም፣ መላልሶ ማስታወስ | የክፍል ውስጥ ጽብረቃ |
| **ሰዋስው** | • ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክሎ መጻፍ፤ | ዓረፍተ ነገር መጻፍ | ግለ ትምህርት | የተማሪዎችን ብቃት በመጠየቃና በማየት መገምገም፤ |

የምዕራፍ አምስት:- እንግዳ ተቀባይነት(8 ክፍል ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፦**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- ✓ የማዳመጥ ስልቶችን ተከትለው ያዳምጣሉ።
- ✓ ጭብጥ ተኮር ንግግሮችንና የሰላምታ ልውውጦችን በማዳመጥ ይተነትናሉ።
- ✓ የግል ልምዳቸውን በማወዳደር ይጽፋሉ።
- ✓ የንግግርን ጠቀሜታ በንግግር ይገመግማሉ።
- ✓ የታሪኮችን ማጠቃለያ ይጽፋሉ።
- ✓ የተሰጣቸውን ጽሑፍ  ካነበቡ በኋላ ጭምቅ ሀሳቡን ይናገራሉ።
- ✓ ቃላዊ ንግግር ያድርጋሉ።
- ✓ ስለእንግዳ ተቀባይነት የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን ያነባሉ።
- ✓ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚያሳዩትን የቃል ክፍል ለውጥ ይጽፋሉ።

| ችሎታ | የመማር ብቃት | ይዘት | የማስተማሪያ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| **ማዳመጥ** | • በአካባቢያቸው ስለአለው የእንግዳ አቀባበል መግለጽ፤ | በእንግዳ ተቀባይነት ዙሪያ የሚደመጡትን የተጻፉ ጽሁፎችን አዳምጣችሁ መወያየት፤ | የእርስ በእርስ ንግግርና ማዳመጥን መተግበር፤ አሳታፊ መማር ማስተማርዘዴዎችን መጠቀም፤ | እርስ በእርስ ጥያቄና መልስ በማድረግ መገምገም |
| **ንግግር** | • ስለእንግዳ ተቀባይነት የክፍል ውስጥ ንግግር ማድረግ፤ | ስለእንግዳ ተቀባይበት በምልልስ፣በክርክርና በውይይት መሳተፍ<br><br>በሚሰጣችሁ ርእሰ ጉዳይ ላይ በመመርኮዝ ስለእንግዳ ተቀባይነት ልምድ ለመለዋወጥ የሚያስችል ንግግር ማድረግ፤ | በተመረጡ ርሰ ጉዳዮች ላይ ክፍሉ በሁለት ቡድን ተከፍሎ ውይይት ማድረግ ጽሁፎችን ለጓደኞቻችሁ ማቅረብ፣ የቢጤ መማር ማስተማር ማከናወን፤ | በቡድኑን መሪዎችን የሚሰጡ አስተያየቶች፣ግለግምገማ፣ የንግግርብቃትፍተሻ፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ንባብ** | • ተጨማሪ መጻህፍትን ማንበብ፤ | ተጨማሪ መጻህፍትን ማንበብ<br><br>የተለያዩ  የንባብ ዓይነቶችን መጠቀም፤ | በግልና በተናጠል መማር፤<br><br>መምህር መር ንብብ ማካሄድ | የመምህር እርማት፣ ግለግምገማ፣ አሳታፊ እርማት፤ |
| **ጽሕፈት** | • አያያገሮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችንና አጭር ጽሑፍ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻች ማቅረብ፤ | አያያዥ ቃላትን መጻፍ፤<br><br>ሁሉንም የጽሕፈት ሂደቶች አንቀጽ በመጻፍ መለማመድ፤ | በጋራና በቡድን መጻፍ፤ | በተግባራቱ ልምምድ መገምገም፤በቡድንና በቢጤ መገምገም፤ |
| **ቃላት** | መሰረታዊ ቃላትን በእርስ በእርስ መስተጋብራችሁ መጠቀም፤ | የእለቱ  ውስብስብ ቃላት | የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ቃላትን በውህድ ማስተማር | የቡድን ግምገማ ፣<br><br>የክፍል ሥራ፣<br><br>የቢጤ ግምገማ፣ |
| **ሰዋስው** | • ጥገኛና ነጻ ሀረጋትን መጻፍ፤ | ጥገኛና ነጻ ሀረጋት | ደረጃውን የጠበቀ የቡድን ሥራና ውይይት ማካሄድ፤ | የቋንቋውን ሰዋስው ተከትለው እንዲጽፉ ማድረግ፤ |

# ሁለተኛው ወሰነተ ትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት፦ ባህላዊ ክንውኖች (8 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፦**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- አጠቃላይ እውነታዎችን አዳምጠው ይወያያሉ።
- እያዳመጡ ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን ያወጣሉ።
- በመረጃዎቹ ላይ ሀሰባችውን ይገልጻሉ።
- አዳምጠው ለጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ።
- በሚሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ያደርጋሉ።
- በርስ በርስ ንግግር ይሳተፋሉ።
- በመማሪያ መጽሐፋቸው ያሉ ማስታወሻዎችን አንብበው ይመዝናሉ።
- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተሟላ አንቀጽ ይጽፋሉ።
- በተጨባጭ ርእሰ ጉዳች ላይ ይጽፋሉ።
- የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይለያሉ።
- ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ።
- ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ይለያሉ።

| ክሂል | የመማር ብቃት | ይዘት | ስነ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| ማዳምጥ | የሚያዳምጡትን ጽሑፍ ይዘት መግለጽ፤ | •ሀገር በቀል እውቀትና ባህል አስመልክቶ የሚቀርቡ አሃዶችን ማዳመጥ | •ክፍት ውይይት<br>•ተማሪዎች ራሳቸው ስለ ርእሰ ጉዳዩ ጥያቄ እንዲያነሱ ማድረግ<br>•በጥንድና በትንንሽ ቡድኖች መወያየት | • ተከታታይ የተማሪዎችን ችሎታ መገምገም<br>• ተግባር /ችሎታ-መር ግምገማ |
| ንግግር | • ስለሚያደንቁት ባህ ንግግር ማድረግ፤ | ሰፊ ንግግሮችን አቀናጅቶ በፍጥነት መናገር | • ተማሪዎች ሰፊ የንግግር ስልቶችን እንዲያዳብሩ ማገዝ<br>• | • የህዝብ አስተያየቶችን ሰብስበው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ የቤት ሥራ መስጠት |
| ንባብ | ከሚያነቡት ጽሑፍ ዋና ሀሳቡን ማውጣት፤ | • ለእውቀት ለመጨበጥ የሚያስችል ምንባብ ማንበብ፤ | • መንገድ ጠቋሚ ማስተማሪና የተናጠል ትምህርት | •ታሪኮችን ማንበብና በጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቆ እንደገና መናገር |
| ጽሕፈት | በሚያውቁት ባህል ላይ ተንተርሰው አጭር ጽሑፍ ማዘጋጀት፤ | ባህልን መሰረት ያደረገ ጽሑፍ መጻፍ፤ | የግልና የቡድን ጽሕፈት<br>ራስ መርና መምህር መር ጽሑፍ | ራስን ማረም |
| ቃላት | የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መገንዘብ፤ | የቃላትን ፍች | የግልና የብጤ ንባብ | የብጤ ግምገማ |
| ሰዋስው | ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ማዋቀር፤<br>• | የአረፍተ ነገር ተዋቃሪዎችና ሰዋስዋዊ ህጎች | • ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ በመጠቀም<br>• ነባራዊ ምሳሌዎችን ከነባራዊ አህዶች በመጠቀም | • የአረፍተ ነገር መዋቅሮችን መጠየቅ፣<br>• በአንቀጽ ውስጥ የአረፍተ ነገር የመዋቅር ስህተቶችን ማሰተተካከል |

ምዕራፍ ሰባት፡ አካቶ ትምህርት (8 ክፍል ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፦**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- አዳምጠው ያልተሟሉ አንቀጾችን ይሞላሉ።
- አዳምጠው የራሳቸውን ሀሳብ ይሰጣሉ።
- በተለያዩ ይዘቶች ላይ ንግግር ያደርጋሉ።
- በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ንግግር ያደርጋሉ።
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ ይሰጣሉ።
- ጽሑፍ አዘጋጅተው ያሳያሉ።
- የቃላት ፍች ይሰጣሉ።
- በተወሰነ ርእሰ ጉዳይ ላይ ድርሰት ይጽፋሉ።
- ቅድመ፣ ውስጠና ድህረ ቅጥያዎችን ይለያሉ።
- ሰዋሰዋዊ ህጎችን የጠበቁ መዋቅሮችን ይመሠርታሉ።

| ክሂል | የመማር ብቃት | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| ማዳመጥ | ስለአካቶ ትምህርት የሚነሱ ነጥቦችን ማብሰልሰል፤ | ያላለቁ አንቀጾችን ማዳመጥ<br><br>የቢጤ ግለ ተሞክሮ ንግግሮችን ማዳመጥ | ገለጻውችና ጽሁፎችን ማቅረብ<br><br>በማሚያ ክፍለግዜ መደበኛ ክህሎቶች ላይ ተመስርቶ ሁለት ቡድኖችን መመስረትና ሥራ ክፍፍል ማድረግ | የ ቢጤና የመምህር እርማቶች<br><br>ትንንሽ ቡድናዊ ግምገማዎችና የግል ጽብረቃዎች |
| ንግግር | የምንባብቱን ይዘትን መናገር እና ማብራራት | ከ መለከቱት እና ከተረዱት ላይ መሰረት አድረገው መናገር<br>የተላያዩ ሚናውችን ተላብሶ ንግግር ማድረግ<br><br>ቀድመው በተዘጋጁ ጉዳዮች ዙርያ ንግግር ማድረግ | የቡድን ጽብረቃ እና ውይይት<br><br>ተግባር ተኮር<br><br>አካባቢን በማሰስ መማር | ተማሪውች ሃሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ መጠየቅ<br><br>የቃልና የጽሑፍ ግምገማ<br><br>አጭር የጥያቄና መልስ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ንባብ** | የጸሃፊው ሃሳብ እና አመለካከት መገምገም፤ | ጽሁፎችን እና ደንቦችን ማንበብ | በትብብር መማር | ድንገቴ ፈተናና የክፍል ሥራ |
| **ጽሕፈት** | የጽሕፈት ደረጃዎችን በመግለጽ ጽሑፍ ማዘጋጀት፤ | የተረዱትንና የተገነዘቡትን መጻፍ፤ | ገለጻዎች፣ ውይይቶችና በግል የመጻፍ ክንውኖች | ተማሪውች ሲማሩ በገለጻ ወይም በ ውይይት ወቅት ባልገባቸውና ግልጽ ባልሆነላቸው ጉዳይ ዙርያ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ መጠየቅ |
| **ቃላት** | በ ቅድመገብና ድህረ ቅጥያ መሃከል ያለውን ልዩነት መለየት፤ | ቃላትን መመስረት | በቡድን ውይይት ማድረግ | የመምህር ክትትል |
| **ሰዋ ሰው** | የንግግር ክፍሎችን መለየት፤ | የንግግር ክፍሎች፤ | ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች ላይ ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ | በ በተዋቀሩ አንቀጾች ላይ የ ቃላትና የስርዐተ ነጥቦችን አጠቃቀምን ማረም |

## ምዕራፍ ስምንት:-ሥነ ግጥም(8 ክፍለ ጊዜ)

### የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- ✓ የቀረበውን ግጥም በማዳመጥ ማብራሪያ ይሰጣሉ።
- ✓ የተሰጣቸውን ግጥም ተጠቅመው በግጥሙ ላይ ውይይት ያደርጋሉ።
- ✓ ግጥሞችን በመሰብ ያነባሉ።
- ✓ ስለመማሪያ ክፍላቸው አጭር ግጥም ይጽፋሉ።
- ✓ የሥነግጥም ቃላት አጠቃቀምን ያብራራሉ።
- ✓ ሥነግጥም የሚያካትታቸውን ይዘቶች ይዘረዝራሉ።
- ✓ የቃላትን የፍች ልዩነት ያሳያሉ።
- ✓ እማሬያዊና ፍካሪያዊ ፍች አብራርተው ይጽፋሉ።

| ችሎታ | የመማር ብቃት | ይዘት | ማስተማሪያ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| **ማዳመጥ** | ስለግጥም ይዘት  መወያየት፤ | የግጥም ምንነት/ሀሳብ፤ | ውይይትና ግለጽብረቃ | የቡድን ግምገማ |
| **ንግግር** | በግጥም ቃላት አጠቃቀም ላይ ውይይት ማካሄድ፤ | የግጥም ቃላት፤ | እውናዊ በሆኑ አሃዶች ላይ በመመስረት የሚና ነጠቃ መጠቀም | የቢጤና የቡድን ግምገማ |
| **ንባብ** | ስለግጥም ቃላት ተፈጥሮ ውይይት ማካሄድ፤ | ቀላል ግጥሞችም በቃል ማንበብ፤ | ድምጽን እያሰሙ ማንበብ፣ | የተማሪዎችን ተሰትፎ ያሚጠይቅ የአንብቦ መጻፍ ተግባር መትስጠት |
| **ጽሕፈት** | ግጥም መጻፍ፤ | ግጥም መጻፍ | ግለትምህርት | ግለግምገማ |
| **ቃላት** | በግጥም ውስጥ የሚገኙ ቃላትን እማሬና ፍካሬያዊ ፍች መግለጽ፤ | እማሬና ፍካሬ ቃላት ፍች፤ | ውይይት | የቡድን ግምገማ |
| **ሰዋስው** | የቃላት ፍች ልዩነት መፈለግ፤ | የግጥም ቃላት ፍች ከሌላው መለየት፤ | የቢጤ መማር | የቢጤ ግምገማ |

**ምዕራፍ ዘጠኝ:- አንድነትና ብዝሃነት(8 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- ✓ አዳምጠው የአካባቢያቸውን ማህበራዊ አውድ ይገልጻሉ።
- ✓ የሚያዳምጡትን ጽሑፍ ወደ ንግግርና ውይይት ለውጠው ያቀርባሉ።
- ✓ የክፍል ውስጥ ንግግራችውን ከጓደኞቻቸው ንግግር ጋር በማነጻጸር ልምድ ይለዋወጣሉ።
- ✓ በመምህሩ/በተጋባዥ እንግዶች የሚቀርቡ ንግግሮችን ይተነትናሉ።
- ✓ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ተጠቅምው መረጃዎችን ይናገራሉ።
- ✓ በተለያዩ ይዘቶች ላይ ጽሑፎችን ካዘጋጁ በኋል ከጓደኞቻቸው ሥራ ጋር ያወዳድራሉ።
- ✓ የጽሕፈት ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ።
- ✓ ካነበባችሁትና ካዳመጣችሁት ያገኛችኋቸውን አዳዲስ ቃላት ተጠቅመው ድርሰት ይጽፋሉ።

| ችሎ ታ | የመማር ብቃት | ይዘት | ማስተማሪያ ዘዴ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| ማዳመጥ | በውይይቶችና በንግግሮች መሳተፍ | ስለአንድነትና ብዝሃነት የሚነገሩ ድስኩሮችን ማዳመጥ፤<br>አንድነትንና ብዝሃነትን መሰረትያደረጉ ውይይቶች ማድረግ፤ | ተሳትፏዊ አቀራረብ፤<br><br>ምልከታ፣ ቃለምልልስና የሰነድ ፍተሻ በማድረግ ውጤቱን ለጓደኛ ማቅረብ፤ | የቃል ጥያቄ<br>ጥያቄና መልስ፤ክፍት ቦታ ሙላና የተጠቃለለ መልዕክት |
| ንግግር | አውድን ተጠቅሞ ንግግሮችንና ሰላምታዎችን ማቅረብ | የመረጃ ክፍተትን በብጤና በቡድን ውይይት መሙላትና አውድን ጠብቆ መናገር፤ | የትብብር መማር ስልት፤<br>ይዘት ተኮር ዘዴ፤<br>ውይይት፤ | የብጤና የቡድን ግምገማ፤<br>በእያንዳንዱ ንግግርና ተግባር ላይ ጽብረቃ ማካሄድ፤ |
| ንባብ | በንባብ ወቅት የተለያዩ የንባብ ስልቶችን መጠቀም፤ | የተለያዩ  የንባብ ዓይነቶችን መጠቀም፤ | መምህር መር ንባብ | ድህረ ንባብ /መልመጃ ተግባራት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ጽሕፈት** | አጭር ጽሑፍ በማዘጋጀት እርስ በርስ ማወዳደርና ማነጻጸር፤ | ጠንካራ የሥራ ባህል ባላቸው ማህበረሰቦች ላይ መሰረት አድርጎ ድርሰት መጻፍ፤<br>ጽሕፈት ደራጃዎችን ጠብቆ መጻፍ፤ | የተለያዩ ድርሰቶችን ለመጻፍ የሚያግዝ ማነቃቂያ መስጠት፣<br><br>የገለጻ ዘዴና በራስ መማር፤ | በክፍል ውስጥ ተግባራት መገምገም፤<br>የመጻፊያ እርዕስ በመስጠትየተሰጣቸውን ርዕስ በአንቀጽ እንዲጽፉ በማድረግ መገምገም፤ |
| **ቃላት** | • የሚያዳምጧቸውንና ያነበቧቸውን ቃላት መጠቀም፤ | የቃላት እውቀት | በአረፆ ሞዴል የቃላት ጨዋታና አጠቃቀም፤ | የቡድን ግምገማ |
| **ሰዋስው** | የተለያዩ የቃላትን ምስረታ ስልቶችን መለየት | የቃላት ምስረታ | ገለጻና ልምምድ | የክፍል ሥራ |

**የምዕራፍ አስር:- ስደት(8 ክፍለ ጊዜ)**
**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች፣ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንዲያደርሱ ይጠበቃል።

- ✓ ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ተነስተው የአካባቢያቸውን ማህበራዊ አውድ ይገልጻሉ።
- ✓ ቀለል ባሉ ንግግሮችና ውይይቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- ✓ ለተለያዩ ሀሳቦች የማጠቃለያ አሳብ ያመነጫሉ።
- ✓ በተለያየ ማህበራዊ አውድ ላይ ንግግር ያደርጋሉ።
- ✓ የቀረበላቸውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ ይዘቱን ይተነትናሉ።
- ✓ መምህሩ የሚጠቁሟቸውን አጋዥ መጻህፍት ያነባሉ።
- ✓ አጭር ጽሑፍ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ያነባሉ።
- ✓ በተመረጡ ርዕሶች ላይ አንቀጽ ይጽፋሉ።
- ✓ በአረፍተ ነገሮች አጻጻፍ ወቅት ትክክለኛ ቃላትን ይጠቀማሉ።
- ✓ ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ።
- ✓ ሰዋስዋዊ ትክክለኝነቱን የጠበቀ አንቀጽ በመጻፍ ያሳያሉ።

| ክሂል | የመማር ብቃት | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴ | ግምገማ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| **ማዳመጥ** | ስለስደት ምክንያትና ውጤት መወያየት፡ | ስለስደትና ቀውሱ የሚቀርቡ ንባቦችን ማዳመጥ፤<br>ስለአንድነትና ብዝሃነት የተጻፉ ጽሑፎችን ማዳመጥ | • ተሳትፏዊ አቀራረብ<br>• ምልከታ፣ ቃለምልልስና፣ የሰነድ አቀራረብ | የቃል ጥያቄ<br>ጥያቄውችን መመለስ፣ ባዶቦታዎችን መሙላት፣ መልክትን አሳጥሮ ማቅረብ |
| **ንግግር** | የሚደመጡ ንግግሮችን መሰረትያደረጉ ማጠቃለያዎችን ማዘጋጀት፡ | የተደራጁ ሀሳቦች ላይ ንግግር ማቅረብ<br>የተለያዩ ሚናዎችን ተላብሶ ንግግር ማቅረብ | የአሰሳ ትምህርትና ጭውውት ተኮር የማስተማር ዘዴ | አጫጭር ጥያቄና መልሶች<br>የቃልና የጽሑፍ ግምገማ |
| **ንባብ** | ያነበቡትን ምንባብ ይዘት አሳጥሮ መጻፍ፤ | ድምጽ አልቦና ግላዊ ንባብ ማድረግ | • የግል ና የ አቻ ለአቻ ትምህርት<br>• የግል ና የተናጠል ትምህርት | • የማገናዘብ መልመጃ<br>• መምህር መር እርማትና ግምገማ<br>• የንባብ ፍጥነት ግለ ግምገማ |
| **ጽሕፈት** | አከራካሪ ድርሰት መጻፍ፤ | አከራካሪ የድርሰት/አንቀፅ አፃፃፎችን መለማመድ<br>ርዕስ መርጦ አንቀጽ መፃፍ | • በቡድን መጻፍ<br>• የግል ጽሕፈት | • የቡድንና<br>• የቢጤ ግምገማ/ምዘና<br>• የተማሪዎችን ተሳትፎ በብጤና በቡድን መገምገም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ቃላት** | ድርብ ቃላትን በትክክል መጠቀም፤ | ድርብ ቃላትን መመስረት<br><br>ስነጽሁፋዊ ፍቺ | • የቡድን ውይይት<br>• የግል ንባብ | • የመምህሩ ክትትል<br>• የግል ምዘና |
| **ሰዋ ስው** | የስምና ግስ ስሙሙነትን በትክክል መጠበቅ፤ | የአረፍተ ነገር አገነባብ ቅንጅትን ማጎልበት፤ | • ምሳሌዎችን በመጠቀም ገለጻ ማድረግ | • ጥያቄ መጠየቅና የተማሪዎችን የ ሰዋስው እውቀት መመዘን |